አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ

የሂዩማንቲስ፣የቋንቋዎች ጥናት፣የጆርናሊዝምና የኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ፣ሥነ ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

የድኅረ ምረቃ መርሐ ግብር

# ባህላዊ የሸክላና አንጥረኝነት ስራ በክስታኔ ማህበረሰብ

በ

ደምስ መሸሻ

ሰኔ 2009 ዓ.ም.

አዲስ አበባ

ባህላዊ የሽክላና አንጥረኝነት ስራ በክስታኔ ማህበረሰብ

አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ

የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣የጆርናሊዝምና የኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

የድኅረ ምረቃ መርሐ ግብር

ለአማርኛ ቋንቋ፣ሥነ ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል ለኤም.ኤ
ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት

በ

ደምስ መሸሻ

አማካሪ፡- አየለ ፍቅሬ (ዶ/ር)

ሰኔ 2009ዓ.ም.

# አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ

## የሂዩማኒቲስ፣የቋንቋዎች ጥናት፣ የጆርናሊዝምና የኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ

## የአማርኛ ቋንቋ፣ሥነ ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

## የድኅረ ምረቃ መርሐ ግብር

# ባህላዊ የሽክላና አንጥረኝነት ስራ በክስታኔ ማህበረሰብ

በ

ደምስ መሸሻ

2009ዓ.ም.

የፈተና ቦርድ አባላት

| አማካሪ ስም | ፊርማ |
|---|---|
| ______________________ | ____________ |
| ______________________ | ____________ |

| ፈታኝ ስም | ፊርማ |
|---|---|
| ______________________ | ________________ |
| ______________________ | ________________ |

# ምስጋና

የጥናቱን ወረቀት ደጋግመው በማረምና ምክር በመስጠት ጊዜዬን በአግባቡ እንድጠቀም የረዱኝን አማካሪዬን ዶ/ር አየለ ፍቅሬን አመሰግናለሁ፡፡ በመቀጠል ለጥናቱ ማከናወኛ የሚሆን የገንዘብ እርዳታ ያደረገልኝን የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲን አመሰግናለሁ፡፡ መስክ ከመሄዴ በፊትም ሆነ በመስክ ላይ እያለሁ በስልክና በአካል መረጃ የሰጣችሁኝን በሙሉ አመሰግናለሁ፡፡ጽሑፉን በኮምቲውተር በመተየብ ያገዘኝን አቶ አብርሃም ረታን አመሰግናለሁ፡፡

# ማውጫ

ይዘት ገፅ

ምስጋና........................................................i
አጠቃሎ ........................................................v
1.መግቢያ........................................................1
1.1. የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት........................................................1
1.2. የጥናቱ ዓላማ........................................................1
1.2.1. የጥናቱ ዋና ዓላማ........................................................1
1.2.2. የጥናቱ ዝርዝር ዓላማዎች፡-........................................................1
1.3. የጥናቱ የምርምር ጥያቄዎች........................................................2
1.4. የጥናቱ ጠቀሜታ ........................................................2
1.5. የጥናቱ ወሰን........................................................2
1.6. የጥናቱ ዘዴ........................................................3
1.6.1. የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች ........................................................3
1.6.1.1. ምልከታ/observation/ ........................................................3
1.6.1.2. ቃለ መጠይቅ/Interview/ ........................................................4
1.6.1.3. የተተኳሪ የቡድን ውይይት/focus group discussion/........................................................4
1.6.2. የመረጃ አደረጃጀት ዘዴ........................................................6
1.6.3. የመረጃ ትንተና ዘዴ........................................................6
1.6.4. የመረጃ ማጠቃለያ ዘዴ ........................................................6
1.7. የመስክ ቆይታ ........................................................7
1.8. ያጋጠሙ ችግሮችና የተወሰዱ የመፍትሔ ሃሳቦች........................................................8
1.9. የጥናቱ አደረጃጀት........................................................9
2. ክለሳ ድርሳናት ........................................................10
2.1. የንድፈ ሃሳባዊ መሰረት........................................................10
2.1.1. የቁሳዊ ባህል ምንነት........................................................10
2.1.2. የቁሳዊ ባህል ዘውጎች ........................................................13
2.1.3. የቁሳዊ ባህል ጥናት ፋይዳ........................................................14
2.1.4. ቁሳዊ ባህልን የመመደቢያ መስፈርቶች........................................................15
2.1.5. የቁሳዊ ባህል መተንተኛ ሞዴሎች ........................................................17
2.1.6. Prown ያቀረባቸው የቁሳዊ ባህል መተንተኛዎች ........................................................19
2.1.7. Fleming ያቀረባቸው የቁሳዊ ባህል መተንተኛ ሂደቶች ........................................................20
2.2. የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት........................................................24
3. የጥናቱ አካባቢያዊ ዳራ ........................................................29
3.1. የክስታኔ ማህበረሰብ ታሪካዊ አመጣጥ ........................................................29

3.2. የወረዳው መልክዓ ምድራዊ ገፅታ ....... 30
3.3. ሃይማኖት ....... 31
3.4. ቋንቋ ....... 31
3.5. የማህበረሰቡ መተዳደሪያ ....... 32
3.6. ክብረ በዓል ....... 32
3.7. ባህላዊ የአስተዳደር ስርዓት ....... 34
3.8. የጋብቻ ስነ ስርዓት ....... 35
3.9. የለቅሶ ስነስርዓት ....... 36
4. በክስታኔ ማህበረሰብ የሸክላና አንጥረኝነት ስራ መረጃ እና ትንተና ....... 38
4.1. የሸክላ ቁሶች አሰራር፣አገልግሎትና የማህበረሰቡ የህይወት ፍልስፍና ....... 38
4.2. በሸክላ ቁሶችና በሰው ልጅ መካከል ያለው ተፈጥሯዊ ተዛምዶ ....... 64
4.3. የሸክላ ባለሙያዎች ለመስሪያነት የሚጠቀሙባቸው ቁሶች ስምና ተግባር ....... 65
4.4. የሸክላ ስራ ደረጃዎች ....... 65
4.4.1. የሸክላ አፈርን የመቆፈር ተግባር ....... 66
4.4.2. የሸክላ አፈርን ለስራ የማዘጋጀት ተግባር ....... 66
4.4.3. ቁሶችን በተለያየ መጠንና ቅርፅ የመስራት ተግባር ....... 67
4.4.4. ቁሶቹን በተለያየ ቦታ ላይ የማስጌጥ ተግባር ....... 67
4.4.5. ቁሶችን የመተኮስና የማሰር ተግባር ....... 68
4.5. የሸክላ ቁሶች ጠቀሜታ ....... 68
4.5.1. ማህበራዊ ጠቀሜታ ....... 68
4.5.1.1. ፈሳሽ ነገሮችን ለማዘጋጃነትና ለማቅረቢያነት የሚያገለግሉ ቁሶች ....... 68
4.5.1.2. ምግብ ለማዘጋጃነትና ለማቅረቢያነት የሚያገለግሉ ቁሶች ....... 68
4.5.2. የሸክላ ቁሶች ባህላዊ አገልግሎት ....... 69
4.5.2.1. ሀብታምነትን የሚያመለክቱ የሸክላ ቁሶች ....... 69
4.5.2.2. ድህነትን የሚያመለክቱ የሸክላ ቁሶች ....... 69
4.5.3. ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ....... 69
4.6. በሸክላ ስራ ላይ የባለሙያዎቹ ፆታዊ ተሳትፎ ....... 70
4.7. የሸክላ ባለሙያዎች እምነት ....... 71
4.8. በአንጥረኛ ባለሙያዎች የሚሰሩ ቁሶች መረጃ ትንተና ....... 72
4.9. በአንጥረኛ ባለሙያዎች የሚሰሩ ቁሶች አሰራር፣ አገልግሎትና የማህበረሰቡ የህይወት ፍልስፍና ....... 72
4.10. ለአንጥረኛ ባለሙያዎች መስሪያ የሚያስፈልጉ ቁሶች ስምና አገልግሎት ....... 81
4.11. በአንጥረኛ ባለሙያዎች የሚሰሩ ቁሶች የሚያልፏቸው ደረጃዎች ....... 82
4.11.1. የከሰል እንጨት ፈለጣና በወናፍ ከሰሉን የማቀጣጠል ተግባር ....... 83
4.11.2. ብረታ ብረቱን እሳት ውስጥ የማስገባትና ማገለባበጥ ተግባር ....... 83

4.11.3. የጋለውን ብረታ ብረት በጉጠት የማውጣትና መቆራረጥ ተግባር ....83
4.11.4. ብረታ ብረቱን በመዶሻ በመቀጥቀጥ ቅርፅ የማውጣት ተግባር ....83
4.11.5. ቁሶቹን የመሞረድ ተግባር ....84
4.12. በአንጥረኛ ባለሙያዎች የሚሰሩ ቁሶች ጠቀሜታ ....84
4.12.1. ማህበራዊ ጠቀሜታ ....84
4.12.1.1. ከእንስት ስራ ጋር የተያያዙ ቁሶች....84
4.12.1.2. ከእንስሳት ጋር የተያያዙ ቁሶች ....85
4.12.2. ባህላዊ አገልግሎት ....85
4.12.3. ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ....86
4.13. በአንጥረኛ ባለሙያ የሚሰሩ ቁሶች ወቅታዊ ሁኔታ ....86
4.13.1.ድሮ የሚሰሩና በአሁኑ ወቅት የመሰራት መጠናቸው የቀነሱ ቁሶች ....86
4.13.2. ድሮ የማይሰሩና በአሁኑ ወቅት የሚሰሩ ቁሶች ....87
4.14. በአንጥረኝነት ስራ ላይ የባለሙያዎቹ ፆታዊ ተሳትፎ ....87
5.ማጠቃለያና የይሁንታ ሃሳብ ....89
5.1. ማጠቃለያ....89
5.2. የይሁንታ ሃሳብ....91
ዋቢ ጽሑፎች
አባሪዎች
አባሪ 1 ለሽክላ ባለሙያዎች የቀረቡ መሰረታዊ ጥያቄዎች
አባሪ 2 ለአንጥረኛ ባለሙያዎች የቀረቡ መሰረታዊ ጥያቄዎች
አባሪ 3 ለሀገር ሽማግሌዎችናታሪክ አዋቂዎች የቀረቡ መሰረታዊ ጥያቄዎች
አባሪ 4 ለወረዳው ባህልና ቱሪዝም ጽ/ቤት የቀረቡ መሰረታዊ ጥያቄዎች
አባሪ 5 ለወረዳው ጥቃቅንና ንግድ ኢንዱስትሪ ጽ/ቤት የቀረቡ ጥያቄዎች
አባሪ 6 በሸክላና አንጥረኛ ባለሙያዎች የሚሰሩ ቁሶችና አገልግሎታቸው
አባሪ 7 የአውራ መረጃ አቀባዮች ዝርዝር
አባሪ 8 የፎቶ ንባብ
አባሪ 9 ካርታዎች

# አጠቃሎ

ይህ ጥናት ባህላዊ የሸክላና አንጥረኝነት ስራ በክስታኔ ማህበረሰብ በሚል ርዕስ የተከናወነ ነው። የጥናቱ ዋና ዓላማ አድርጌ የተነሳሁት በሸክላና አንጥረኛ ባለሙያዎች የሚሰሩ ቁሶች አሰራርና አገልግሎት መተንተን እንዲሁም በቁሶቹ አማካኝነት የማህበረሰቡን የህይወት ፍልስፋና መመርመር ነው።

የጥናቱን ዓላማ ከግብ ለማድረስ የቤተ መፅሃፍት ንባብ እንዲሁም ጥናቱ በሚከናወንበት ቦታ ላይ በአካል በመገኘት በምልከታ፣በቃለ መጠይቅና ተተኳሪ ቡድን ውይይት የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎችን በመጠቀም መረጃዎችን ለመሰብሰብ ችያለሁ። መረጃዎቹን እንደ አስፈላጊነቱ በቪዲዮና በፎቶ ግራፍ ተሰንደዋል።

የተግባራዊ ንድፈ ሃሳብን/Functional theory/ እንዲሁም የSchlereth ሞዴሎች( ታሪካዊ ጥበብ አመልካች፣ትዕምርታዊነት፣ባህላዊነት፣አካባቢያዊነት፣አገልግሎት፣መዋቅራዊነት፣ባህርይ ጠቋሚነት፣ማህበራዊነትና ታሪክ ገላጭነትን) በመጠቀም መረጃዎቹ ተተንትነዋል። በሸክላና በአንጥረኛ ባለሙያዎች የሚሰሩ ቁሶች አሰራርና አገልግሎት ምን ይመስላል?ቁሶቹ የማህበረሰቡን የህይወት ፍልስፍና በምን መልኩ ያሳያሉ? የሸክላ ስራ በሴቶች የአንጥረኝነት ስራ ደግሞ ወንዶች ለምን ይተገበራል? የሚሉ ጉዳዮችን ተመልክቼ የሚከተለው መደምደሚያ ላይ ደርሻለሁ።

ጥናቴ ባተኮረባቸው ቀበሌዎች ላይ የቁሶቹ አሰራርና አገልግሎት ተመሳሳይነት ያላቸው መሆኑ ታውቋል። በክስታኔ ማህበረሰብ የአማች መመገቢያ ጣባ ጌጥ የሚደረግበት ምክንያት ከዘመድ ይልቅ ለአማች ትልቅ ክብር የሚሰጡ መሆናቸው ማሳያ መሆኑን በጥናቱ ታውቋል። በሰርግ፣በለቅሶና መሰል የማህበራዊ ህይወት ላይ ለመሳተፍ በእግር ሲጓዙ አባወራዎች ከፊት እማወራዎች ደግሞ ተከትለው የሚሄዱ መሆናቸው ታውቋል። ማህበረሰቦቹ በመገልገያ ቁሶቹ አማካኝነት የኢኮኖሚ ደረጃቸውን፣ማህበራዊ ቦታቸውንና ባህላዊ አኗኗራቸውን የሚገልፁ መሆናቸውን በጥናቱ ታውቋል። ‹‹አፈሳ አፈር›› ተበጥብጦ በሚጠለው ውሃ ጎመን በሚቀቀልበት ወቅት መልኩን እንዳይቀይር የሚያስችል መሆኑ ታውቋል። የሸክላ ቁሶች በቤት ውስጥ አገልግሎት የሚሰጡ መሆናቸውና አፈር መፍጨትና ማቡካት ከእህል መፍጨትና ማቡካት ጋር ተመሳሳይነት ስላለው በሴቶች እንዲሰሩ ምክንያት መሆኑን ጥናቱ አረጋግጧል።

አንጥረኝነት ስራ በወንዶች የሚከናወነው ቁሶቹ ለእርሻና አደን ተግባር መከወኛ የሚያገለግሉ በመሆናቸው እና ስራው ጠንከር ያለ ጉልበትን የሚጠይቅ በመሆኑ ምክንያት እንደሆነ ተረጋግጧል። የቢላዋ ቅርፅ መነሻ የተሰነጠቀ ሸንበቆ ሲሆን፣ የማጭድ ቅርፅ ደግሞ በጋማ ከብት ላይ ያሉ ጥርሶች መሆናቸው ታውቋል።

የጥናቱን ግኝት መነሻ በማድረግ የሃይማኖት አባቶች፣ ሀገር ሽማግሌዎች፣የወረዳው ጥቃቅንና ንግድ ኢንዱስትሪ እንዲሁም ባህልና ቱሪዝም ጽ/ቤት በባለሙያዎቹ የሚሰሩ ቁሶችን በቅርስነት የሚቀመጡበት ሁኔታ ቢመቻች መልካም ነው የሚል የይሁንታ ሃሳብ ሰንዝሬአለሁ።

# 1.መግቢያ

## 1.1. የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት

ይህን ጥናት ባካሄድኩበት ቦታ ላይ በመንግስት መስሪያ ቤት ተቀጥሬ ለአምስት ዓመት ያህል አገልግያለሁ፡፡ በቆይታ ጊዜዬ የተሳተፍኩባቸውና የተመለከትኳቸው ማህበራዊና ባህላዊ አውዶች ነበሩ፡፡ ትኩረቴን ይስብ የነበረው ግን የሸክላ ሰሪ ባለሙያዎች አደይ ሲፈነዳ ቀያቸውንና ስራቸውን ለቀው በተለያዩ ቀበሌዎች የሚዞሩት ከሙያቸው ጋር ምን ግንኙነት እንዳለው መገንዘብ ነው፡፡ በሌላ መልኩ የሸክላና አንጥረኛ ባለሙያዎች የተለያዩ ቁሶችን ሲሰሩ መነሻ የሚያደርጉትን ቅርፅ ምን እንደሆነ በጥናት ለመረዳት ነው፡፡

በክስታኔ ማህበረሰብ ላይ በቁሶቹ አማካኝነት የማህበረሰቡን የህይወት ፍልስፍና የሚያሳይ ጥናት ባለመኖሩና በቁሳዊ ባህል ጥናት ውስጥ የታዩ ክፍተቶችን በተወሰነ መልኩ ለመሙላት ነው፡፡ የሸክላና አንጥረኛነትን ስራ በጥምርታ ማጥናት የፈለኩበት ምክንያት በባለሙያዎች የሚሰሩ ቁሶች ከተቀዳሚው አገልግሎታቸው ባሻገር በማህበረሰቡ ውስጥ ትዕምርት ያላቸው በመሆናቸው ነው፡፡

ሌላኛው ምክንያት ደግሞ የሁለተኛ ዲግሪ ለማግኘት ከሚጠበቁ ግዴታዎች መካከል አንዱ ጥናትና ምርምር መስራት በመሆኑ ጥናቱን አካሂጃለሁ፡፡

## 1.2. የጥናቱ ዓላማ

ይህ ጥናት የሚከተሉት ዓብይና ንዑስ ዓላማዎች አሉት፡፡

### 1.2.1. የጥናቱ ዋና ዓላማ

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ በክስታኔ ማህበረሰብ በሸክላና አንጥረኛ ባለሙያዎች የሚሰሩ ቁሶችን አሰራርና አገልግሎት መተንተን እንዲሁም በቁሶቹ አማካኝነት የማህበረሰቡን የህይወት ፍልስፍና መመርመር ነው፡፡

### 1.2.2. የጥናቱ ዝርዝር ዓላማዎች፡-

የዚህ ጥናት ዝርዝር ዓላማዎች የሚከተሉት ናቸው፡፡ እነሱም፡-በሸክላና አንጥረኛ ባለሙያዎች የሚሰሩ ቁሶች ማህበረሰቦቹ የሚጠቀሙባቸው ከምን አስተሳሰብ በመነሳት

እንደሆነ ማሳየት እንዲሁም ከሸክላ አፈርና ብረት የሚሰሩ ቁሶቹ ለማህበረሰቡ የሚሰጡትን አገልግሎት መግለፅ ነው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ቁሶቹን ሲሰሩ መነሻ የሚያደርጉትን ቅርፅ መግለፅ እና ቁሶችን በምን አይነት ብልሃት እንደሚያበጁ ማሳየት ነው፡፡

## 1.3. የጥናቱ የምርምር ጥያቄዎች

ይህ ጥናት ዋና እና ዝርዝር ዓላማዎችን መነሻ በማድረግ የሚከተሉትን ጥያቄዎች ይመልሳል፡፡ እነሱም፡- በሸክላና አንጥረኛ ባለሙያዎች የሚሰሩ ቁሶች የማህበረሰቡን የህይወት ፍልስፍና በምን መልኩ ያሳያሉ? በሸክላና አንጥረኛ ባለሙያዎች የሚሰሩ ቁሶችን ማህበረሰቦቹ ከምን አስተሳሰብ በመነሳት ይገለገሉባቸዋል? የሸክላና አንጥረኛ ባለሙያዎች የሚሰሯቸው ቁሶች አሰራራቸው ምን ይመስላል? በሸክላና አንጥረኛ ባለሙያዎች የሚሰሩ ቁሶች የሚሰጡት አገልግሎት ምንድን ነው? እንዲሁም የሸክላና አንጥረኛ ባለሙያዎች ቁሶችን ሲሰሩ መነሻ የሚያደርጉት ቅርፅ ምንድን ነው? የሚሉት ናቸው፡፡

## 1.4. የጥናቱ ጠቀሜታ

ጥናቱ ለአማርኛ ቋንቋ፣ስነፅሁና ፎክሎር ትምህርት ክፍል፣ለተጠኚው ማህበረሰቦችና ለወረዳው ባህልና ቱሪዝም ጽ/ቤት የሚከተሉትን ጠቀሜታዎች ያስገኛል፡፡ ለአማርኛ ቋንቋ፣ስነፅሁፍና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት የሚያስገኘው ጠቀሜታ በቁሳዊ ባህል ጥናት ውስጥ ጎልተው የሚስተዋሉ ክፍተቶችን በተወሰነ መልኩ ይሞላል፡፡ ለተጠኚው የማህበረሰብ ክፍሎች ደግሞ በቁሶቹ አማካኝነት ባህላቸውን የበለጠ እንዲያስተዋውቁ እድል ይሰጣቸዋል፡፡ በሌላ መልኩ ለወረዳው ባህልና ቱሪዝም ጽ/ቤት የሚሰጠው ጠቀሜታ ደግሞ በሸክላና አንጥረኝ ባለሙያዎች የሚሰሩ ቁሶች የቱሪዝም መስብ የሚሆኑበትን መንገድ ይጠቁማል፡፡

## 1.5. የጥናቱ ወሰን

ይህ ጥናት ከቦታ አንፃር በደቡብ ብሔር፣ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልል በጉራጌ ዞን በሶዶ ወረዳ ስር ከሚገኙ ሃምሳ ስምንት ቀበሌዎች መካከል በስድስቱ ቀበሌዎች ላይ ያተኮረ ነው፡፡ የሸክላ ስራ በሱተን ዙሪያ፣ ዋጬ እና ቆላ ኑረና ቀበሌዎች ላይ ሲሆን የአንጥረኝነት ስራ ደግሞ ዳሞ አንድ ቀበሌ፣ቡኢ ዙሪያ እና ኬላ ዙሪያ ቀበሌዎች ላይ ያነጣጠረ ነው፡፡

ከርዕሰ ጉዳይ አንፃር ደግሞ በሸክላ ባለሙያዎች ከሚሰሩ ቁሶች መካከል በሚከተሉት ላይ ያተኮረ ነው። እነሱም፦ ኩሮ፣ኮለሊት፣ደንጋሳ፣ነክብ፣ ጣባ፣ጀበና፣ጉልላት፣ገንቦ፣ጥወ፣ትክዬ፣ እንጨቡዬ፣ክርን፣መስመስያ፣ ጋውዝዬ፣ድፋት፣ሸሸትና ሻማ፣ ናቸው።

በአንጥረኛ ባለሙያዎች ከሚሰሩ ቁሶች መካከል ደግሞ /ሰንዳ፣ጦር፣ወለት፣ቆፋሪ፣የብረት ሲቢሳ፣ቁንጥል፣የብረት ዣግባ፣ቃጭል፣የብረት ድግር፣ማጭድ፣ ቢላዋና የብረት ምድጃ/ ሲሆኑ በቁሶቹ አሰራር፣አገልግሎትና በማህበረሰቡ የህይወት ፍልስፍ ላይ ያተኮረ ነው።

## 1.6. የጥናቱ ዘዴ

የጥናቱ ዘዴ በሚለው ሥር የመረጃ መሰብሰቢያ፣የመረጃ አደረጃጀት ፣የመረጃ ትንተናና የመረጃ ማጠቃለያ ዘዴ የሚሉት ተካተዋል።

### 1.6.1. የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች

የጥናቱን ዓላማ ከዳር ለማድረስ ቀዳማይና ካልዓይ የመረጃ ምንጮችን ተጠቅሜ አስፈላጊ መረጃዎችን ሰብስቤአለሁ። ወደ መስክ ከመሄዴ በፊት በርዕሰ ጉዳይ ዙሪያ የተሰሩ ጥናቶችንና በመስኩ ምሁራን የተዘጋጁ መፃህፍትን አንብቤአለሁ። በመቀጠል የጥናቱ ርዕስ በተመረጠበት ቦታ ላይ በአካል በመገኘት በሚከተሉት የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች መረጃዎችን ሰብስቤአለሁ። የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎቹ በምልከታ፣ቃለ መጠይቅና የተተኳሪ ቡድን ውይይት ናቸው።

#### 1.6.1.1. ምልከታ/observation/

የሸክላና አንጥረኛ ባለሙያዎች ቁሶቹን ሲሰሩ ስምምነታዊ ምልከታ በማድረግ የቁሶቹን የአሰራር ሂደትና የሚያልፉትን ደረጃ ተመልክቻለሁ።

መረጃዎችን የሰበሰብኩት ተፈጥሮአዊ መቼትን ተጠቅሜ ነው። በተፈጥሮአዊ መቼት መረጃ ለማግኘት ያስቸገረኝን ደግሞ ቅንብራዊ ተፈጥሯዊ መቼቶችን/Natural settings/ በመጠቀም መረጃዎችን ሰብስቤአለሁ። የሰበሰብኳቸውን መረጃዎች በቪዲዮ ካሜራ በመቅረፅ ሰንጃለሁ።

#### 1.6.1.2. ቃለ መጠይቅ/Interview/

የጥናቴን አላማ ለማሳካት ሌላኛው የተገለገልኩበት የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ ቃለ መጠይቅ ነው፡፡ ለቃለ መጠይቅ የተመረጡት መረጃ አቀባዮቼ ወንድ 24 ሴት ደግሞ 22 በአጠቃላይ 46 ናቸው፡፡ ሴትና ወንድ መረጃ አቀባዮቼ በቁጥር እኩል ያልሆኑበት ምክንያት መስፈርቶቼን ተጠቅሜ የመረጥኳቸው መረጃ አቀባዮች ቁጥር በተገለፀው መልኩ ስለመጣ ነው፡፡ የመረጃ አቀባዮቼ የእድሜ ክልል ከ25-90 ዓመት ድረስ ያለውን ያካተተ ነው፡፡ ከወጣት እስከ ሽማግሌ ድረስ ያካለልኩበት ምክንያት የእድሜ ባለፀጋዎቹ ድሮ ይገለገሉባቸው ስለነበሩ ቁሶች ስያሜ፣ አገልግሎታቸውና ተጠቃሚው የማህበረሰብ ክፍል ለቁሶቹ የነበራቸውን አመለካከት እንዲነግሩኝ ስለፈለኩ ነው፡፡ ወጣቶቹ ደግሞ የሀገር በቀል ቁሶችን ስም፣አገልግሎትና ለቁሶቹ ያላቸውን አመለካከት እንዲገልፁልኝ በመፈለግ ነው፡፡

ለቃለ መጠይቅ የተመረጡት መረጃ አቀባዮች በሚከተሉት መስፈርት ነው፡፡ እነሱም፡-የአካባቢውን ባህልና ታሪክ በአግባቡ የሚያውቁ፣ ከርዕሰ ጉዳዩ ጋር ቅርበት ያላቸው እና ቁሶቹ በማህበረሰቡ ውስጥ ሲሰጡት የነበረውንና እየሰጡት ያለውን አገልግሎት የሚያውቁ የሚሉት ተጠቃሽ ናቸው፡፡ ቃለ መጠይቅ የተጠቀምኩት በምልከታ ወቅት ማግኘት ያልቻልኩትን መረጃ ለማግኘት ሲሆን የተገኙትን መረጃዎች በምስልና ድምፅ ሪከርድ ተሰንዷል፡፡

#### 1.6.1.3. የተተኳሪ የቡድን ውይይት/focus group discussion/

በቃለ መጠይቅ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ ከተሰበሰቡት መረጃዎች ውስጥ እርስበርስ የሚፋለሱትን ሃሳቦች በአግባቡ በመለየት ትክክለኛውን መረጃ ለማጣራት የተተኳሪ የቡድን ውይይት ዘዴን ተጠቅሜአለሁ፡፡

ይህን ዘዴ ተግባራዊ ሳደርግ መረጃ አቀባዮቼን በሚከተሉት መስፈርቶች መርጫለሁ፡፡ እነሱም፡-የአካባቢውን ባህል ጠንቅቆ ማወቅ፣ ድሮ ይሰሩ የነበሩ ቁሶችን ስያሜና አገልግሎት የሚያውቅና ከርዕሰ ጉዳዩ ጋር ቅርበት ያላቸው የሚሉት ተጠቃሽ ነበሩ፡፡ በዚህ መስፈርት መሰረት ባለሙያዎች ፣ከሙያው ውጭ ያሉ የማህበረሰብ ክፍል እና ከሙያ ጋር ቅርበት ያላቸው የመስሪያ ቤት ሰራተኛ በሚል በሶስት ከፈልኳቸው፡፡

በቆላ ኑረና ቀበሌ ውስጥ በቁጥር ስምንት ከሆኑ የሸክላ ባለሙያዎች ጋር ለተከታታይ ሁለት ሰዓት ያህል ውይይት ተደርጓል። የመወያያው ርዕስ አደይ ሲፈነዳ የሸክላ ስራችሁንና ሰፈራችሁን ለቃችሁ የምትሄዱት ለምንድን ነው? የሸክላ ስራ በሴቶች ብቻ የሚሰራው ለምንድን ነው? የሚሉት ሲሆኑ ለመወያያ እንዲሆኑ የተመረጡት ጥያቄዎች ግን በቃለ መጠይቅ ወቅት የተሰበሰቡት መረጃዎች ተጣራሽ ሆነው በተገኙት ላይ ብቻ እንጂ በቃለመጠይቅ የተጠየቁትን ጥያቄዎች እንዳለ መድገም ላይ ያተኮረ አይደለም።

በዳሞ ቀበሌ በቁጥር 13 ከሆኑ የአንጥረኛ ባለሙያዎች ጋር ለሁለት ሰዓት ተኩል ያህል ስለቁሶቹ የአሰራር ሂደት፣ማህበረሰብ ለቁሶቹ ያላቸው አመለካከት፣ቁሶቹን የምትሰሩት ምን መነሻ ቅርፅ ይዛችሁ ነው? እንዲሁም የአንጥረኝነት ሙያ በወንዶች ብቻ የሚከወነው ለምንድን ነው? በሚሉት ላይ ውይይት ተደርጓል።

በቡኢ ከተማ ባህልና ቱሪዝም ቢሮ ውስጥ ከሚሰሩ ባለሙያዎችና የአካባቢውን ባህል ከሚያውቁ የማህበረሰብ ክፍል ጋር በአንጥረኛና ሸክላ ባለሙያዎች የሚሰሩ ቁሶች የማህበረሰቡን ምን የህይወት ገፅታ ያሳያሉ በሚለው ርዕስ ላይ ውይይት አድርገዋል።

በኬላ ዙሪያ ቀበሌ የአካባቢውን ባህልና ወግ በአግባቡ ከሚያውቁ የማህበረሰብ ክፍል ጋር የሸክላ ባለሙያዎች አደይ ሲፈነዳ ለምን ይለምናሉ? የሸክላ ባለሙያዎች በሚለምኑበት ወቅት ማህበረሰቡ ቤት ያፈራውን ነገር የሚሰጣቸው ለምንድን ነው? በሚሉት መጠይቆች ዙሪያ ውይይት ተደርጓል።

በቃለ መጠይቅ ወቅት የሸክላ ባለሙያዎች አደይ ሲፈነዳ ስራቸውን ትተው ለምን ወደ ሌላ ቀበሌዎች እንደሚሄዱ ተጠይቀው አብዛኛዎቹ መረጃ ለመስጠት ፈቃደኛ አልነበሩም።

በተተኳሪ ቡድን ውይይት ወቅት ግን አንድ ሰው መረጃ ሲሰጥ ሲመለከቱ ከማን አንሳለሁ በሚል የፉክክር መንፈስ ተጨማሪ ሃሳብ አለ እያሉ ትክክለኛ መረጃ ሰጥተውኛል። እውነተኑት የሌለው መረጃ ከሰጠሁ ታማኝነትን አጣለሁ ውሸታም የሚል ስም ማህበረሰቡ ይሰጠኛል በሚል ስጋቻ ጭምር እንደሆነ ሌሎች መረጃ አቀባዮቼን በመጠየቅ አረጋግጫለሁ።

በወረዳው ውስጥ ካሉት ቀበሌዎች ውስጥ ስድስቱ የተመረጡት በሚከተለው መስፈርት ነው። እነሱም ፦የሸክላና አንጥረኛ ባለሙያዎች በብዛት የሚገኙበት አካባቢ፣በሸክላና አንጥረኝነት ሙያ ላይ ለረዥም ጊዜ የቆዩ፣አዳዲስ ቁሶችን ሰርተው የሚያስተዋውቁ፣ የተለያዩ ቁሶችን የሚሰሩ፣ባለሙያዎቹ ቁሶቹን በሚሸጡበት ገበያ አቅራቢያ የሆነ እንዲሁም ለሌሎች ቀበሌዎች አማካይ የሆኑ ቦታዎች የሚሉት ይገኙበታል። በወረዳው ውስጥ ከሚገኙ

ቀበሌዎች ውስጥ በስድስቱ ላይ ብቻ ያተኮረበት ምክንያት ከላይ በተጠቀሰው የመምረጫ መስፈርት መሰረት ስድስቱ ቀበሌዎች በመረጃ አቀባዮቼ ስለተመረጡ ነው።

### 1.6.2. የመረጃ አደረጃጀት ዘዴ

በምልከታ፣ቃለመጠይቅና የተተኳሪ ቡድን ውይይት የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎችን ተጠቅሜ የሰበሰብኳቸውን መረጃዎች ለየብቻቸው አደራጀሁ። በመቀጠልም ቅደም ተከተላቸውን በጠበቀ መልኩ የእርማት ተግባር አከናወንኩ። እርማት ያደረኩባቸውን መረጃዎች መለያ ምልክት አስቀመጥኩ በማስከተልም በየርዕሰ ጉዳይ ውስጥ እንዲገቡ በመከፍፈል አሰናዳሁ።

### 1.6.3. የመረጃ ትንተና ዘዴ

በተለያዩ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች የተሰበሰቡትን መረጃዎች ለየብቻቸው የመለየትና እርማት ተግባር ከሰራሁ በኂላ ተመሳሳይነት ያላቸው ይዘቶችን ለየሁ። በመቀጠልም ርዕስ ሰጠኂቸው። በእያንዳንዱ ርዕስ ስር ሊካተቱ የሚችሉ ሃሳቦችን በመለየት የሃሳብ ቅደም ተከተላቸውን መሰረት በማድረግ አካትቼ ትንታኔ ሰጥቻለሁ።

### 1.6.4. የመረጃ ማጠቃለያ ዘዴ

ስለ ቁሶቹ አሰራርና ጥሬ እቃዎቹ ወደ ቁስነት ደረጃ የሚያልፉበትን መንገድ ባለሙያዎቹ በሚሰሩበት ቦታ ላይ በአካል ተገኝቼ ስምምነታዊ ምልከታ በማድረግ መረጃዎችን ሰብስቤአለሁ። ማህበረሰቡ ለቁሶቹ ያላቸውን እይታ በተመለከተ መረጃዎቹን የሰበሰብኩት ደግሞ ቃለ መጠይቅን በመጠቀም ነው። በቃለ መጠይቅ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ የተሰበሰቡና እርስ በርሳቸው የሚጋጩ መረጃዎችን በተተኳሪ የቡድን ውይይት ወቅት ለማጣራት ችያለሁ።

በሦስቱም የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች የተሰበሰቡ መረጃዎችን እንደአስፈላጊነቱ በመቅረፀ ድምፅ፣በፎቶና በቪዲዮ ካሜራ ተሰንደዋል። በዚህ ዘዴ የተሰበሰቡት መረጃዎች ቁሳዊ ባህል ከሚጠናባቸው ንድፈሃሳቦች ውስጥ ተግባራዊ ንድፈ ሃሳብ /functional theory/ ጥቅም ላይ ውሏል። ገላጭ የምርምር ዘዴን በመጠቀም ትንታኔ ተሰጥቷል።

## 1.7. የመስክ ቆይታ

የጥናቱ ርዕስ ከፀደቀበት ቀን ጀምሮ የሶዶ ወረዳ ባህልና ቱሪዝም ሃላፊን በስልክ ለማግኘት ጥረት አድርጌአለሁ፡፡ በአቶ አዳነ ቦጋለ አማካኝነት የወረዳውን ባህልና ቱሪዝም ቢሮ ሃላፊ ስምና ስልክ ቁጥር ተቀበልኩ፡፡ የወረዳው ባህልና ቱሪዝም ሃላፊ የሆኑትን ወ/ሮ የውቤ ኮርቡ ዲረሳ በስልክ አግኝቼ የጥናቴን ዓላማ በመግለፅ የሸክላና የአንጥረኛ ባለሙያዎች በየትኞቹ ቀበሌዎች እንደሚኖሩ፣የማህበረሰቡን ባህልና ታሪክ  እነማን በአግባቡ ያውቃሉ? በሚሉ ነጥቦች ላይ ውይይት አድርገናል፡፡ 4/05/09 ለጥናቱ የሚያስፈልገኝን ገንዘብና ቁሳቁስ በአግባቡ በመያዝ ወደ ሶዶ ወረዳ ተጓዝኩ፡፡ ወረዳው ላይ በአካል እንደደረስኩ ወደ ባህልና ቱሪዝም  ቢሮ አመራሁ፡፡ ከአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ አማርኛ ቋንቋ፣ስነፅሁፍና ፎክሎር ት/ክፍል የተፃፈልኝን የትብብር ደብዳቤ ለባህልና ቱሪዝም ቢሮ ሃላፊና ለባለሙያዎች አሳየሁ፡፡ የጥናቴን ዓላማ አስረዳሁ፡፡ ሃላፊዋና ባለሙያዎቹ የሚደረገው ጥናት የክስታኔን ማህበረሰብ ማንነት ለሌላው የማህበረሰብ ክፍል በማስተዋወቅ በኩል ያለው ድርሻ ከፍተኛ በመሆኑ አስፈላጊውን ትብብር እንደሚያደርጉልኝ ገለፁልኝ፡፡ በመቀጠልም ስለ ክስታኔ ማህበረሰብ ባህልና ታሪክ በአግባቡ የሚያውቁ ሰዎችን መረጡልኝና በአካል አስተዋወቁኝ፡፡ ካስተዋወቁኝ የመረጃ አቀባዮቼ መካከል የተወሰኑትን አውቃቸው ስለነበር  በእነሱ አማካኝነት ሌሎች የመረጃ ሰጪዎቼን ተዋወኩ፡፡

የክስታኔ ማህበረሰብ ባህልና ወግ ማወቅ እንደምፈልግ ገለፅኩላቸው፡፡ በዚህ መንገድ የተጀመረው ውይይት ወደ ባህልና ታሪክ፣ሃይማኖት፣ቋንቋ፣ባህላዊ አስተዳደር፣የሰርግና ሃዘን ስነስርዓትን ምን እንደሚመስል መረጃ እንዲሰጡኝ አደረኩ፡፡

በማስከተልም የሸክላና አንጥረኛ ባለሙያዎች በየትኞቹ ቀበሌዎች ውስጥ እንደሚገኙ እንዲለዩልኝ አደረኩ፡፡ የመምረጫው መስፈርት ብዙ ባለሙያዎች የሚገኙበት ቦታ፣ የተለያዩ ቁሶችን የሚሰሩ እንዲሁም አዳዲስ አይነት አሰራር የሚያስተዋውቁ ባለሙያዎች የሚሉት ተጠቃሽ ናቸው፡፡ የተመረጡትም ሰዎች ተወያይተው የሸክላ ባለሙያዎች ሱተን ዙሪያ፣ቆላኑረና እና ዋጮ ቀበሌዎች እንደሚገኙ የአንጥረኛ ባለሙያዎች ደግሞ ኬላ ዙሪያ፣ዳሞና ቡኢ ዙሪያ ቀበሌዎች ውስጥ እንደሚገኙ ገልፁልኝ፡፡ ለጥናቱ የተመረጡልኝ ቀበሌዎች የተወሰኑትን አውቃቸው ስለነበረ በየቀበሌዎቹ በመዘዋወር የማላውቃቸውን ቀበሌዎች ደግሞ በመንገድ መሪ አማካኝነት በመንቀሳቀስ  ከየቀበሌዎቹ የስራ ሃላፊዎች ጋር ውይይት አካሄድኩ፡፡

ስለሽክላና አንጥረኝነት ስራ መረጃ ሊሰጡኝ የሚችሉ አካላትን እንዲጠቁሙኝ አደረኩ፡፡ የተጠቀምኩትን መረጃ አቀባዮች ስም ሰንጠረዥ በማዘጋጀት ከተራ ቁጥር 1-4 ወደ ጎን በመፃፍ ማን አንድ ጊዜ ፣ማን ሁለት ጊዜ፣ማን ሦስት ጊዜና ማን አራት ጊዜ እንደተጠቀመ ለመለየት የሚከተለውን ምልክት ተጠቅሜአለሁ::

- ✓ በጥቆማ የተመረጡትን ሰዎች እንዳለ የመረጃ አቀባዮቹ አድርጌ ከመውሰድ ይልቅ በሙያው ላይ ለብዙ ዓመት መቆየት እንዲሁም የተለያዩ ቁሶችን መስራት የሚሉትን እንደ ተጨማሪ መስፈርት ተጠቅሜ አውራ የመረጃ አቀባዮቼን ለይቻለሁ፡፡

ለጥናቱ አስፈላጊ የሆኑትን መረጃዎች የሰበሰብኩት ባለሙያዎቹ በሚኖሩበት መንደር፣በሚሰሩበት ቦታና ቁሶቹን በሚሸጡበት ገበያ ቦታ በአካል ተገኝቼ ነው፡፡ የተለያዩ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎችን በመጠቀም ጉዳዩ ከሚመለከታቸው አካላት መረጃዎችን እስከ የካቲት 20/2009ዓ.ም ድረስ ከሰበሰብኩ በኋላ ወደ አዲስ አበባ በመመለስ በፎቶና በካሜራ የተቀረፁትን መረጃዎች ወደ ሲ.ዲ አስገለበጥኩ፡፡ የተሰበሰቡትን መረጃዎች ከተመረጡ ትውሮች ጋር በማናበብ ትንታኔ አካሄድኩ፡፡ በመቀጠልም የመጀመሪያውን የጥናቴን ረቂቅ ሰርቼ ለተመደበልኝ አማካሪ ከነሲዲው አስረከብኩ፡፡ ከአማካሪዬ የተሰጠኝን አስተያየት ለማስተካከል ለሁለተኛ ዙር 19/07/09/-18/08/09 ዓ.ም ድረስ በመስክ በመቆየት የተጓደሉትን መረጃዎች ሰብስቤ በተፈላጊው ቦታ ውስጥ አካተትኩ፡፡

## 1.8. ያጋጠሙ ችግሮችና የተወሰዱ የመፍትሔ ሃሳቦች

ይህን ጥናት ሳከናውን የገጠመኝ መሰናክል በመስክ ስራ ላይ ነው፡፡ በመስክ ቆይታዬ ላይ መረጃ እንዲሰጡኝ የተመረጡ የቆላ ኑረና ቀበሌ የሽክላ ባለሙያዎች በቀጠሩኝ እለት ወደ ቦታው ስሄድ የባለሙያዎቹ ዘመድ የሆኑ አንድ ሽማግሌ ሞተው ስለነበረ ለቅሶ ላይ በመሆናቸውና በማግስቱም ሀዘን ላይ እንደሚቀመጡ በመገንዘብ መረጃውን ማግኘት እንደማልችል ተረዳሁ፡፡ ለቅሶው ላይ ውዬና ተሰናብቼ ተመለስኩ፡፡ ለቅሶው ካለፈ አንድ ሳምንት በኋላ ወደ ባለሙያዎቹ ቤት አቀናሁና ቀጠሮ ይዤ ተመለስኩ፡፡ በቀጠሮው ቀን ባለሙያዎቹ ወደሚሰሩበት ቦታ ላይ በመሄድ ተፈላጊውን መረጃ ለመሰብሰብ ችያለሁ፡፡

## 1.9. የጥናቱ አደረጃጀት

ይህ ጥናት በአምስት ምዕራፎች ተሰናድቶ የቀረበ ነው፡፡ በቀዳሚው ምዕራፍ ውስጥ የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት፣የጥናቱ ዓላማዎች፣የጥናቱ የምርምር ጥያቄዎች፣የጥናቱ ጠቀሜታ፣ የጥናቱ ወሰን፣ የጥናቱ ዘዴ፣ የመስክ ቆይታ፣ እንደዚሁም ያጋጠሙ ችግሮችና የተወሰዱ የመፍትሄ ሃሳቦችን አቅፎ የያዘ ክፍል ነው፡፡

በሁለተኛው ምዕራፍ ከሸክላና አንጥረኝነት ስራ ጋር ቅርበት ያላቸው ለአርትስ ማስተር ዲግሪ ማሟያ የቀረቡ ጥናቶች ቅኝት የተደረጉበት እና ንድፈሃሳቦች የተመረመሩበት ክፍል ነው፡፡ የቁሳዊ ባህል ምንነት፣ አመዳደብ፣መተንተኛ ሞዴሎችና ሂደቶች ተያይዘው ቀርበዋል፡፡

በሦስተኛው ምዕራፍ ጥናቱ ስለተከናወነበት ማህበረሰብ መልካምድራዊ ገፅታ፣ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ዳራ ማስተዋወቂያ የተደረገበት ክፍል ነው፡፡ በምዕራፍ አራት ውስጥ ደግሞ ጥናቱ በተከናወነበት አካባቢ የሚኖሩ በሸክላና አንጥረኛ ባለሙያዎች የሚሰሩ ቁሶች አሰራር፣አገልግሎትና የማህበረሰቡ የህይወት ፍልስፍና እንዲሁም ቁሶቹ የሚያልፉት ደረጃና ያታዊ ተሳትፎ ትንታኔ የተሰጠበት ክፍል ነው፡፡ በመጨረሻው ምዕራፍ ማጠቃለያና የይሁንታ ሃሳቦች የቀረቡ ሲሆን ዋቢ ጽሑፎችና አባሪዎችም ተያይዘው ቀርበዋል፡፡

# 2. ክለሳ ድርሳናት

በዚህ ምዕራፍ ውስጥ የንድፈ ሃሳባዊ መሰረት ምርምር የተደረገበትና ከጥናቴ ርዕሰ ጉዳይ ጋር ተያያዥነት ያላቸው ጥናቶች የተዳሰሱበት ነው፡፡

## 2.1. የንድፈ ሃሳባዊ መሰረት

ይህ ክፍል የሚያተኩረው ስለ ቁሳዊ ባህል/Material culture/ ምንነት፣የቁሳዊ ባህል ዘውጎችና ቁሳዊ ባህል የመጠናት ፋይዳ ላይ ነው፡፡ የቁሳዊ ባህል አመዳደብ፣ የመተንተኛ ሞዴሎቹና የአተናተን ሂደቱ ሌላኛው የትኩረት ክፍል ነው፡፡

### 2.1.1.የቁሳዊ ባህል ምንነት

የቁሳዊ ባህል ምንነትን አስመልክቶ የፎክሎርና የስነሰብእ ሊቃውንት የተለያየ አስተሳሰብ ያራምዳሉ፡፡ የፎክሎር ሊቃውንት ቁሳዊ ባህል የሚባለው የቁሶቹን ጥርቅም ብቻ ሳይሆን በቁሶቹ አማካኝነት የማህበረሰቡን አስተሳሰብና ማንነት የሚጠናበት ነው ይላሉ፡፡ የዚህ ሃሳብ አቀንቃኝ ሊቃውንት ያቀረቡት ሃሳብ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

Dorson(1972፣2) "ቁሳዊ ባህል የዘመን አሻራን የሚጠቁሙ፣ ራሳቸው ሰዎች አብጅተዋቸው ለኑሯቸው፣ለጌጣጌጣቸው፣ለመዝናኛቸው የሚገለገሉባቸውና ህይወታቸውን ለመጠበቅ የሚውሉ መሳሪያዎችን የሚያካትት" መሆኑን ገልፀዋል፡፡ ከዚህ የምንረዳው ሃሳብ ቁሶች በተለያየ ዘመናት ውስጥ የነበሩ የማህበረሰብ ክፍሎች ማህበራዊ፣ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ደረጃቸው ምን እንደሚመስል የሚገልፅ መሆኑን ነው፡፡ የተለያዩ ቁሶችን ሰርተው የእለት ከእለት ተግባራቸውን መከወኛነት፣ለማስዋቢያና መንፈሳቸውን ለማደሻነት እንደሚያውሏቸው የሚያስገነዝብ ነው፡፡ በሌላ መልኩ ህይወታቸውን ከሚጎዱ እንስሳትም ይሁኑ ሰዎች ራሳቸውን የሚከላከሉበትን ቁሳቁስ አቅፎ የያዘ መሆኑን የሚያመለክት ነው፡፡

Prown (1982፣1 ) «Material culture is study of through artifacts of the beliefs, values, ideas, attitudes and assumption of a particular community or society at a given time.» ይላል፡፡ ቁሳዊ ባህል የትኩረት አቅጣጫው በቁሶቹ አማካኝነት ቁሶቹ ስለበቀሉበት የማህበረሰብ ክፍል እምነት፣አስተሳሰብ፣እሴት፣አመለካከትና መላምታቸውን የሚመረመርበት መሆኑን የሚጠቁም ነው፡፡

Wood (2007፣14) «Material culture have as their primary concern the mutual relations between people and objects.In particular,studies of material culture are concerned with what uses people put objects to and what objcets do for,and to,people» ይላል፡፡ ከዚህ ሃሳብ የምንረዳው ቁሳዊ ባህል ተቀዳሚው ትኩረቱ በማህበረሰቡና በቁሱ መካከል ያለውን የጋራ ግንኙነት መመርመር ነው፡፡ ማህበረሰቦቹ ቁሶቹን ለምን አገልግሎት ያስቀምጡታል? ቁሱ ለማህበረሰቡ የሚሰጠው አገልግሎት ምንድን ነው? የሚሉትን መጠይቆች የሚመረምር መሆኑን ነው፡፡

ቁሳዊ ባህል በቁሶቹና በማህበረሰቡ መካከል ያለውን ግንኙነት የሚመለከት ነው፡፡ ይህ ደግሞ ቁሶቹ የማህበረሰቡን ምን የህይወት ፍልስፍና ያሳያሉ? ቁሶቹ የበቀሉበት የማህበረሰብ ክፍሎች ለቁሱ ያላቸው አመለካከት ምን ይመስላል? ማህበረሰቡ ቁሶቹን የሚጠቀሙባቸው ከምን አስተሳሰብ የመነጨ ነው? ቁሶቹ ከእለት ግልጋሎት ባሻገር ምን የሚያመለክቱት ነገር አለ? ቁሶቹ በማህበረሰቡ ውስጥ ምን ትዕምርትን ይወክላሉ? ቁሶቹ የያዙትን ቅርፅ እንዴት ሊይዙ ቻሉ? የሚሉትን መጠይቆች እንድናነሳን ያስችለናል፡፡

የመጠይቆቹን ምላሽ ስንመረምር ደግሞ ቁሶቹ የበቀሉበትን የማህበረሰብ ክፍል አመጋገብን፣ሰርካዊ ኑሯቸውን፣መልካምድራዊ ገፅታውን፣እምነታቸውን፣ አስተሳሰባቸውንና መሰል ጉዳዮችን እንድንገነዘብ መንገዱን ያመቻችልናል፡፡

Glassie( 1999፣41) «Material culture is the culture made material it is the inner wit at work in the world. Beginning necessarily with things,but not ending with them, the study of material culture uses objects to approach human thought and action.» ይላል፡፡ Glassie ካቀረበው ሃሳብ የምንረዳው ቁሳዊ ባህል ተዳሳሽ የሆኑና የሰው ልጅ ባህልን መነሻ አድርጎ የእለት ከዕለት ተግባራትን ለመከወኛነት የሚያገለግሉ ቁሶችን የሚመለከት ነው፡፡ ቁሶች የእለት ተግባራትን በመከወን ብቻ የተገደቡ አይደሉም፡፡ የቁሶቹን አገልግሎት መሸጋገሪያ በማድረግ የሰዎችን አስተሳሰብና ተግባራት ለመመርመር የሚያስችል መሆኑን የሚያስገነዝብ ነው፡፡ የቁሶቹ አሰራር ከምን አስተሳሰብ የመነጨ ነው? የቁሶቹ ተጠቃሚዎች ከምን እሳቤ በመነሳት ግልጋሎት ላይ ሊያውሏቸው ቻሉ? የቁሶቹ ተግባርና አሰራር ምን የህይወት ፍልስፍና ያሳያሉ? የሚሉትን መጠይቆች በማንሳትና በመመርመር በቁሶቹ አማካኝነት የሰዎችን አስተሳሰብና ድርጊት መገንዘብ የሚያስችለን መሆኑን የሚጠቁም ነው፡፡

ፈቃደ (1991፣15)‹‹ቁሳዊ ባህል››በአይን የሚታየውን በእጅ የሚዳሰሰውን፣ ከዘመናዊ ኢንድስትሪ በፊት ጀምሮ የሰው ልጅ ፈጥሮ የተገለገለባቸውን ቁሳቁሶች፣እነዚህ ቁሳቁሶች

የተሰሩበትን ዘዴ ወይም ቴክኒክ የልዩ ልዩ ምግቦችን አሰራር፣የቅመም አቀማመም ብልሃትን ፣የልብስ፣የቤት፣የአጥር ወዘተ አሰራርን ፤ሰዎች ልዩ ልዩ ስራዎችን የሚያከናውኑባቸውን መሳሪያዎችንና ሌሎች ተመሳሳይ ጉዳዮችን ያጠናል ማለት ነው፡፡ እቃውን እራሱን ማጥናት አንድ ዋና ተግባር ሲሆን አሰራሩን ማጥናት ደግሞ ሌላው ነው ማለት ነው፡፡ ይላል፡፡

ፈቃደ ካቀረበው ሃሳብ የምንረዳው ቁሳዊ ባህል የሚዳሰሱና የሚጨበጡ መሆናቸውን ነው፡፡ ቁሶቹ ከምንና እንደምን ባለ ብልሃት ይሰራሉ? ቁሶቹ የያዙት ቅርፅ እንዴት ሊይዙ ቻሉ?የቁሶቹ አሰራር ከምን አስተሳሰብ ፈለቀ? የሚሉት ጥያቄዎችን ለመመርመር የሚያስችል ነው፡፡ በቁሶቹ አሰራርና አገልግሎት መነሻነት የሰዎችን አስተሳሰብ የሚመረመርበት መሆኑን የሚጠቁም ነው፡፡

ከቁሶቹ አሰራርና አገልግሎት ውስጥ ተፈልቅቀው የሚወጡ አስተሳሰቦችን በመመርመር ቁሶቹ የበቀሉበትን የማህበረሰብ ክፍሎች ያላቸውን አስተሳሰብ፣እምነት፣ማህበራዊ ደረጃና እርስ በርሳቸው ያላቸውን ማህበራዊ ግንኙነት እንዲሁም የህይወት ፍልስፍናቸው ምን እንደሚመስል እንድንገነዘብ የሚያስችለን መሆኑን የሚያመለክት ነው፡፡

ሁለተኛው ጎራ ደግሞ ቁሳዊ ባህል የምንለው የእለት ከእለት ተግባራትን ለመከወን የሚያስችሉ የቁሶች ስብስብ መሆኑን የሚገልፁ ናቸው፡፡

Cleary /2004፤2/‹‹ The Term material culture represents the ‹‹thing›› or the “stuff” Which we create and use on daily basis.›› ነው ይላል፡፡ ይህ ሃሳብ የሚስረዳው ቁሳ ባህል የሚለው ስያሜ ውክልናው ለቁሶች ስብስብ የቆመ መሆኑን ነው፡፡ ቁሶቹ በእኛው ተበጅተውና የእለት ከእለት ተግባራትን መከወኛነት የሚውሉ ናቸው የሚል ነው፡፡ ቁሳዊ ባህል የእለት ከእለት አገልግሎት ለመከወኛነት የሚውሉና የቁሶችን ስብስብ የሚገልፁ ቢሆኑም ከቁሶቹ አገልግሎት ጀርባ ያለውን ትዕምርት የሚፈትሽ መሆን አለበት፡፡ ይህ ማለት ግን ቁሳዊ ባህል ስለቁሶቹ አገልግሎትና አሰራር አያነሳም ማለት አይደለም፡፡ የቁሶቹ አሰራርና አገልግሎት መነሻ በማድረግ ቁሶቹ የበቀሉበትን የማህበረሰብ ክፍሎች ምን የህይወት ፍልስፍና ያሳያሉ? የቁሶቹ አሰራር ከምን ፍልስፋና የመነጩ ናቸው? የቁሱ ተጠቃሚዎች ቁሱን የሚጠቀሙት ከምን አስተሳሰብ በመነሳት ነው? ቁሶቹ አሁን የያዙትን ቅርፅ እንዴት ሊይዙ ቻሉ?የሚሉትን መጠይቆችን የሚመረምር መሆን አለበት፡፡

ከእኔ ጥናት ዓላማ ጋር የጠበቀ ትስስር ያለው ቁሳዊ ባህል የቁሶች ስብስብ ብቻ ሳይሆን በቁሶቹ አማካኝነት የማህበረሰቡን አስተሳሰብ፣ባህልና ማንነት ይገልፃል በሚለው ሃሳብ ላይ

ነው፡፡ ከስያሜው መረዳት እንደሚቻለው ቀሳዊ ባህል የሁለት ቃላት ጥምርታ መሆኑን ነው፡፡ እነሱም፡-ቁስና ባህልን የሚሉት ናቸው፡፡ ቁስ የምንለው የተለያየ መጠንና ቅርፅ ያለው የቁስ ስብስብ ሲሆን የእለት ከእለት ተግባራትን ለማከናወኛነት የሚያገለል ነው፡፡ ባህል የምንለው ደግሞ የአንድን ማህበረሰብ ማንነት የሚያሳይ ነው፡፡

## 2.1.2. የቁሳዊ ባህል ዘውጎች

Dorson [1972፣2] በቁሳዊ ባህል ስር የሚካተቱት ሀገረሰባዊ እጅ ሥራ/ folk crafts/ ሀገረሰባዊ ሥንክን/folk art/ ሀገረሰባዊ ምህንድስና /folk architecture/ ሀገረሰባዊ ልብስ /folk costume/ እና ሀገረሰባዊ የምግብ አሰራር /folk cookery/ በሚል ከፍሏቸዋል፡፡

የእኔ ጥናት ትኩረት በቁሳዊ ባህል ስር ከሚጠኑት መካከል ሀገረሰባዊ እጅ ስራ ላይ ያነጣጠረ በመሆኑ ርዕሰ ጉዳዩን ወደ ማብራራቱ አቀናለሁ፡፡

### ሀገረሰባዊ እጅ ሥራ/ folk crafts/

ሀገረሰባዊ እጅ ሥራ ከቁሳዊ ባህል ዘውግ ውስጥ አንዱ ነው፡፡ ከስያሜው እንደምንረዳው ሀገረሰባዊ የሚለው ሀገር በቀልነትን /አካባቢያዊነትን/ ሲያመላክት የእጅ ስራ የሚለው ደግሞ በእጅ የሚሰራ ቁስን የሚመለከት ነው፡፡

Roberts ውስተDorson (1972፣233) ማህበረሰብ በቀያቸው /በአቅራቢያቸው/ የሚያገኙትን የተለያዩ ጥሬ እቃዎችንና ሀገር በቀል እውቀትን ተጠቅመው በእጃቸው የሚሰሩትን ቁስ የሚመለከት ነው፡፡ ቁሱ የእለት ከእለት ተግባራትን ለመከወኛነት ይውላል በማለት ገልፀዋል፡፡

ባለሙያዎቹ በአቅራቢያቸው የሚያገኙትን ጥሬ እቃዎች በመጠቀም የተለያዩ ቁሶችን በእጃቸው ሲሰሩ ኖረዋል፡፡ በአሁኑ ወቅትም ባህር ተሻግረውና ሀገር አቋርጠው በመጡ ዘመነኛ ቁሶች ቢወረሩም እየተሰሩ ነው፡፡ ሀገር በቀል ቁሶች ለማህበረሰቡ ብዙ ጥቅም ይሰጣሉ፡፡ ሀገረ ሰባዊ እጅ ሥራ ኢመደበኛ እውቀትን መሰረት በማድረግ የማህበረሰቡን የአኗኗር ዘይቤ፣ታሪክ፣ አስተሳሰብ፣ወግና ፍልስፋና የሚገለፅበት ነው፡፡

### 2.1.3. የቁሳዊ ባህል ጥናት ፋይዳ

የሰው ልጅ የህይወት ውጣ ውረዱን ለመግፋት የሚያስችሉ ቁሶችን ሲሰሩ ብዙ ዘመናትን አስቆጥረዋል፡፡ በአሁኑ ወቅት የክስታኔ ማህበረሰብ በኢንዱስትሪ አብዮት ቁሶች ቢጥለቀለቁም ባለሙያዎቹ ግን ቁሶቹን መስራት አላቋረጡም፡፡ በሸክላና አንጥረኛ ባለሙያዎች የሚሰሩ ቁሶች ዘርፈ ብዙ ተግባራትን ለመከወኛነት ከማገልገላቸውም በላይ የዘመን ጥበብ አሻራ ያረፈባቸው ናቸው፡፡ በተለያየ መጠንና ቅርፅ የተሰሩ ቁሶች የማህበረሰብ ባህል፣ፍልስፍና እና እሴትን በመግለፅ በኩል አበርክቶ ስላላቸው ቢጠኑ ጥሩ ነው፡፡

የቁሳዊ ባህል ጥናት አስፈላጊነት በተመለከተ Prown እና Mayo እንደሚከተለው ገልፀውታል፡፡ Prown [1982፣3] «Inherent and Attached value. The most obvious culture belief associated with material objects has to do with value.» ይላል፡፡ ከዚህ የምንረዳው ሃሳብ ቁሶች ከእለት እለት ግልጋሎት ባሻገር የተለየ እሴት የሚገለፅባቸው መሆናቸውን የሚያስገነዝብ ነው፡፡ እሴቶቹም ተፈጥሯዊ ወይም ሰዎች የሚያበጁቸው ሊሆኑ ይችላሉ፡፡

በማስከተልም Prown ‹‹Surviving Historical events. Objects created in the past are the only Historical occurrences that continue to exist in the present.››[1982፣3] የሚለውን ሃሳብ አቅርቧል፡፡ ከዚህ የምንገነዘበው ሃሳብ ቁሶች ስላልኖርንበት ዘመን የተከናወነን ድርጊት ታሪክን እየነቀሱ በውል እንድንገነዘብ የሚያስችሉ መሆናቸውን የሚጠቁሙ መሆናቸውን የሚያመለክት ነው፡፡

‹‹More Representative. They offer the possibility of a way to understand the mind of the great majority of non literate people,past and present,Who remain otherwise in accessible except through impersonal records and the distorting view of a contemporary literary elite.›› [1982 3] ቁሳዊ ባህል የተማሩ የማህበረሰብ ክፍሎች ይሁኑ ያልተማሩ የማህበረሰብ ክፍሎች በቁሶቹ አማካኝነት አስተሳሰባቸውን፣ባህላቸውን፣ እምነታቸውን እንዲሁም ማህበራዊ ደረጃቸውን የሚገልፁበት መሆኑን የሚያመለክት ነው፡፡

በመጨረሻም Prown ‹‹The fundamental purpose of the study of material culture is the quest for cultural belief systems, the patternts of belief of a particular group of people in acertain time and place.›› [1982፣6] ይላል፡፡

ከዚህ የምንገነዘበው ሃሳብ የቁሳዊ ባህል መሰረታዊ ግቡ በባህል ውስጥ ያሉ እምነቶችን መፈለግ፣በአንድ ቦታና ጊዜ ውስጥ የነበረን እምነት፣ባህል፣ታሪክ፣የአኗኗር ሁኔታን እንዲሁም አስተሳሰባቸውን መመርመር መሆኑን ያስገነዝበናል፡፡

እንደMayo[1984፣ 3] አገላለፅ ደግሞ‹‹Artifacts are symbols and can explain much about society,religiousbeliefs,forms of government, manual dexterity, level of intelligence,artistic comprehension, available natural materials,structure of commerce,and scientific and emotional sophistication of the producing society.›› ነው፡፡ ከዚህ ሃሳብ የምንገነዘበው ቁሶች ትዕምርት ያላቸውና የአንድን ማህበረሰብ ሀይማኖታዊ እምነቶች፣አስተዳደራዊ መዋቅር፣የእውቀትን ደረጃና የአምራቹን ማህበረሰብ ሳይንሳዊና ስሜታዊ ሁነቶችን መግለፅ የሚችል መሆኑን የሚጠቁም ነው፡፡ ቁሶቹ ከእለት ተግባራት መከወኛነት ባሻገር የበቀሉበትን የማህበረሰብ ክፍል ባህል፣ማህበራዊ ደረጃ፣አስተሳሰብና የህይወት ፍልስፋና ጭምር እንደሚያሳዩ የሚገልፅ ነው፡፡

Glassie ውስተ Dorson [1983፣380] እና [1999፣42] በአንድ ማህበረሰብ ውስጥ የሚገኙ ቁሶችን ለማጥናትና ለመፈከር ስናስብ ቁሶቹን ያበጁ ባለሙዎችን በጥምረት መመርመር እንደሚገባቸው፣ቃላዊ ይሁን ቁሳዊ የፈጠራው ጥበቡ በባለሙያዎቹ አዕምሮ ውስጥ ተሸሽገው ስለሚገኙ ድብቁን ነገር መመርመር ጠቀሜታ አለው ይላል፡፡

ከላይ ከቀረበው ሃሳብ የምንረዳው ቁሶቹን ለማጥናት ቁሶቹንና ያበጃቸውን የማህበረሰብ ክፍል በውህደት መመርመር አስፈላጊ መሆኑን ነው፡፡ ቁሶቹን የሰሯቸውን ባለሙያዎች ማጥናት ያስፈለገበት ምክንያት በአዕምሯቸው ውስጥ ያለውን አስተሳሰብ ለመመርመር ስለሚያስችል ነው፡፡ ቁሶቹን የሚሰሩት ከምን መነሻ አስተሳሰብ ነው? ምን የህይወት ፍልስፍና እንዲያንፀባርቁ አስበው ነው? ቁሶቹ እንዴት አሁን የያዙትን ቅርፅ እንዲይዙ አድርገው ሰሯቸው? በቁሶቹ ስራ ላይ የፆታ ክፍፍል ለምን አስፈለገ? የሚሉትን ጥያቄዎች እንድንመረምርና ምላሽ እንድናገኝ የሚያንደረድር መሆኑን የሚጠቁም ነው፡፡

## 2.1.4. ቁሳዊ ባህልን የመመደቢያ መስፈርቶች

በተለያየ መጠንና ቅርፅ የተሰሩ ቁሶችን በየፈርጃቸው ማደራጀት ጠቀሜታ አለው፡፡ የቁሶቹ ምደባ አስፈላጊነት ስለቁሶቹ በጥልቀትና ባልተወሳሰበ መልኩ ለመመርመር የሚያስችል በመሆኑ ነው፡፡

እንደ Marches አገላለፅ "classification is the means by which artifactual materialis categorized and subject to manipulation" ነው [1984፣ 15] ይላል። ከዚህ የምንረዳው ምደባ ቁሳዊ ባህልን /በእጅ የተሰሩ ቁሶችን/ለመክፈል እንደ መሳሪያ የሚያገለግል መሆኑን ነው። ቁሶቹ የያዙትን ቅርፅ ለምን እንደያዙ? ምን የህይወት ገፅታ እንደሚያሳዩ? የቁሶቹ ተጠቃሚዎች ከምን አስተሳሰብ ተነስተው ቁሶቹን እንደሚገለገሉባቸው? በቁሶቹ ስራ ላይ ለምን የዖታ ክፍፍል እንዳለ ለመመርመር ምደባ ፋይዳ አለው። ቁሳዊ ባህልን የተለያዩ መስፈርቶችን በመጠቀም መመደብ እንደሚቻል ከሚገልፁ ምሁራን መካከል prown እና Ames ተጠቃሽ ናቸው።

Prown[1982፣2 ] ቁሳዊ ባህልን መመደብ አስቸጋሪ መሆኑን ጠቁሟል። ምደባውን ለመከወን መሰናክል እንዲኖር ያደረጉት የሚከተሉት ምክንያቶች እንደሆኑ ገልጿል። እነሱም:-ቁሶቹ በአይነትም ሆነ በቁጥር በርካታ መሆናቸው፣ ቁሳዊ ባህልን ለመመደብ የሚያስችል ምልዑነትን የተጎናፀፈ እና አንድ ወጥ መስፈርት አለመኖሩን ጠቅሷል። ለቁሳዊ ባህል ምደባ እንቅፋት የሆኑትን ምክንያቶችን ያንሳ እንጂ ይበጃሉ ያላቸውን የቁሳዊ ባህል መመደቢያ መስፈርቶች ሳይገልፅ አላለፈም። መስፈርቶቹም:-ቁሱ ከሚሰራበት ንጥረ ቁስ ፣ከአሰራር ጥበብና አገልግሎት አንፃር በመመደብ ማጥናት እንደሚቻል ጠቁሟል። የገለፃቸው መስፈርቶች ግን ምልዑነትን የተካኑ አለመሆናቸውን አያይዞ ጠቁሟል።

መስፈርቱ ሰንካላ የሆነበትን ምክንያት ቁሱ የተሰራበትን ንጥረ ቁስ የመመደቢያ መስፈርት ሲደረግ ቁሶቹ ከአንድ በላይ በሆነ ንጥረ ቁስ ሊሰራ ስለሚችል ለምደባ ያስቸግራል። ያቀረበውን ሃሳብ ግልፅ ለማድረግ አንድ ምሳሌ ላንሳ ማጭድ በአንጥረኛ ባለሙያዎች የሚሰራ ቁስ ሲሆን ባለሙያዎቹ እጀታውን ከእንጨት ቀሪውን ክፍል ደግሞ ከብረት በማጣመር ማጭድ ያበጃሉ። ማጭድ የእንጨትና ብረት ድምር ውጤት በመሆኑ ከተሰራበት ንጥረ ቁስ አንፃር ለመመደብ አስቸጋሪ ነው።

የቁሶቹን የአሰራር ጥበብ ደግሞ በመስፈርትነት ሲያገለግል ቁሱን የሚሰሩት ባለሙያዎች የግል ችሎታቸው የተለያየ መሆኑና የአሰራር ሂደቱ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተለወጠ የመጣና የሚሄድ በመሆኑ ቁሶቹን በአሰራር ጥበብ መመደብ አዳጋች ይሆናል። ቁሳዊ ባህልን ለመመደብ አገልግሎት የተሻለ መሆኑን አመላክቷል። አገልግሎትን የተሻለ መስፈርት በማለት መግለፁ ቁሶቹ ከተሰሩበት ንጥረ ቁስና የአሰራር ጥበባቸውን መስፈርት አድርጎ ከመጠቀም ይሻላል ማለቱ መሆኑን ከገለፃው መረዳት ይቻላል።

በሌላ በኩል ቁሳዊ ባህልን በቁሶቹ አገልግሎት መክፈል ውስንነት ያለበት መሆኑን ምክንያታዊነቱን ጭምር የሚገልፁ ምሁራን አሉ። ከነዚህ መካከል Somjee[1993፣ 86] ቁሶችን የሚጠቀሙ የማህበረሰብ ክፍል ከጊዜ ጊዜ እንደሚለዋወጡና ከቁሱ ፍይዳ አንፃር አገልግሎቱም እንደሚቀያየር ገልፀዋል። ከዚህ የምንረዳው ቁሶቹን ድሮ ይጠቀም የነበረ የማህበረሰብ ክፍል በአሁኑ ወቅት ላይጠቀሙ መቻላቸውን ነው። ቁሱን የማይጠቀሙበት ምክንያት ባህር ተሻጋሪ ቁሶች በየቤታቸው ውስጥ የሚገቡ ከሆነ ወይም ቁሶቹ ይሰጡት የነበረውን አገልግሎት ሲያቋርጡ የማይጠቀሙበት ሁኔታ ሊፈጠር ይችላል።

Beals and Harry [1958፣238] አንድ ቁስ ዘርፈ ብዙ ግልጋሎት"multi functional objects" እንዳለው ጠቁመዋል። ከዚህ የምንረዳው ሃሳብ አንድ ቁስ በአንድ ተግባር ላይ ብቻ አለመወሰኑን የሚያሳይ ነው። አንድ ቁስ በአንድ ተግባር ላይ ብቻ ከመወሰን ይልቅ የተለያዩ ተግባራትን ለመከወኛነት የሚያስችል መሆኑን የሚያስገነዝብ ነው። ምሳሌ የሸክላ ቁስ የሆነው ጀበና ተቀዳሚው ተግባር ለቡና ማፍሊያነት ነው። ጀበና ከቡና ማፍሊያነት ውጪ ቤት ውስጥ በመስቀል/በማንጠልጠል/ ለጌጥ የሚሆንበት አጋጣሚ ስላለ ነው።

Ames[1978-20]‹‹Clasifications based on Forms, function, material, date, school or maker or style are frequently employed.More subtle models may in corporate several of these factors.›› ቁሳዊ ባህልን ለመመደብ ቅርፅ፣አገልግሎት፣ቁሱ የተሰራበት ዘመን፣ለቁሱ መስሪያ የሚያገለግል ጥሬ እቃና የአሰራር ጥበብን መነሻ በማድረግ መከፋፈል/መመደብ/ እንደሚቻል ጠቁሟል። የቁሳዊ ባህል መመደቢያ መስፈርቶችን ቢገልፅም የተሻለው የምደባ መስፈርት ግን የተጠቀሱትን መስፈርቶች አዋህዶ መጠቀም ተመራጭ መሆኑን ሳይጠቁም አላለፈም።

የተለያዩ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎችን ተጠቅሜ ከምንጩ የሰበሰብኩትን መረጃ አንድ ወጥ መስፈርት እስከሚገኝ ድረስ prownእና Ames ከዘረዘሩት የመመደቢያ መስፈርት ውስጥ የቁሶቹን ተቀዳሚ አገልግሎት መነሻ በማድረግ ለመመደብ ሞክሪያለሁ።

## 2.1.5. የቁሳዊ ባህል መተንተኛ ሞዴሎች

Schlereth ውስተ ኢንተርኔት[7-8] ለቁሳዊ ባህል ጥናት ይበጃሉ ያላቸውን ዘጠኝ የመተንተኛ ሞዴሎችን ዘርዝሯል። ሞዴሎቹን በተናጠል ከመጠቀም ይልቅ በውህደት መጠቀሙ ተመራጭ መሆኑን አክሎ ጠቅሷል። እኔም ሞዴሎቹን እንደ አስፈላጊነታቸው በውህደት ተጠቅሜያለሁ።

**ታሪካዊ ጥበብ አመልካች** /Art Historical/ -evaluation of art by material cultural means. **ይህ የሞዴል አይነት ባህላዊ ቁሶችን ስናጠና የእለት ከእለት ግልጋሎታቸው ላይ ማተኮር ሳይሆን በቁሶቹ ላይ የተረጨውን ጥበባዊ ውበት የምናመለክትበት ነው፡፡ ውበታዊ ዋጋቸው ጎልቶ እንዲወጣ የቁሶቹን ቅርፅ፣ቀለም፣ስስነትና ጥንካሬን በአግባቡ በመግለፅ ታሪካዊ ጥበብ አመልካችነታቸውን ፍንትው አድርጎ መግለፅ ይገባል፡፡**

**ትዕምርታዊነቱ** /symbolic/ The role held by an object in society. **ቁሶች ከዘወትራዊ ፍይዳቸው ባሻገር የማንነት መታወቂያ በመሆን ያገለግላሉ፡፡ ለምሳሌ አንዳንድ ቁሶች በማህበረሰቡ ውስጥ አዳኝነትን፣ባለሙያነትንና ሀብታምነትን የሚገልፁበት ሁኔታ አለ፡፡ በቁሳዊ ባህል ጥናት ውስጥ ከቁሶቹ ግልጋሎት ጀርባ ያለውን ጥበብ ፈልቅቆ መመርመር እንደሚገባ የሚያስገነዝብ ነው፡፡ ቁሶቹ የያዙት ቅርፅ ትዕምርቱ ምንድን ነው? ቁሶቹ ምን የህይወት ፍልስፍና ያሳያሉ? የሚሉትን ጥያቄዎች ለመመለስ የሚያስችል ነው፡፡**

**ባህላዊነቱ** /cultural/ The development of characteristics of an object which can be related to particular cultures. **በቁሶቹና በማህበረሰቡ ባህል መካከል ያለውን ተዛምዶ የሚመረምር ሲሆን የሚከተሉትን ጥያቄዎች ያነሳል፡፡ ቁሶቹ የአንድን ማህበረሰብ የትኛውን የባህል አይነት ይወክላል? ቁሶቹ የየትኛውን የማህበረሰብ ክፍል ባህል ይገልፃሉ? የሚሉት ጥያቄዎች ለመመርመር የሚያስችል የሞዴል አይነት ነው፡፡**

**አካባቢያዊነት**/Environmental/The role of the physical environment on object. **የአንድ አካባቢ ምልክአ ምድራዊ ገፅታና ማህበረሰቡ በቁሱ ላይ መልካምና መጥፎ ነገር የሚፈጥርበት መንገድ አለ ወይ? ቁሱ የተበጀበትን አካባቢ የሚያመለክትበት ሁኔታ ምን ይመስላል ?የሚሉት ጥያቄዎች የሚቃኙበት ሞዴል ነው፡፡**

**አገልግሎቱ /**Function / The way an object is used.**ቁሶቹ ምን ምን ተግባራትን ለመከወኛነት ይውላሉ? ቁሶቹ በምን መልኩ አገልግሎት ይሰጣሉ? የቁሶቹ ተጠቃሚዎች ከምን አስተሳሰብ በመነሳት ይገለገሉባቸዋል? የቁሶቹ አገልግሎት የማህበረሰቡን የህይወት ፍልስፋና በምን መልኩ ያሳያሉ? የሚሉ ጥያቄዎችን እያነሳን እንድንመረምር የሚያስችል ሞዴል ነው፡፡**

**መዋቅራዊነቱ** /structural / How an object was physically made. **ቁሶቹ የቁስነት ደረጃ የሚይዙበትን ውቅር የሚያሳይ ነው፡፡ ቁሶቹ ከምን ከምን ጥሬ እቃዎች ተሰሩ? ቁሶቹን ለመስራት ጥቅም ላይ የዋሉት ምን ምን ናቸው? የአሰራር ሂደቱ እንዴት ነው? የሚሉትን ጥያቄዎች በማንሳት ምላሽ ለመስጠት የሚያስችል የሞዴል አይነት ነው፡፡**

**ባህርይ ጠቋሚነት** /behavioral/ The interaction of object and behavior patterns of society.**ማህበረሰቡ ቁሱን በምን መልኩ ይረደዋል? በቁሱና በማህበረሰቡ መካከል ምን ባህርያዊ ግንኙነት አለ? የቁሱ አገልግሎት በማህበረሰቡ ዘንድ ምን ተፅዋ አሳደረ? ቁሶቹ የማህበረሰቡን አስተሳሰብ የለወጡበት ሁኔታ አለ ወይ? ለሚሉት ጥያቄዎች ምላሽ ለማግኘት የሚያንደረድር ሞዴል ነው፡፡**

**ማህበራዊነቱ** /community/ The interaction of object and society which form /reflects a common view point/ character.**ቁሶቹ ከማህበረሰቡ ጋር ያላቸውን ትስስርና ቁርኝት የሚቃኝ ነው፡፡ ቁሶቹ የማህበረሰቡን የህይወት ገፅታ በምን መልኩ ያሳያሉ? የቁሶቹ ተጠቃሚዎች ቁሶቹን ከምን አስተሳሰብ በመነሳት ይገለገሉባቸዋል? ማህበረሰቡ ለቁሶቹ ያላቸው እይታ ምን ይመስላል? የሚሉትን ጥያቄዎች የሚመረመርበት ነው፡፡**

**የማህበረሰብ ታሪክ ገላጭነት** /social History/ The story of the object or its provenance.**ቁሶቹ የማህበረሰቡን ታሪክ በምን መልኩ ገለፁ/ይገልፁታል/? ቁሶቹን ማን አበጃቸው? ከየትኛው የማህበረሰብ ክፍል ተገኙ? በየትኛው ዘመን ፈለቁ? ለሚሉት ጥያቄዎች ምላሽ ለመስጠት የሚያስችል የሞዴል አይነት ነው፡፡**

### 2.1.6. Prown **ያቀረባቸው የቁሳዊ ባህል መተንተኛዎች**

Prown/1982፣7-10/**ቁሳዊ ባህልን ለመተንተን ያስችላሉ ያላቸውን ሶስት ሂደቶች ዘርዝሯል፡፡ እነሱም፡-ገላጭ**/Description/፣**ትርጓሜ**/Deduction/ **አመላካች**/speculation/**የሚሉት ናቸው፡፡**

#### **ሀ. ገላጭ** /Description/

‹‹Description is restricted to what can be observed in the object it self,that is to internal evidence››. **በቁሳዊ ባህል ትንተና ወቅት መጀመሪያ ላይ የሚቀመጥ ሂደት ነው፡፡ ቁሱን በእውን አይን በመመልከት ገለፃ የሚደረግበት ደረጃ ነው፡፡ ገለፃው መነሻ የሚያደርገው የቁሱ ቅርፅ፣ የተሰራበት ጥሬ እቃዎች፣ ውፍረትና ቀለምን ነው፡፡**

#### **ለ. ትርጓሜ** /Deduction/

‹‹Deduction The second stage of analysis moves from the object it self to the relation ship between the object and perceiver.›› **በቁሱና በማህበረሰቡ መካከል ያለውን መስተጋብር ጥልቀት ባለው መልኩ በመመርመር ትርጓሜ ለመስጠት የሚያስችል ሂደት ነው፡፡ ቁሶች**

የበቀሉበትን የማህበረሰብ ክፍል የህይወት ፍልስፍና በምን መልኩ ያሳያሉ? የቁሶቹ ተጠቃሚዎች ቁሶቹን የሚገለገሉባቸው ከምን አስተሳሰብ በመነሳት ነው? ባለሙያዎቹ ቁሶቹን ሲሰሩ መነሻ የሚያደርጉት ቅርፅ ምንድን ነው? ባለሙያዎቹ ቁሶቹን ሲሰሩ ምን የህይወት ገፅታ እንዲያሳዩ አስበው ነው? የቁሶቹ ተጠቃሚዎች ለቁሶቹ ያላቸው አመለካከት ምን ይመስላል? ለሚሉት ጥያቄዎች ምላሽ ለመስጠት የሚያስችል ነው፡፡

### ሐ.አመላካች/Speculation/

‹‹Speculation having progressed from the object it self in description to the interaction between object and perceiver in deduction,the analysis now moves completely to the mind of the perceiver, to speculation there are few rules or proscriptions at this stage››. **ይላል፡፡** አመላካች በቁሳዊ ባህል ሂደት ውስጥ በሶስተኛ ደረጃ ላይ የሚገኝ ነው፡፡ በገላጭ የቁሳዊ ባህል ትንተና ሂደት ውስጥ ቁሱን በእውን አይን ውጫዊ ገፅታውን መቃኘት ላይ ትኩረት ያደርጋል፡፡ በትርጓሜ ሂደት ውስጥ ደግሞ በቁሱና በማህበረሰቡ መካከል ያለውን መስተጋብር መነሻ በማድረግ ወደ ተቀባዩ አዕምሮ በቀጥታ የሚሄደውን የሚመለከት ነው፡፡ በአመላካች ላይ ደግሞ በገላጭና በትርጓሜ የተገኘውን መረጃ መነሻ በማድረግ ከትውሮች ጋር የሚጣቀስበትና የተወሰኑ አዳዲስ ትውሮች የሚቀመርበት ነው፡፡

## 2.1.7. Fleming ያቀረባቸው የቁሳዊ ባህል መተንተኛ ሂደቶች

በሌላ መልኩ Fleming /ውስተ ኢንተርኔት 156–161/ የቁሳዊ ባህል በሚከተሉት መንገዶች ከፋፍሎ ማጥናት እንደሚቻል ጠቁሟል፡፡ እነሱም፦የቁሱን ታሪክ/history/፣ ቁሱ/material/፣ የአሰራር ስልቱ/construction /፣ ጌጥ/ design / እና አገልግሎት/ function /ናቸው፡፡

Fleming ከላይ የጠቀሳቸውን በማሻሻል በሚከተለው መንገድ ማጥናት እንደሚቻል ጠቁሟል፡፡ እነሱም፦መለየት/Identification/፣ግምገማ/Evaluation/ባህላዊ ትንተና/Cultural analysis/ እና ፍከራ /Interpretation/ የሚሉት ናቸው፡፡

### ሀ.መለየት /Identification/

Fleming ካቀረባቸው የቁሳዊ ባህል መተንተኛዎች ውስጥ መጀመሪያ ላይ የሚገኘው መለየት ነው፡፡ በመለየት ሂደት ውስጥ ደግሞ ምደባ ቀዳሚ መሆኑን እንደሚከተለው ተገልጿል፡፡

> Identification should begin with the question, what is it? The answer is classification-specification of the general class to which the particular object

under consideration belongs. Most current systems of classification are unstematic. Many are based on function/chair,floor covering, coffeepot,firearm/ some on material/textile glass ware/ other on construction /painting,print/,or oniconography and subject matter/map/. **በሚል አቅርቧል፡፡**

**ከዚህ የምንረዳው ሃሳብ ለምደባ መነሻ የሚሆነው አብዛኛው ቁሱ በሚሰጠው አገልግሎት ላይ ሲሆን ሌላኛው ደግሞ በቁሱ ላይ ነው፡፡ የተወሰነው ደግሞ የቁሱን አሰራር መሰረት ያደረገ ነው፡፡ በመለየት ሂደት ውስጥ የቁሱን መጠሪያ ስም መለየት አንዱ ትኩረት የሚሰጠው ጉዳይ ነው፡፡ ለቁሱ መስሪያ ጥቅም ላይ የዋሉ ጥሬ እቃዎችንና አገልግሎታቸውን በአግባቡ ለመግለፅ የሚያስችል ሂደት ነው፡፡**[1]

### ለ. ግምገማ/ Evaluation/

Fleming **ከገለፃቸው የቁሳዊ ባህል መተንተኛዎች ውስጥ ግምገማ ከመለየት ቀጥሎ የሚመጣ ነው፡፡ ቁሶቹ በማህበረሰቦቹ ውስጥ ያላቸውን ደረጃ ለመገምገም የሚያስችል መሆኑ እንደሚከተለው ተገልጿል፡፡**

There are two kinds of evaluation one has to do with judgments of aesthetic quality and work man ship i.e appropriateness of material and texture,skill and test of crafts manship, effectiveness of over all design/proportion, balance,unity/ and expressiveness of form,style and ornament. The other kind of evaluation consists of factual comparisons of one object with others of its

---

[1] History where and when it was made by whom and for whom and why and successive changes in ownership,condition and function.ታሪክ/history /ቁሱ የትና መቼ እንደተሰራ በማንና ለማን ተሰራ?ለምንና በምን አይነት ሁኔታና አገልግሎቱ ይለወጣል፡፡ የቁሱ ባለሙያዎች ስኬታማ የለውጥ ሁኔታና ተግባር የሚታኝበት ነው፡፡ Material involves what the object is made of woods, fibers, ceramic bodies,metals,glass andsoon.ቁሱራሱ/material/ቁሱ የተሰራው ከምንድን ነው ከእንጨት፣ቃጫ፣ብረት፣ሳርና መሰል ነገሮች የተሰሩ መሆናቸውን መነሻ በማድረግ የሚከፋፈልበት ዘዴ ነው፡፡

Construccction has to do with the technigues of manufacture employed,work man ship, and the way parts are organized to bring about the object's function.ባለሙያዎቹ ቁሶቹን የሚሰሩበት ዘዴ፣ የቁሶቹ የተለያየ ክፍል የሚዋቀርበትና አገልግሎት የሚሰጥበትን ሁኔታ የሚዳስስ ነው፡፡ Design includes the structure,form,style,ornament and iconography of the object.የቁሱ ቅርፅ/Design /የቁሱ አወቃቀር፣ቅርፅ፣ዘዴና ጌጣጌጡን መነሻ በማድረግ የሚዋገንበት ዘዴ ነው፡፡Function embraces both the uses/intended functions/ and the roles /unintended functions/ of the object in its culture,including utility,delight,and communication.ቁሶች ለተሰሩበት ዓላማ ወይም ተቀዳሚ ተግባርን ከመከወኛነት ባለፈ የተጠቃሚውን ማህበረሰብ ደስታና ተግባቦትን ገላጭ መሆናቸውን የሚጠቁሙ ናቸው፡፡

kind in quantifiable terms such as relative size, cost, rarity or temporal primacy as determined through objective research.**ይላል፡፡**

ግምገማ ተግባራዊ የሚደረገው በሁለት መልኩ ነው፡፡ አንደኛው የግምገማ አይነት በቁሱ ውበታዊ ዋጋና ባለሙያው መካከል ያለው ተዛምዶ የሚቃኝበት ነው፡፡ ይህ ግምገማ መነሻ የሚያደርገው የሚከተሉትን ነው፡፡ እነሱም፡- የቁሱ ትክክለኝነት፣ገፅታ፣የባለሙያው ችሎታ፣ ከሌሎች የተሻለ አሰራር፣ተመጣኝነቱ፣ተመሳሳይነቱ እና ትርጉም ያለው ቅርፅ፣መልክ እና ጌጣጌጥን የሚቃኝ የግምገማ አይነት ነው፡፡ ሌላኛው የግምገማ አይነት ደግሞ ቁሱ በፈለቀበት አካባቢ ከሚገኙ ጓደኞቹ ጋር አንፃራዊ የሆነ ንፅፅርና ውድድር የሚደረግበት ነው፡፡ አንድ ወይም የተለያዩ ባለሙያዎች የሚያበጁቸውን ተመሳሳይ ቁሶችን  አንድ ላይ በማድረግ የሚነፃፀርበት ነው፡፡

### ሐ. ባህላዊ ትንታኔ/Cultural analysis/

Cultural analysis can carry artifact study beyond description to ward explanation by ‹‹the explication of those critical links that exist between human behavior and its material products.›› **ይላል፡፡ ይህ የቁሳዊ ባህል ሂደት ከመለየትና ግምገማ ቀጥሎ የሚመጣ ነው፡፡ የቁሱ ተጠቃሚ የማህበረሰብ ክፍል ቁሶቹን ከየትኛዎቹ የባህል ዘውግ ጋር አጣጥሞ ጥቅም ላይ እንደሚያውሏቸው የሚተነተንበት ነው፡፡ የቁሱ ተጠቃሚዎች ቁሶቹን የሚጠቀሙት ከምን አስተሳሰብ በመነሳት ነው? ቁሶቹ የማህበረሰቡን ባህል በምን መልኩ ይገልፁታል? ማህበረሰቡ ለቁሶቹ ያላቸው አመለካከት ምን ይመስላል? ቁሶቹ ከማህበረሰቡ ባህል አንፃር ምን ፍይዳ አላቸው? ቁሶቹ ለየትኞቹ የማህበረሰብ ክፍሎች ተምሳሌት ናቸው? የሚሉትን ጥያቄዎች በመመርመር ቁሶቹ ከማህበረሰቡ ባህል ጋር ያላቸውን ተዛምዶ መገንዘብ ያስችላል፡፡**

One important form of cultural analysis deals with the functions performed by the artifact in its culture.unlike the other artifact properties of material, construction, and design, function involves both the concrete and the abstract aspects of the artifact, the reasons for its initial manufacture, its various intended uses, and its unintended roles. **ይላል፡፡**

**ከላይ የቀረበው ሃሳብ የሚስረዳው ባህላዊ ትንታኔ ሁለት አይነት መሆናቸውን ነው፡፡ እነሱም፡-አንደኛው የቁሱ ተግባራዊነት በራሱ ውስጥ መሆኑን የሚቃኝ ነው፡፡ ቁሶቹ**

ከተቀዳሚው ተግባራቸው ባሻገር ምን ትዕምርት አላቸው? ከቁሶቹ አገልግሎት ውስጥ ተሽልቅቆ የሚወጣው እሳቤ ምንድን ነው? ቁሶቹ አሁን የሚሰጡትን አገልግሎት እንዴት ሊሰጡ ቻሉ? ለሚሉት መጠይቆች ምላሽ ለመስጠት የሚያስችል ነው፡፡

ሌላኛው ደግሞ የቁሶቹን አሰራርና ጌጣጌጥ የሚቃኝ ነው፡፡ የቁሱን አገልግሎት ስንቃኝ የሚታየውና የማይታየው ክፍል በጥምርታ መመርመር እንደሚገባ የሚገልፅ ነው፡፡ የቁሶቹ አሰራር ከምን አስተሳሰብ የመነጩ ናቸው? በቁሶቹ ላይ ያለው ጌጥ የማህበረሰቡን የህይወት ፍልስፍና በምን መልኩ ያሳያሉ? ባለሙያዎቹ ቁሶችን ሲሰሩ መነሻ የሚያደርጉት ቅርፅ ምንድን ነው? ቁሶቹ በተጠቃሚዎች እይታ አስደሳች ከመሆናቸው ባሻገር ከጀርባቸው ምን እሳቤ አለ? የሚሉትን ጥያቄዎች በመመርመር የቁሱን ተቀዳሚ ተግባርና ከታለመለት አገልግሎት ባሻገር ያለውን ሚና እንድንገነዘብ ያስችለናል፡፡

### መ. ፍካሬ /Interpretation/

Fleming ካቀረባቸው የቁሳዊ ባህል መተንተኛ ሂደቶች ከባህላዊ ትንታኔ ቀጥሎ የሚመጣው ፍካሬ ነው፡፡ የትኩረት አቅጣጫውም ስለ ቁሶቹ የተገነዘብነውን እውነታ እና በባህሉ ውስጥ ባለው ተግባርና እሴት መካከል ያለውን መስተጋብር የሚቃኝ መሆኑን እንደሚከተለው ገልፀዋል፡፡

> Interpretation is concerned with the relations of the artifact to our culture. more specifically, interpretation focuses on the relation between some fact learned a bout the artifact and some key aspect of our current value system and this relation must be sufficiently intense or rich to have self evident meaning, significance, or relevance.**ይላል፡፡**

ይህ የቁሳዊ ባህል መተንተኛ ሂደት ቁሱ ላይ የፈሰሰውን ጥበባዊ ሃሳብ ከባህሉ ጋር በማዛመድ ፍይዳ ያለው መረጃ የሚገኝ መሆኑን ለመፈከር የሚሞክር ነው፡፡ ‹‹Interpretation will vary as the personal, class, ideological and national interests of Interpreters and their audiences vary.›› ይላል፡፡ ይህ ሃሳብ የሚያስረዳው ፍከራ እንደ ግለሰቡ፣መደብ፣ርዕዮት አለምና እንደ ታዳሚው አተያይ የሚለያይ መሆኑን ነው፡፡

እኔም Prown ካቀረቡት የቁሳዊ ባህል መተንተኛዎች ውስጥ ትርጓሜ/Deduction/ እንዲሁም Fleming ካቀረቡት ውስጥ ደግሞ ባህላዊ ትንታኔን/Cultural analysis/በዋናነት እንደ አስፈላጊነታቸው በውህደት ተጠቅሜባቸዋለሁ፡፡

## 2.2. የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት

ከጥናቱ ርዕሰ ጉዳይ ጋር ተያያዥነት ያላቸው ጥናቶች በአማርኛ ቋንቋ፣ ስነፅሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል ለአርትስ ማስተር ዲግሪ ሟሟያ እንዲሁም ከትምህርት ክፍሉ ውጪ የተሰሩ ጥናቶች አሉ፡፡ የተከናወኑት ጥናቶች ከቁሳዊ ባህል ዘርፍ ውስጥ በምን ላይ የተከናወኑ ነበሩ? ምን ምን ፍሬ ሀሳቦችን አነሱ? የጥናታቸው ዓላማ ምን ላይ ያነጣጠረ ነበር? ከዓላማ አንፃር ያላቸው ጠንካራና ደካማ ጎን ምን ይመስላል? መቼ፣ የትና በማን ተከናወነ? በሚሉት ላይ ትኩረት ያደረገ ነው፡፡ ከእኔ ጥናት ጋር በምን ይዛመዳል እንዲሁም በምን ይለያል የሚለው ሌላኛው የቅኝት ክፍል ነው፡፡ በአማርኛ ቋንቋ፣ ስነፅሁፍና ፍክሎር ትምህርት ክፍል ውስጥ ለአርትስ ማሰተር ድግሪ ማሟያነት የቀረቡትን ጥናቶች ቀዳማይ ከትምህርት ክፍሉ ውጪ ያሉት ጥናቶች ደግሞ ተከታይ በማድረግ  ቀርበዋል፡፡

አስቴር ሙሉ(2000ዓ.ም)‹‹ባህላዊ ቤቶችና ከሸክላ የተሰሩ የቤት ቁሳቁሶች በዘጌ ባህረ ሰላጤ›› በሚል ርዕስ ለአርትስ ማስተር ድግሪ ማሟያ ባቀረበችው ጥናት ዋና አላማ አድርጋ የተነሳችው በዘጌ ባህረ ሰላጤ ውስጥ የሚገኙ ባህላዊ ቤቶችና ከሸክላ የተሰሩ የቤት ቁሳቁሶችን በሳይንሳዊ የአጠናን መንገድ መግለፅ ፣መቅረስ፣መሰነድና እነዚህ ቁሳዊ ባህሎች ህልውና ፈፅሞ ከመጥፋት ተቆጥቦ ለማህበረሰቡ ጠቀሜታ የሚሰጥበትን መንገድ መጠቆም መሆኑን ገልፃለች፡፡ የጥናቷን ዓላማ ለማሳካት ቀዳማይና ካላዓይ የመረጃ ምንጮችን ተጠቅማ መረጃዎችን ሰብስባለች፡፡ ባህላዊ ቤቶቹ ማህበረሰቡ ቅርፁን ተከትሎ በሰጣቸው ስያሜ፣ የሸክላ ቁሶቹን ደግሞ በአገልግሎታቸው መድባ በገላጭ ዘዴ ሰፋ ያለ ትንታኔ አቅርባለች፡፡

ከዓላማ አንፃር ያላት ጠንካራ ጎን የቁሶቹ አገልግሎትና የሚሰነዱበትን መንገድ መግለጿ ነው፡፡ የሸክላ ስራ በሴቶች ብቻ እንደሚከወን ስትገልፅ ምክንያቱንም ጭምር አያይዛ አለመግለጿ በጥናቷ ውስጥ የታየ ክፍተት ነው፡፡ በጥናቷ የቁሶቹን አገልግሎትና የባለሙያዎቹን ማህበራዊ ህይወት መመርመሯ እና የሸክላን ስራ በዋናነት ማንሳቷ  ከእኔ ጥናት ጋር ይመሳሰላል፡፡ የእኔ ጥናት ከሸክላ ስራ ጎን የአንጥረኝነትን ስራ መመርመሩ በተወሰነ መልኩ ከርዕሰ ጉዳይ አንፃር ይለያያል፡፡ በተጠኝ መገኛ ቦታ እንዲሁም የእኔ ጥናት በቁሶቹ አማካኝነት የማህበረሰቡን የህይወት ፍልስፍና መመርመሩ ሌላው ልዩነታችን ነው፡፡

ሀብታሙ እንግዳው (2001ዓ.ም) ‹‹በደቡብ ጎንደር አስተዳደር ዞን በሊቦ ከምከም ወረዳ ሻሞ ጉድጓዲት ገጠር ቀበሌ የሻሞ መድሃኒአለም ሸክላ ስራ ውጤቶች የአሰራር ሂደትና ጠቀሜታ›› በሚል ርዕስ ለአርትስ ማስተር ዲግሪ ማሟያ ባቀረበው ጥናት ዋና አላማ አድርጎ የተነሳው የሸክላ ስራ የአሰራር ሂደት፣ የሸክላ ስራ ውጤቶች የሆኑ ቁሶችን መሰብሰብ ፣ መሠነድ ከዚያም ባለፈ ቁሶች ያላቸውን ባህላዊና ማህበራዊ ፋይዳ መርምሮ ማሳየት የሚል ነው፡፡ ስለ ሸክላ ስራ የአሰራር ሂደት፣አገልግሎትና በማን ይተገበራል? የሚሉ ጉዳዩችን አንስቶ የሚከተለው ማጠቃለያ ላይ ደርሷል፡፡ የሸክላ ስራ አሰራር ተመሳሳይነት ያለው መሆኑን፣ቁሶቹ ባህላዊ፣ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ አገልግሎት ያላቸው መሆኑን እንዲሁም የሸክላ ስራ በሴቶች የሚከወን ተግባር መሆኑን አብራርቷል፡፡ ከዓላማ አንፃር የሸክላ አሰራር ሂደቶችንና ጠቀሜታቸውን መግለፁ ጥንካሬው ሲሆን የሸክላ ስራ በሴቶች ብቻ መከወኑን ሲገልፅ ምክንያቱንም ጭምር አያይዞ አለመግለፁ በጥናቱ ውስጥ የታየው ክፍተት ነው፡፡ ከእኔ ጥናት ጋር የሚመሳሰለው የሸክላ ስራን የአሰራር ሂደት በመመርመሩ ነው፡፡ የእኔ ጥናት የሸክላና አንጥረኝነትን ስራ ጎን ለጎን የሚመረምር መሆኑ፣ የተጠኘው ማህበረሰብ መገኛ ቦታ መለያየት አንደኛው ልዩነታችን ነው፡፡ የእኔ ጥናት በቁሶቹ አማካኝነት የማህበረሰቡን የህይወት ፍልስፋና የሚመረምር መሆኑ ሌላኛው ልዩነታችን ነው፡፡

መሰረት ብርሃኔ (2003 ዓ.ም) ‹‹ሽመናና አንጥረኝነት በጃና አሞራ ወረዳ››በሚል ርዕስ ለአርትስ ማስተር ድግሪ ማሟያ ባቀረበችው ጥናት ዋና አላማ አድርጋ የተነሳችው በጃና አሞራ አካባቢ የሚገኙ ሸማኔዎችና አንጥረኞች ሙያና ህይወት መመርመር፣የቁሱን ምንነት፣አሰራር፣ አገልግሎት እና የሙያተኞች ህይወት ማሳየት የሚል ነው፡፡ ሙያተኞቹን የሚመለከቱ ቃል ግጥሞችን መሰብሰብና መተንተን ሌላው የጥናቷ አላማ እንደሆነ ገልፃለች፡፡ ከዓላማ አንፃር በባለሙያዎቹ የሚሰሩ ቁሶች ስያሜ፣ ለቁሱ መስሪያ የሚያስፈልጉ ጥሬ እቃዎች፣የቁሱን አሰራርና አገልግሎት መግለጿ ጥንካሬዋ ነው፡፡ የአንጥረኝነት ሙያ በወንዶች እንደሚከወን ስትገልፅ ምክንያቱንም ጭምር አያይዛ አለመግለጿ በጥናቷ ውስጥ የታየው ክፍተት ነው፡፡ በጥናቷ በአንጥረኛ ባለሙያዎች የሚሰሩ ቁሶችንና አሰራራቸውን መመርመሯ ያመሳስለናል፡፡ በተጠኚዎች መገኛ ቦታ እንዲሁም በጥናቴ ውስጥ የሽመና ስራ አለመነሳቱ ልዩነታችን ነው፡፡ በቁሶቹ አማካኝነት የማህበረሰቡን የህይወት ፍልስፋና በእኔ ጥናት መመርመሩ ሌላኛው ልዩነታችን ነው፡፡

ደግሰው ጥላሁን (2003ዓ.ም) ‹‹ባህላዊ የሸክላና የቆዳ ስራ በቡሬና ወንበርማ ወረዳ›› በሚል ርዕስ ለአርትስ ማስተር ድግሪ ማሟያ ባቀረበችው ጥናት ዋና አላማ አድርጋ የተነሳችው

ባህላዊ የሽክላና ቆዳ የአሰራር ሂደትና ጥቅም ማሳየትና መቅረስ፣የባለሙያዎቹን የህይወት ልምድ መዳሰስ ነው፡፡ ባለሙያዎቹ ከሌላው ማህበረሰብ ጋር ያላቸውን ግንኙነት እና በሙያቸው ያገኙትና ያጡትን ጉዳይ መቃኘት ሌላኛው ዓላማ መሆኑን ገልፃለች፡፡

የሽክላና ቆዳ የአሰራር ሂደትና ጥቅም እንዲሁም የባለሙያዎቹን የህይወት ልምድ ምን እንደሚመስል ተመልክታ የሚከተለው ማጠቃለያ ላይ ደርሳለች፡፡ ጥናቷ ባተኮረበት ቦታ ላይ ቁሶቹ ተመሳሳይ የአሰራር ሂደትን የሚከተሉ መሆናቸውን እንዲሁም ቁሶቹ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ያላቸው መሆናቸውን ገልፃለች፡፡

ከዓላማ አንፃር የሽክላና ቆዳ የአሰራር ሂደትና ጥቅምን እንዲሁም የባለሙያዎቹን ህይወት መተንተኗ ጥንካሬዋ ነው፡፡ የሽክላ ስራ በሴቶች የሚከወን ተግባር መሆኑን ስትገልፅ ምክንያቱንም ጭምር አያይዛ አለመግለጿ በጥናቷ ውስጥ የታየው ክፍተት ነው፡፡ ስለ ሸክላ አሰራርና አገልግሎት እንዲሁም የባለሙያዎቹን ህይወት መመርመሯ ያመሳስለናል፡፡ በእኔ ጥናት ውስጥ የቆዳ ስራ አለመመልከቴ እንዲሁም በተጠኝዎች መገኛ ቦታ ልዩነት አለን፡፡ በቁሶቹ አማካኝነት የማህበረሰቡን የህይወት ፍልስፋና በእኔ ጥናት መመርመሩ ሌላኛው ልዩነታችን ነው፡፡

አብይ አክሊሉ አበበ (2004ዓ.ም) ‹‹የክስታኔ ማህበረሰብ የቤት ውስጥ መገልገያ ቁሶች ጥናት›› በሚል ርዕስ ለአርትስ ማስተር ድግሪ ማሟያ ባቀረበው ጥናት ዋና አላማ አድርጎ የተነሳው በክስታኔ ማህበረሰብ ምን ምን አይነት የቤት ውስጥ መገልገያ ቁሶች እንዳሉ መለየት፣አገልግሎታቸውንና ባህላዊ ፋይዳቸውን መግለፅ የሚል መሆኑን አብራርቷል፡፡ ቁሶቹ በበቀሉበት ማህበረሰብ ውስጥ ምን ምን የቤት ውስጥ መገልገያ ቁሶች እንዳሉ እንዲሁም ምን አገልግሎት አላቸው የሚሉትን ጉዳዩች ተመልክቶ የሚከተለው መደምደሚያ ላይ ደርሷል፡፡ የቤት ውስጥ መገልገያ ቁሶቹ ከተለያዩ ጥሬ እቃዎች የሚሰሩ መሆናቸውን እንዲሁም ቁሶቹ በተለያየ መልኩ የእለት ተግባራትን መከወኛ በመሆን እንደሚያገለግሉ ገልጿል፡፡ ከዓላማ አንፃር የቤት ውስጥ መገለገያ ቁሶች ምን ምን እንደሆኑና የቁሶቹን አገልግሎት መግለፁ ጥንካሬውን ያሳያል፡፡ ከአንድ በላይ በሆኑ ንጥረ ቁስ የሚሰሩ ቁሶችን ሲመድብ በምን አግባብ እንደመደባቸው በቅጡ አለማሳየቱ ድክመቱ ነው፡፡ ይህ ጥናት በተጠኝዎች መገኛ ቦታ እንዲሁም ከቁሳዊ ባህል ዘርፍ ውስጥ ሀገረ ሰባዊ እጅ ስራ ላይ ማተኮሩ ከእኔ ጥናት ጋር ያመሳስለዋል፡፡ የአብይ ጥናት በቤት ውስጥ የሚገኙ ቁሶችን ሁሉ የሚዳስስ ሲሆን የእኔ ጥናት ደግሞ በሽክላና አንጥረኛ ባለሙያዎች የሚሰሩ ቁሶች ላይ ብቻ

ማተኮሩ አንደኛው ልዩነታችን ነው፡፡ የእኔ ጥናት  በቁሶቹ አማካኝነት የማህበረሰቡን የህይወት ፍልስፋና  የሚመረምር መሆኑ ሌላኛው ልዩነታችን ነው፡፡

Gedef Abawa [2005] <<An Ethno Archaeological Investigation of Pottery Making Among Traditional Potters of Gondar>> በሚል ርዕስ ለአርኪዮሎጂ ትምህርት ክፍል ለአርትስ ማስተር ዲግሪ ማሟያ ያቀረበው ጥናት ሲሆን ዋና ዓላማው በጎንደር/ ጭልጋ፣እንፍራዝ እና አዲስ ዘመን/የሚገኙ የሸክላ ባለሙያዎች ከጥሬ እቃ አቅርቦት እስከ ቁሱ አሰራር ሂደት በኤትኖአርኪኦሎጂካዊ ምርምር ስልት ለኢትዩጵያ ሴራሚክ የሚያበረክቱትን አስተዋፅኦ መመርመር የሚል ነው፡፡

አጥኚው የሸክላ ስራ በሴቶች የሚሰራ ሙያ መሆኑን፣ በማህበረሰቡ ዘንድ ዝቅተኛ ቦታ እንደሚሰጣቸው፣የገበያው ሁኔታ አንፃራዊ በሆነ መልኩ ጥሩ የሚባል አለመሆኑን እንዲሁም የሸክላ ስባሪዎቹ በሚሰሩበትና በሚሸጡበት አካባቢ ስለሚገኝ ለአርኪኦሎጂካዊ ምርምር አመቺ መሆኑን አስቀምጧል፡፡ ከዓላማ አንፃር ያለው ጥንካሬ የሸክላ ቁሶችን አሰራር ሂደቶችን ማሳየቱ ነው፡፡ የሸክላ ስራ በሴቶች የሚሰራ ሙያ መሆኑን ሲገልፅ ምክንያቱንም ጭምር አያይዞ አለመግለፁ በጥናቱ ውስጥ የታየ ክፍተት ነው፡፡ ይህ ጥናት ስለሸክላ የአሰራር ሂደት መመርመሩ ያመሳስለናል፡፡ ከተጠኝዎች መገኛ ቦታ እንድሁም የእኔ ጥናት ከሸክላ ስራ ጎን የአንጥረኝነት ስራ መመርመሩ አንደኛው ልዩነታችን ነው፡፡ በእኔ ጥናት ውስጥ በቁሶቹ አማካኝነት ቁሶቹ የበቀሉበትን የማህበረሰብ ክፍል የህይወት ፍልስፍና መመርመሩ ሌላኛው ልዩነታችን ነው፡፡

Takele Merid [2007] Gendered Culture Pottery as Women's Activity in Ethiopia;A case  study of selected city in Addis Ababa and its surroundings በሚል ርዕስ ለአርትስ ማስተር ዲግሪ ያቀረበው ጥናት ሲሆን  የጥናቱ ዋና ዓላማ በአዲስ አበባና አካባቢው የሚገኙ የሸክላ ባለሙያዎች  የሸክላ አሰራር ጥበብ መመርመር እንዲሁም የሸክላ ስራ የሴቶች ብቻ መሆኑን መተንተን የሚል ነው፡፡[2] ከአላማ አንፃር ያለው ጠንካራ

[2] ለአርትስ ባችለር ዲግሪ ማሟያ የቀረቡ ጥናቶች በክስታኔ ማህበረሰብ ‹‹የክስታኔ ግጥሞች›› አስራት ጋሻው (1964)ዓ.ም፣‹‹የክስታኔ የለቅሶ ግጥሞች›› ሐረገወይን ድፋባቸው(1974)ዓ.ም፣ ‹‹የክስታኔ ተረቶች›› ሙሉ ነህ ጉግሳ(1993)ዓ.ም በቁሳዊ ባህል ላይ ለአርትስ ማስተር ዲግሪ ማሟያ የቀረቡ ሄለን አላምረው(1999)ዓ.ም ሽመናና ቆዳ ስራ፣ያሬድ ተፈራ(2002)ዓ.ም አልባሳት ላይ፣ ሰይድ ይማም/2001/ዓ.ም አልባሳት ላይ፣ዋልተ ንጉስ መኮንን(2000)ዓ.ም አልባሳት ላይ የኔአለም አረዶ (2000)ዓ.ም አልባሳት ላይ፣አፀደ ያረጋል(2003)ዓ.ም አልባሳት እንዲሁም አዜብ ወርቁ(2006) ዓ.ም አልባሳት ላይ የተደረጉ ጥናቶች እንዳሉ ባውቅም ከእኔ ጥናት ጋር ቀጥተኛ ተያያዥነት የሌላቸው በመሆናቸው በቅኝቴ አላካተትኳቸውም፡፡

ጎን የሽክላ አሰራር ሂደቶችን መመርመሩ እንዲሁም የሸክላ ስራ በሴቶች ብቻ የሚከናወን ተግባር መሆኑን መግለፁ ነው፡፡ የቁሶቹን አሰራር ሲያነሳ አሰራሮቹ ከምን አይነት አስተሳሰብ እንደመነጨ አያይዞ አለመግለፁ በጥናቱ ውስጥ የታየ ክፍተት ነው፡፡ ስለ ሸክላ ቁሶች የአሰራር ሂደት መመርመሩ ከእኔ ጥናት ጋር ያመሳስለናል፡፡ በተጠኝዎች መገኛ ቦታ እንዲሁም የእኔ ጥናት ከሸክላ ስራ ጎን ለጎን የአንጥረኝነትን ስራ መመርመሩ አንደኛው ልዩነታችን ነው፡፡ የእኔ ጥናት በቁሶቹ አማካኝነት የማህበረሰቡን የህይወት ፍልስፍና መመርመሩ ሌላኛው ልዩነታችን ነው፡፡

# 3. የጥናቱ አካባቢያዊ ዳራ

በዚህ ክፍል ውስጥ የጥናቴ ትኩረት የሆነው የክስታኔ ማህበረሰብ ታሪክና አመጣጥ፣ መልካዓ ምድራዊ ገፅታ፣ሀይማኖትና ቋንቋ ቅኝት የተደረገበት ነው፡፡ የማህበረሰቡ የስራ መተዳደሪያ፣የክብረ በዓል አከባበር፣ባህላዊ አስተዳደር ፣የጋብቻና ሀዘን ስነስርዓት ሌላኛው የቅኝት አካል ነው፡፡

## 3.1. የክስታኔ ማህበረሰብ ታሪካዊ አመጣጥ

የክስታኔ ማህበረሰብ ማነው? ከየት መጣ? እንዴት መጣ ? በሚሉት ዙሪያ ያላቸውን አስተሳሰብ ቀዳማይ እንዲሁም በምሁራን የተገለፁትን ሃሳብ ደግሞ ተከታይ በማድረግ አቀርባለሁ፡፡

በኤርትራ ክፍለ ሀገር በአካለ ጉዛዪ አውራጃ ደቀ መሃሪ ወረዳ ከጉርዓ እንደ ፈለሱ ይነገራል፡፡ አዝማች ስብሃት የጎጃም፣ ጎንደር፣ መንዝና ወሎ ተወላጆችን በአስተዳዳሪነት ይዘው መጡ፡፡ በመጀመሪያ ገጀሞ ላይ ሰፈሩ ቀጥለው ምድረ ከብድ፣ከዚያ አይመለል ገቡ፡፡ በመቀጠልም ሰባት ቤት ላይ ሰባት ሰዎችን አስቀመጡ በተጠቀሱት ቦታዎች ላይ ተወካይ እያስቀመጡ ይጓዙ እንደነበር ይነገራል፡፡

የሸክላና አንጥረኛ ባለሙያዎች ግን ቀድመው የመጡ ናቸው፡፡ እስራኤል በግብፅ ጦርነት በተሸነፉበት ጊዜ ጉልት አገር አለ ብለው ወደ ኢትዮጵያ የመጡ የዠርያ ጎሳዎች እንደነበሩ ይነገራል፡፡ እስራኤል ምርኮኞቿን ስታስለቅቅ የሸክላና አንጥረኛ ባለሙያዎች ወደ ኢትዮጵያ መጥተው ስለነበረ እዚሁ እንደቀሩ ይነገራል (ታደለ ወርቁ ቃ፣መ.20/07/09 ኬላ ዙሪያ)፡፡

ወርቁ ተስፋዬ /1987፣2-3/ ነገደ ጉራጌ ጥንቱን ከወንድሞቻቸው ከትግሬ ከጉራዕ ሰዎች ተለይተው ሲመጡ በስደት ወይም በአንዳች ጥፋት ምክንያት የመጡ አይደሉም፡፡ አስቀድሞ እንደተመለከተው በ1327ዓ.ም በአፄ ዓምደ ጽዮን ዘመነ መንግስት የክፍላቸውን ፀጥታ ለመጠበቅ በታማኝነት ከመንግስት ታዘው ብዙ ሰራዊት ሆነው በአይመለል ተሰማርተው ከዚያም አናርያ ድንበር ባለው ሀገር ተናኝተው በአካባቢያቸው የተነሳባቸውን ጦር መክተው በክፍለ ሀገሩ የተገናኙትን አድባራት ሳያስደፍሩ በተሰሩበት ሀገር ፀንተው ክርስቲያኑ ከክርስቲያን ሃይማኖት ፤እስላሙ ከመሀመድ ሃይማኖት ሳይናወፅ ፤በየዘመኑም ከኢትዮጵያ ነገስታት ስር ሳይወጡ ከዓፄ ዓምደ ጽዮን ዘመነ መንግስት እስከ ዛሬ የቆዩ ናቸው፡፡ ይላል፡፡

## 3.2. የወረዳው መልክዓ ምድራዊ ገፅታ

በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል ውስጥ ከሚገኙ ዞኖች አንዱ የጉራጌ ዞን ነው፡፡ ዞኑ በአስራ አምስት ወረዳዎች የተዋቀረ ሲሆን ከነዚህ ወረዳዎች ውስጥ አንዱ የሶዶ ወረዳ ነው፡፡ ወረዳው ሃምሳ ስምንት/58/ቀበሌዎችን አቅፎ የያዘ ነው፡፡ ከነዚህ ውስጥ አራቱ ከተሞች ሲሆኑ 54 ደግሞ የገጠር ቀበሌዎች ናቸው፡፡ የወረዳው ርዕሰ ከተማ ቡኢ ከዞኑ ርዕሰ ከተማ ውልቂጤ በ121 ኪ/ሜ ርቀት ላይ ይገኛል፡፡ ወረዳው በሰሜን፣በምዕራብና ምስራቅ ከኦሮሚያ ጋር ሲዋሰን በስተ ደቡብ ምእራብ ከመስቃን ወረዳ ጋር ይዋሰናል፡፡ የወረዳው ደጋማው አካባቢ በብዛት በእንሰት አብቃይነቱ ይታወቃል፡፡በተጨማሪም ከአዝርእት አይነቶች ገብስ፣ስንዴ፣ጤፍ፣ከአገዳ ሰብሎች በቆሎና ማሽላ ከጥራጥሬ ሰብሎች ባቄላ፣ሽንብራ እና የመሳሰሉት በወረዳው ውስጥ በብዛት የሚመረቱ የሰብል አይነቶች ናቸው፡፡ [የሶዳ ወረዳ ፍይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ፅ/ቤት የተዘጋጀ የስነ ህዝብ ቡክሌት 2009፣31]

የወረዳው መልክዓ ምድራዊ አቀማመጥ ሰንሰለታማና ተራራዎች የሚበዙበት ነው፡፡ በአንዳንድ ቦታዎቹ ደግሞ ወጣ ገባ የሆኑ ቦታዎች የሚታዩበት ወረዳ ነው፡፡ የወረዳው አጠቃላይ ስፋት 88553.5ሄክታር ሲሆን የአየር ንብረቱ 35% ደጋ፣65% ወይና ደጋ ነው፡፡ ከደጋው የወረዳ ክፍል በመነሳት አመቱን ሙሉ የሚፈሱ ወንዞችና ምንጮች በስፋት የሚገኙበት አካባቢ ነው፡፡ የወረዳው ከፍተኛ ቦታ ጉንባር ናዳ የሚባለው ተራራ ሲሆን ከፍታውም ከባህር ጠለል በላይ 3343 ሜትር ነው፡፡ ዝቅተኛው ቦታ ደግሞ ኤጀርሳ ሲሆን ከባህር ጠለል በታች 1850 ሜትር ነው፡፡

ከወረዳው ጠቅላላ መሬት ሊለማ የማይችለው መሬት 12053 ሄክታር ሲሆን ሊለማ የሚችለው መሬት ደግሞ 13301 ሄክታር፣በደን የተሸፈነው9061 ሄክታር ነው፡፡ የመሬት አቀማመጡ ሜዳማ 40%፣ሰበርባራማ 30%፣ገደላ ገደል 23%፣ተራራማ 7% ነው፡፡ ከወረዳው ስነ ምህዳር መለያየት ጋር ተያይዞ ዓመታዊ የዝናብ መጠኑ ከ801-1200 ሚሊሜትር ይደርሳል፡፡ አማካይ የሙቀት መጠኑ ከ10-24 ዲግሪ ሴንቲ ይደርሳል፡፡ በወረዳው ከሚታወቁ ትልልቅ ወንዞች መካከል መቂ፣ለቡና ወልዲያ ተጠቃሽ ናቸው፡፡ (የደ/ብ/ብ/ህ/ም/ቤት ፕሮፋይል 2001፣318)

በ2007 እ.ኤ.አ በተደረገው የህዝብ ቆጠራ የወረዳው አጠቃላይ ህዝብ ቁጥር 134,683 ሲሆን ወንድ 67,130 ሴት 67,553 ሲሆን በገጠር የሚኖሩ ወንድ 60,235 ሴት 60,728 ድምር 120,963 በከተማ የሚኖሩ ወንድ 6,895 ሴት ደግሞ 6,825 ድምር 13,720 ነው፡፡

(Federal Democratc Republic of Ethopia Population Census Commission Central Statistical Agency/፣7)

## 3.3. ሃይማኖት

በሶዶ ወረዳ ውስጥ ከሚገኙ ነዋሪዎች መካከል አብዛኛዎቹ የኦርቶዶክስ ክርስትና ሃይማኖት ተከታዮች ናቸው። ማህበረሰቦቹ ክስታኔ የሚለውን መጠሪያ ሊያገኙ የቻሉበት አብይ ምክንያት የክርስትና ሃይማኖት ተከታይ በመሆናቸው ነው ። በወረዳው ውስጥ አንድ መቶ ሰማንያ ዘጠኝ ደብር በተለያዩ ቀበሌዎች ውስጥ ይገኛል። የእስልምና ሃይማኖት ተከታዮች መስጊድ በቁጥር አንድ ብቻ ነው። የፕሮቴስታንት ክርስትና ተከታዮች ደግሞ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ቁጥራቸው እየተበራከተ መጥቷል። በክርስቶስ ክርስቲያን በክርስቲያን ክስታኔ የተባለ ማህበረሰብ ነን ይላሉ። ማህበረሰቡ የሽምግልና፣ሰርግና ሀዘን ስነ ስርዓት በሚከውኑበት ወቅት ሁሉ ከሃይማኖታዊ አስተምሮ ጋር በማሰናሰን ነው (አቶ አዱኛ ጉግሳ ቃ.መ. 11/05/09 ዓ.ም ዳሞ)።

ጥናቴ ባካለላቸው ቀበሌዎች የሚገኙ የሸክላና አንጥረኛ ባለሙያዎች የኦርቶዶክስ ክርስትና ሃይማኖት ተከታዩች ናቸው። የሸክላ ባለሙያዎች በሰንበት ቀን ለሸክላ ስራ የሚያገለግለውን አፈር አይቆፍሩም። የአንጥረኛ ባለሙያዎችም ብረት ቀጥቅጠው አይሰሩም።

እንደ ድንበሩና ሌሎች አገላለፅ የክስታኔ ጉራጌ አካባቢ ከጥንት ጀምሮ የክርስትና እምነት ከተቀበሉት የሰሜን ኢትዮጵያ ሕዝቦች ተያይዞ የመጣው የክርስትና ሃይማኖት በሰፊው የተሰበከበት ምድር በመሆኑ ሕዝቡ ክስታኔ ጉራጌ የተባለ ሲሆን ስያሜው ክርስትና ከሚለው ቃል የተወረሰ ነው። ክርስታኔዎች በረዥም ዘመናት ጀምሮ የክርስትና እምነት ተከታይና በሰንበት አክባሪነታቸው በጣም የታወቁ ናቸው /1987፣25/ ይላሉ።

## 3.4. ቋንቋ

የክስታኔ ማህበረሰብ አፍ መፍቻ ቋንቋ ክስታንኛ በመባል ይታወቃል። የወረዳውም ሆነ የክልሉ የስራ ቋንቋ አማርኛ ነው። ትምህርቱ የሚሰጠው በአማርኛና እንግሊዘኛ ቋንቋ ነው። በወረዳው ውስጥ ከክስታንኛና አማርኛ ቋንቋዎች በተጨማሪ ኦሮምኛና መስቃንኛ ቋንቋዎች ይነገራሉ። ሶዶ ወረዳ ከመስቃና ኦሮሚያ ስለሚዋሰኑና በጋብቻ የተሳሰሩ በመሆናቸው መስቃንኛና ኦሮምኛ ቋንቋዎች በወረዳው ውስጥ እንዲነገሩ አስችሏል።

በወረዳው ውስጥ የሚገኙ የሸክላ ባለሙያዎች አደይ ሲፈነዳ የሚናገሩት ቋንቋ አላቸው፡፡ ከእነሱ ዘር ውጪ ማንም አይናገረውም እንዲሁም አይረዳውም፡፡ ባለሙያዎቹ በመስቀል በዓል አካባቢ የክስታንኛ ቋንቋን አይናገሩም፡፡ የራሳቸውን ቋንቋ ይጠቀማሉ (ቃ.መ.ሲሳይ ዘውዴ 28/05/09)፡፡

ወርቁ ተስፋዬ /1987፣105/ የአይመለል ጉራጌ /ክስታኔ/የተባለው ሕዝብ የሚነጋገርበት ቋንቋ በጣሙን ከአማርኛ ይጠቀሳል፡፡ ይኸውም ከስር ተያይዞ እንደ መጣው ሰብዓ ጉራጌ በአይመለል ከመሰማራታቸው በፊት የሀገሬው ቋንቋ አማርኛ እንደነበር ይጠቁማል፡፡ በሀገሩ ላይ የነበሩትም ሰባክያን እነ አቡነ ዜና ማርቆስና አቡነ ተክለ ሃይማኖት አማሮች ስለነበሩ ስብከታቸው በአማርኛ ነበር፡፡ ይላል፡፡

## 3.5. የማህበረሰቡ መተዳደሪያ

የክስታኔ ማህበረሰብ የተለያዩ የስራ ዘርፎችን በመከወን ኑሯቸውን ይገፋሉ፡፡ በወረዳው ውስጥ በዋናነት ከሚከወኑ የስራ መስኮች መካከል ግብርና፣ ንግድ፣ የከብት እርባታና ዕደ ጥበብ ስራዎች ይጠቀሳሉ፡፡ በእለተ ሰኞ ሱተን ገበያ፣በእለተ ማክሰኞ ቡኢ ገበያ እንዲሁም በእለተ ቅዳሜ ኬላ ገበያ ላይ በመገናኘት ይገበያያሉ፡፡

የሸክላና አንጥረኛ ባለሙያዎች በተለያየ መጠንና ቅርፅ የሰሯቸውን ቁሶች በወረዳው ውስጥ በሚገኙ ገበያዎች ይሸጣሉ፡፡ ቁሶቹ በገበያ ውስጥ ያላቸው ተራ(የሚሸጡበት ቦታ) ዳር አካባቢ ነው፡፡

እንደ ወርቁ ተስፋዬ አገላለፅ የጉራጌ ብሔረሰብ እጁ ለስራ የበረታ፣አንደበቱ ለነገር የረታ፣እግሩ መንገድ የለመደ ፣በስራው ሁሉ የተወደደ ጠንካራ ህዝብ ነው፡፡ በተቻለው መጠን ጥቅሙን የሚጠብቅ፣ባልባሌ ነገር የማይደለል ነው፡፡ ሰነፍ፣ዘዋሪ፣ዋሾ፣ስራ የሚጠላ፣ከብቱን የማይጠብቅ፣ጥቅምና ጉዳቱን የማያመዛዝን ሆኖ የሚታይ ሰው በሕዝቡ ዘንድ የተናቀ ሆኖ የአጥፊነት ስም ይሰጠዋል (1987፣24) ይላል፡፡

## 3.6. ክብረ በዓል

የክስታኔ ማህበረሰብ የተለያዩ በዓላትን የሚያከብሩ ሲሆን ትልቅ ቦታ የሚሰጡት ግን ለመስቀል በዓል ነው፡፡ የመስቀል በዓልን አስደሳችና ማራኪ በሆነ መልኩ ለማሳለፍ የቤተሰብ

አባላት የስራ ክፍፍል ያደርጋሉ። የልጃገረዶች፣ወጣት ወንዶች፣የአባቶችና እናቶች ተግባር በሚል ይከፋፈላሉ።

የልጃገረዶች ተግባር፡- ከወርሃ ነሀሴ ጀምሮ የመኖሪያ ቤታቸውን ያሳምራሉ። የወጣት ወንዶች ተግባር ደግሞ ወደጫካ በመሄድ ለመብራት ተመራጭ የሆነ እንጨት ማምጣት፣መፍለጥ እንዲሁም የማሰር ተግባራትን ይሰራሉ ።

የእናቶች ተግባር፡-የተለያዩ ቅመማ ቅመም ከገበያ መግዛት፣ቤት ውስጥ ጥገት ላሞች ካሉ የሚሰጡትን ወተት በማጠራቀም ቅቤና አይቤ በጥሩ ሁኔታ ያዘጋጃሉ። ጥገት ላሞች ከሌሉ ደግሞ ቅቤና አይቤ ከገበያ ይገዛሉ።

የአባቶች ተግባር፡-ለእርድ የሚሆን ከብት መግዛትና በአንጥረኛ ባለሙያዎች በሚሰሩ ቢላዋና መጥረቢያ ተጠቅመው ያርዳሉ።

የመስቀል በዓል መከበር የሚጀምረው መስከረም 13 ቀን ሲሆን የበዓሉ ስነ ስርዓት የሚጠናቀቀው ደግሞ ጥቅምት 5 ቀን ነው። መስከረም 13 ቀን እናቶች በሸክላ ባለሙያዎች በሚሰሩ የኮለሊት ቁሶች ጎመን በማዘጋጀት ከጎረቤቶቻቸው ጋር በመጠራራት የሚመገቡበት እለት ነው። መስከረም 14 ቀን ደግሞ የደንጌሳት በዓል ሲሆን ጎረቤታሞች የሸክላ ባለሙያዎች በሚሰሩት የጀበና ቁስ ቡና በቅቤ ወይም በወተት አፍልተው የሚጠጡበት ቀን ነው። መስከረም 15 ቀን ጨርቆስ በመባል ይታወቃል። በዚህ ቀን ሰንጋና መሲና እንድሁም ለመጠጥ የሚሆን ጠላና አረቂ ተዘጋጅቶ የእርድ ስነ ስርዓት የሚከናወንበት እለት ነው። መስከረም 16 ቀን የሽማግሌዎች ደመራ በመባል ይታወቃል። መስከረም 17 ቀን በጠዋት ቁርስ ሳይበላ ደመራው ወደ ተቀጣጠለበት ቦታ ላይ ሳቡኘት /እድር/በሙሉ ይሰባሰባሉ። የሳቡኘት ዳኞች የሹም ሽረት ስነ ስርዓት የሚያደርጉበት ወቅት ነው።

መስከረም 18 /የፊቃቆ ማይ/ የስንደዶ ቀን በመባል የሚጠራበት እለት ነው። ልጃገረዶች በጠዋት ተነስተው ምግብ ሳይቀምሱ በየአካባቢው ለስፌት የሚሆን ስንደዶ ያሰባስባሉ። ያመጡትን ስንደዶ እንደ ደረቀ በየቤቱ ጣራ ላይ ይሰቅሉታል (ፀጋዬ ታቦር ቃ.መ.09/05/09 ዓ.ም ቡኢ ዙሪያ)።

በሸክላ ባለሙያዎች ከሚሰሩ ቁሶች መካከል አንዱ ደጋሳ ሲሆን መስቀል መድረሱን በማብሰር በኩል ለማህበረሰቡ ጉልህ አስተዋፅኦ አለው። ቁሱ አመቱን መሉ ግድግዳ ላይ ተሰቅሎ

የሚወርደው መስከረም አስር ቀን ነው፡፡ በዚህ እለት በደንብ ይታጠብና መሬት ላይ ይቀመጣል፡፡

የሽክላ ባለሙያዎች አደይ ሲፈነዳ ቀያቸውንና ስራቸውን ለቀው የሚሰደዱበትን ምክንያትን አስመልክቶ የሽክላ ባለሙያ የሆኑት ወ/ሮ እሸቴ ኩራዝ እንዲህ ገልፀውታል፡፡ " ያው እኛ መስቀል ሲቃረብ ወደ መራን እህዳለን፡፡ የሰጡንን እንቀበላለን፡፡ እግድህ ያው አንለያይም፡፡ አብረን እህዳለን፡፡ ለመስቀል ካለመንማ ሽግር ይደርስብናል፡፡ ርሃብ ይመጣብናል፡፡ ከቤታችን ሽግር አይጠፍም፡፡ በትሩም ቂቤ ይቀባል፡፡ አበባም ይያዛል" (ቃ.መ 19/05/2009 ቆላ ኑረና)፡፡

## 3.7. ባህላዊ የአስተዳደር ስርዓት

የክስታኔ ማህበረሰብ በተለያዩ ምክንያቶች የሚፈጠሩ አለመግባባቶችን ለመፍታት የሚያበቃ ባህላዊ የአስተዳደር ስርዓት አላቸው፡፡ ስርዓቱ ከቀላል እስከ ከባድ ድረስ ያሉ ግጭቶችን ለመቅረፍ የሚያስችል በየደረጃው የተዋቀረ ነው፡፡

ሳቡኝት/እድር/፡-ይህ የዳኝነት ስርዓት በመጀመሪያ ደረጃ ላይ የሚገኝ ሲሆን ማህበረሰቡ በየቅያቸው ተሰባስበው ተግባራዊ የሚያደርጉት ስርዓት ነው፡፡ ድሮም ሆነ  በዛሬው ጊዜ አገልግሎት እየሰጠ ያለ ተቋም ነው፡፡

በሳቡኝት ስርዓት ውስጥ ከሚከወኑት መካከል የሚከተሉት ተጠቃሽ ናቸው፡፡ እነሱም፡-ጥፍተኛ የሚታረምበት፣ኅበዝ የሚበረታታበትና ለተቸገረ እርዳታ የሚደረግበት ስርዓት ነው፡፡ መልካም ስነ ምግባርን መነሻ በማድረግ ሹመት የሚሰጥበት ክፍል ነው፡፡

የሀገር ሸንጎ፡-ሁለተኛው የአስተዳደር መዋቅር ሲሆን በሀገር ሸንጎ  ውስጥ ስልጣን ያላቸው አካላት በየወሩና ሶስት ወሩ በመሰባሰብ በተለያዩ ጉዳዮች ላይ ውይይት ያደርጋሉ፡፡ በእነሱ አቅም ሊፈቱ የሚችሉ መሰናክሎችን ለመፍታት ያላሰለሰ ጥረት ያደርጋሉ፡፡ የተከሰተው ችግር ከአቅማቸው በላይ ከሆነ  ደግሞ ጉዳዩን የበላይ አካላቸው ወደ ሆነው ጎርደና ሸንጎ ያሳልፋሉ፡፡

የጎርደና ሴራ፡-በሶስተኛ ደረጃ ላይ የሚገኝ መዋቅር ነው፡፡ በሀገር ሸንጎ እልባት ያላገኘው ችግር መፍትሔ የሚሰጥበት ተቋም ነው፡፡ የእያንዳንዱ ቀበሌ የጎርደና ሸንጎ ተወካይ አላቸው፡፡ ሴራውን የሚመሩት አዝማችና አበጋዝ በሚል የማዕረግ ስም ይጠራሉ፡፡ የሹመት መመልመያ መስፈርቱም የሚከተሉት ናቸው፡፡ እነሱም፡-በማህበረሰቡ ዘንድ መልካም ስነ

ምግባር ያለው፣ታታሪ ሰራተኛ የሆነ፣የተቸገረን የሚረዳ፣ሀገር እንዳይወረር ጥረት ያደረገና በንብረቱ የተሻለ የሚሉት ተጠቃሽ ናቸው፡፡

ውማኖ፡-አራተኛው የአስተዳደር ስርዓት ሲሆን የሞት/ነፍስ የማጥፋት/ዳኝነት የሚሰጥበት መዋቅር ነው፡፡ ሽማግሌዎች በደል የፈፀመውን አካል ካሳ እንዲከፍል አድርገው ያስታርቃሉ፡፡ የሽክላ ባለሙያዎች በሚሰሩት ገንቦ ጠላ ይቀርብና ሽማግሌዎች መርቀው ከጨረሱ በኋላ ይጠጣሉ፡፡

የሽክላና አንጥረኛ ባለሙያዎች ቀለል ባሉ ጉዳዩች ላይ ምርቃት እንዲመርቁ ይፈለጋሉ፡፡ ማህበረሰቦቹ ምርቃታቸው ይደርሳል ብለው ያምናሉ፡፡ የባለሙያዎቹ ምርቃት ይደርሳል ተብሎ የሚታመንበት ምክንያት አካባቢውን የመሰረቱ ናቸው ተብሎ ስለሚታሰብ ነው፡፡ በሸንጎ ላይ ግን እርቅ እንዲያስታርቁና እንዲመርቁ አይፈለጉም፡፡ የማይፈለጉበት ምክንያቱም ፍትህ ያዛባሉ ተብለው ስለሚታሰቡ ነው( ፀጋዬ ታቦር ቃ.መ. 10/05/09 ዓ.ም ቡኢ ዙሪያ)፡፡

እንደ ድንበሩና ሌሎች አገላለፅ የጉዳ ዳኛው ገዳዩና የገዳይ ወገን የሆኑ ጥቁር ፍየል በመያዝ ወደ አንድ ዛፍ ስር ወስደው ሰው በማያየው ቦታ ላይ ያርዱታል፡፡ ፍየሉ ይታረድና ቶሎ ብሎ አንጀት በማውጣት የገዳይና የሟች ወገን ጣታቸው ይታሰራል፡፡ የዚህን ጊዜ ሁለተኛ አልከዳም፣ቂም አልይዝም መሃላውን አፍርሼ በቂም በቀል ሌላ ወንጀል ብፈፅም ዛሬ እንደዚህ እንደ አንጀት ይቆረጥ በሉ ብሎ አስምሎ አንጀቱን ይቆርጥና ቀብረው ወደ ቤት ይመለሳሉ፡፡ (1987፣13) ይላሉ፡፡

## 3.8. የጋብቻ ስነ ስርዓት

ጋብቻ የሰው ልጆች ከሚያልፉት የህይወት ሽግግር አንዱ ነው፡፡ በክስታኔ ማህበረሰብ ውስጥ የተለያዩ የጋብቻ አይነቶች ሲፈፀሙ ኖረዋል አሁንም የተወሰኑት ይፈፀማሉ፡፡ የጋብቻ አይነቶቹ የሚከተሉት ናቸው፡፡

ሽኮካንቾ፡-ይህ የጋብቻ አይነት የወንድና ሴት ቤተሰቦች ለአቅመ አዳምና ሄዋን የደረሱ ልጆቻቸውን ድግስ ደግሰው ለመዳር ያስባሉ፡፡ በዚህ ወቅት አግቢው በድንገት ከዚህ አለም በሞት የሚለይበት አጋጣሚ ሊኖር ይችላል፡፡ በዚህን ክስተት ሌላ ወንድ ጓደኞቹን ሰብስቦ ወደ ሴቷ ቤት በድንገት በመግባት ልጃችሁን ስጡን ብለው ይጠይቃሉ፡፡ የሴት ቤተሰቦች ወዲያውኑ ተመካክረው ውሳኔ የሚያሳልፉበት የጋብቻ አይነት ነው፡፡ ይህ የጋብቻ አይነት በአሁኑ ወቅት ብዙም የሚፈፀም አይደለም፡፡

ክሊክላ፡-ተጋቢዎቹ ካለ ማንም ተፅዕኖ በራሳቸው ፍላጎት የሚመሰርቱት የጋብቻ አይነት ነው። የጋብቻው አፈፃፀም ወደ ሴቷ ቤተሰብ በቅድሚያ ሽማግሌ ሳይላክ ተግባራዊ የሚደረግ በመሆኑ በሴቷ ቤተሰብ ላይ በተወሰነ መልኩ ቅያሜ ይፈጥራል።

ወዶ ገባ፡- በተለያየ ምክንያት ባሏ የሞተባት ሴት የባሏን ታናሽ ወንድም የምታገባበት የጋብቻ አይነት ነው። የሟችን ንብረት በመቆጣጠር ልጆቹን ላሳድግ በሚል ምክንያት ተግባራዊ የሚደረግ ነው።

መደበኛ ጋብቻ፡- ይህ የጋብቻ አይነት የቤተሰብ መልካም ፈቃድ የተቸረው ነው። የወንድ ቤተሰቦች የሴቷን ቤተሰቦች በማጥናት ሽማግሌዎችን መርጠው ይልካሉ። የሴቷ ቤተሰቦች ቀነ ቀጠሮ ስጡን ብለው ይለያያሉ። በቀጠሮው ቀን ሽማግሌዎች ሲመጡ ወደ ቤት ግቡ ካሏቸው ልጃቸውን ለመስጠት ፈቃደኛ መሆናቸውን የሚያመለክት ነው።

የሽክላና አንጥረኛ ባለሙያዎች ከሙያው ውጪ ካሉ የማህበረሰብ ክፍል ጋር ጋብቻ አይፈፅሙም። ባለሙያዎቹ ጋብቻ የሚፈፅሙት እርስ በርሳቸው ነው። ከሙያው ውጪ ያሉ የማህበረሰብ ክፍል ደግሞ ከሽክላና አንጥረኛ ባለሙያዎች ጋር ጋብቻ የማይፈፅሙበት ምክንያት ሸክላ ሰሪዎች እየሱስ ክርስቶስ የተቀበረበትን መሬት ሰጥተዋል፡ አንጥረኛ ባለሙያዎች ደግሞ እየሱስ ክርስቶስ የተሰቀለበትን ችንካር አቀብለዋል ብለው ስለሚያምኑ ነው (ቃለ መጠይቅ ደበላ ቁፍ 13/05/2009 ኬላ ዙሪያ)።

## 3.9. የለቅሶ ስነስርዓት

ሞት በማንኛውም ነፍስ ያለው ፍጡር ላይ የሚፈጠር ክስተት ነው። በክስታኔ ማህበረሰብ አንድ ሰው ህልፈቱ ሲሰማ ጎረቤት ይሰባሰባሉ። በየቦታው ለሚኖሩ ዘመድ አዝማድ መርዶው ይላካል። ሬሳው ሳይቀበር እስከ ሶስተኛው ቀን ድረስ ይቆያል፡ የአካባቢ ሰዎች በመሰባሰብ ምን ተብሎ ይለቀስ በማለት ለሽማግሌዎች ጥያቄ ያቀርባሉ። ሽማግሌዎቹም ወጣት ከሆነ /አቦ ባይ/፣ትዳር የመሰረተና ወጣትነት መንፈስ ያለው ከሆነ ደግሞ /አቦጎሽ/ ተብሎ ይለቀስ ይሏቸዋል። በማህበረሰቡ ውስጥ ትልቅ ቦታ የሚሰጣቸው ወንዶች ከሆኑ /አቦሹም/ ፣ሴት ከሆነች ደግሞ / አቻም የለና/ እየተባለ ይለቀስ በማለት ሽማግሌዎች መልዕክታቸውን ይገልፃሉ።

የቀብር ስነስርዓት በሚከናወንበት አካባቢ ሴቶችና ወንዶች ለየብቻቸው ዙሪያ ክብ ይሰራሉ። ሴቶቹ ነጠላቸውን ሲያዘቀዝቁ ወንዶቹ ደግሞ ጋቢያቸውን ያደገድጋሉ። ከበሮ እየመቱ ሟች

በህይወት ዘመኑ የተገበራቸውን መልካም ተግባራት በግጥም በማጀብ ያወሳሉ፡፡ በማህበረሰቡ ውስጥ መልካም ስራ የሰሩ፣አዳኝ እንዲሁም መልካም ስብእና ያላቸው ሰዎች ሲሞቱ የአንጥረኛ ባለሙያዎች የሚሰሩትን ጦር ይዘው ያስለቅሳሉ፡፡ ጦር የሚያዘው ጀግና ወንዶች ሲሞቱ ነው፡፡ ሴቶች ሲሞቱ ግን ጦር አይያዝም፡፡

ከቀብር ስነ ስርዓት በኋላ ‹እሳሬ› የሚባል ስርዓት አለ፡፡ የሟች ቤተሰቦች ለእሳሬ ሰጪ ጎሳዎች ሴራ ስጡን ብለው ይጠይቃሉ፡፡ እሳሬ ሰጪዎቹም የሟች ጎረቤቶች እንዲሰበሰቡ ያደርጉና የሟች ቤተሰቦች ሟችን በህመሙ ወቅት በአግባቡ አስታመዋል? አስፈላጊውን እንክብካቤ አድርገዋል? በማለት ይጠይቋቸዋል፡፡ ጎረቤት የሟች ቤተሰቦች ሟችን በአግባቡ አስታመዋል ወይም አላስታመሙም  በማለት ያለውን እውነታ ይገልፃሉ፡፡

የሟች ቤተሰቦች ለሟች አስፈላጊውን ነገር አድርገዋል ተብለው ከተመሰከረላቸው ሴራ ይሰጣቸዋል፡፡ ጎረቤት መልካም ምስክርነቱን ከነፈጋቸው ደግሞ ማህበረሰቡ እግዜር ያጥናችሁ እንዳይላቸው በለቀስተኛው መካከል ወደ ዳር እንዲወጡ ይደረጋል፡፡ ሽማግሌዎች ተሰባስበው ይራገማሉ፡፡ የሟች ቤተሰቦች ተስካር ይደግሳሉ፡፡ በሸክላ ባለሙያዎች በሚሰራው ገንቦ ጠላ ይዘው ወደ ቤተ ክርስቲያን ይሄዳሉ፡፡ ከሸክላ ባለሙያዎች ዘር ውስጥ አንድ ሰው ሲሞት ማንም መርዶ ነጋሪ ሳያረዳቸው ያውቃሉ፡፡ ከያሉበት ቦታም ወዲያውኑ ይሰባሰባሉ፡፡ ግብር ካልተሰጣቸው አስከሬኑን አይሰጡም (ታከለ ደኔ ቃ.መ. 17/5/09ዓ.ም ኬላ)፡፡

# 4. በክስታኔ ማህበረሰብ የሽክላና አንጥረኝነት ስራ መረጃ እና ትንተና

በዚህ ክፍል በሽክላና አንጥረኛ ባለሙያዎች የሚሰሩ ቁሶችን አሰራርና አገልግሎት መተንተን እንዲሁም በቁሶቹ አማካኝነት የማህበረሰቡን የህይወት ፍልስፍና መመርመር ነው፡፡ ቁሶቹን ለማዘጋጀት የሚታለፍ ደረጃዎችና የሽክላ ስራ ላይ በሴቶች የአንጥረኛነት ስራ ደግሞ በወንዶች የሚሰራበትን ምክንያት መተንተን ሌላኛው የትኩረት ክፍል ነው፡፡

የሽክላ ባለሙያዎች ቁሶችን በተለያየ መጠንና ቅርፅ ሲሰሩ ኖረዋል፡፡ በአሁኑ ወቅት ግን በድንበር ተሻጋሪ ዘመንኛ ቁሶች በመወረራቸውና ድሮ ይሰጡት የነበረው አገልግሎት በመቀነሱ ምክንያት መጠናቸው ያሽቆልቁል እንጂ አሁንም ቢሆን በመሰራት ላይ ይገኛሉ፡፡ ባለሙያዎቹ የሚሰሯቸው ቁሶች ለማህበረሰቡ የእለት ከእለት ተግባራትን ለመከወኛነት ከማገልገላቸውም ባሻገር የማህበረሰቡን ሰርካዊ ህይወት በማመልከት በኩል አበርክቶ አላቸው፡፡

ከቁሶቹ ተቀዳሚ አገልግሎት ጀርባቸው ያለውን ጥበብ ፈልቅቆ በማውጣት ቁሶቹ አሁን የያዙትን ቅርፅ እንዴት ሊይዙ ቻሉ? የቁሶቹ ቅርፅ በማህበረሰቡ ውስጥ ምን ትዕምርት አላቸው? የቁሶቹ ተጠቃሚዎች ለቁሶቹ ያላቸው አመለካከት ምን ይመስላል? የቁሶቹ ተጠቃሚዎች ቁሶቹን የሚገለገሉባቸው ከምን አስተሳሰብ በመነሳት ነው? ቁሶቹ ምን የህይወት ፍልስፍና ያሳያሉ? የሚሉትን መጠይቆች በማንሳት መመርመር አስፈላጊ ነው፡፡

በሽክላ ባለሙያዎች የሚሰሩ ቁሶችን የአሰራር ሂደታቸውንና አገልግሎታቸውን እንዲሁም በቁሶቹ አማካኝነት ቁሶቹ የበቀሉበትን ማህበረሰብ የህይወት ፍልስፍና ትንታኔ ሰጥቻለሁ፡፡

## 4.1. የሽክላ ቁሶች አሰራር፣አገልግሎትና የማህበረሰቡ የህይወት ፍልስፍና

**ኩሮ፡-**በሽክላ ባለሙያዎች ከሚሰሩ ቁሶች መካከል አንዱ ነው፡፡ ይህ ቁስ ልዩ መገለጫው ባለ ሁለት ጡት መሆኑ ነው፡፡ ለምን ሁለት ጡት ሆነ? ፍይዳውስ ምንድን ነው? የሚሉትን ጥያቄዎችን ማንሳት ተገቢ ነው፡፡ የኩሮ ቁስ በአፍንጫ በኩል ቅቤ ለመሳብ የሚያገለግል ነው፡፡ አፍንጫ ደግሞ ሁለት ቀዳዳ ስላለው ቅቤው በሁለቱም የአፍንጫ ቀዳዳ እንዲገባ ለማድረግ ነው ይላሉ፡፡ ስለ ቁሱ አሰራር ወ/ሮ አዩነሽ ንጋቱ እንደሚከተለው ገልፀዋል፡፡

> ሲሰራ አፈር ይፈጫል፡፡ እንግድህ ከያ በኂላ አፈር ይቦካል፡፡ ጭቃውን እጠፈጥፈዋለሁ

መቼም አሰራሩና አይነቱ እኮ እንደ ጀበና ነው፡፡ ትንሽ አነስ ይላል እንጂ የሚጀምረው ያው ከቂጡ ነው፡፡ ለጥቆ ወደላይ ማሳደግ ነዋ፡፡ ሆዱን ምን በእጅ ገፋ ገፋ ይደረጋል፡፡ ከዛማ አገቱ ጋ ቲሆን ሲቃረብ በመወጠኛ ይበጃል፡፡ መወጠኛ ጠቃሚ ነች፡፡ አፍን ጠበብ አድርጌ አበጃለሁ፡፡ ጌጥ አበጅለታለሁ፡፡ እ ከያ ሁለት ቀዳዳ ይሰራለታል፡፡ ከዛ ጠሀይ ይመተዋል፡፡ ከዛ በጭራሮ መለብለብ ነዋ በአሁኑ ወቅት ፈላጊ የለም እኮ፡፡ ፈላጊ ጠፍቷል፡፡ የድሮ የለ (20/7/2009 ዓ.ም ቆላ ኑረና ቀበሌ)፡፡

በቃለ መጠይቅ ያገኘሁት መረጃ የኩሮ ቁስ ሲሰራ የሸክላ ባለሙያዎቹ ለሸክላ ተመራጭ የሆነን አፈር ቆፍረው ካመጡ በኋላ በፀሃይ በማድረቅ በድንጋይ ወፍጮ ይፈጩታል፡፡ የተፈጨውን የሸክላ አፈር ውሃ እየጨመሩ ያቦኩታል፡፡ ጭቃውን ወደ ጥላ ቦታ ይዘው ሄደው መስራት ይጀምራሉ፡፡ ስራው የሚጀምረው ከታች /ከቂጡ/ ነው፡፡ ቅርፁን የሚያሲዙት መወጠኛ ቁስ ተጠቅመው ነው፡፡

ቅቤ የሚወርድበትን ባለ ሁለት ጡት ይሰሩለታል፡፡ በተሰነጠቀ ሸንበቆ አማካኝነት እየላጉ ውፍረቱና ስስነቱን ያመጣጥኑታል፡፡ ከዚያም በመቀጠል በቁራጭ የአቡጀዴ ጨርቅ እያሹ ያለሰልሱታል፡፡ ቁሱ ወደሚለበለብበት ቦታ ይወሰዳል፡፡ አለባለቡም መጀመሪያ ደረቅና ቀጫጭን እንጨት ከታች ይደረጋል፡፡ ተከትሎም በላዩ ላይ ደረቅ ሳር ይጎዘጎዛል፡፡ ቁሶቹ ይቀመጡና ከላይ በእርጥብ ቅጠል ይሸፋፈናሉ፡፡ በመቀጠልም እሳቱ ተቀጣጥሎ በጥሩ ሁኔታ ይለበልባሉ፡፡ አመዱን ከቁሶቹ ላይ በርጥብ ቅጠል ያራግፉታል፡፡ ተከትሎም ለሽያጭ ወደ ገበያ ይወሰዳል፡፡ የ‹ኩሮ› ቁስን አገልግሎት በተመለከተ ወ/ሮ እልፍነሽ ደኔ እንዲህ ገልፀውታል፡፡

ድሮ ድሮ በኩሮ ቂቤ በአፍንጫ ይንቀረቀር ነበር፡፡ አሁን እኳ የዱሮ እየጠፋ ነው፡፡ ላሞቹም ብዙም ወተት እኮ አይሰጡ አሁን፡፡ አናት ላይ ለሚቀመጥ እኳ በጣም እየተወደደ እኮ ነው፡፡ ቂቤ በአፍንጫ ሲሳብ ለጆሮ እ ላይን ለራስ እመም መዳኒት ነው፡፡ እኔ ጋ ባጣ ከጎረቤት አይጠፍም ነበር፡፡ የቤቱ አባወራ የቋግሜ ቂቤ በአፍንጫ ቀዳዳ ውስጥ ይቆረቆርለት ነበር፡፡ አራስ ሴት ቂቤ በአፍንጨዋ እንድትስብ ይደረግ ነበር፡፡ እቃዋ ትንሽ ስለሆነች በእጅ ብድግ ተደሮጎ ይሳባል፡፡ አሁን እኳ የድሮው እየጠፍ ነው (ቃ.መ. 21/7/09 ኬላ ዙሪያ)፡፡

የኩሮ ቁስ ቅመማ ቅመም ያልገባበትና የተነጠረ ቅቤ በአፍንጫ ቀዳዎች ውስጥ እንዲገባ የሚያስችል ነው፡፡ ቁስ ባለ ሁለት ጡት በመሆኑ የቤቱ አባወራዎች በሁለቱ የአፍንጫ ቀዳዳ ቅቤውን ይስባሉ፡፡ አባወራዎች የሚስቡት ቅቤ በጳጉሜ ወቅት የታለበውን ወተት በመግፍት ነው፡፡ ቅቤው የሚቀመጠው በተለየ ቁስ ሲሆን አባወራዎች የሚስቡት ቅቤ በማለት ይጠሩታል፡፡ የጳጉሜ ቅቤ የተመረጠበት ምክንያት ወደ አዲሱ ዓመት ሳይሻገር ያለው ቅቤ መድሃኒት ነው ብለው ስለሚያምኑ ነው፡፡ ቅቤውን በአፍንጫቸው የሚስቡበት ምክንያት ለራስ ምታት፣አይንና ጆሮ ህመም መድሃኒት በመሆኑ ነው ይላሉ፡፡ በተጨማሪም አባወራዎች ስራ ውለው ሲመጡ የዛለ ጉልበታቸውን መጠገኛ እንዲሆናቸው በሚል አስተሳሰብ ነው፡፡

ቅመማ ቅመም ያልገባበት ቅቤ የሚስቡት ለምንድን ነው? የሚለውን ጥያቄ ማንሳት ተገቢ ነው፡፡ ቅመማ ቅመም ሲያዘጋጁ የተለያዩ የማቃጠል ባህርይ ያላቸውንና ለቅመሙ የሚያስፈልጉ ነገሮችን ይጠቀማሉ፡፡ቅመም ያለው ቅቤ በአፍንጫቸው ሲስቡ እንዳያቃጥላቸው በማሰብ ቅመሙ አያስፈልግም ይላሉ፡፡

በሌላ መልኩ አራስ ሴቶች የተነጠረ ቅቤ በአፍንጫቸው እንዲስቡ ይደረጋል፡፡ በማህበረሰቡ ውስጥ ሴቶች ወልደው የሚታረሱት በእናቶቻቸው ቤት እንጂ በባሎቻቸው ቤት ወይም በባሎቻቸው ቤተሰቦች ቤት ውስጥ አይደለም፡፡ የተነጠረ ቅቤ በአፍንጫቸው የሚስቡበት ምክንያት ሰውነታቸው እንዲጠነክርና ውበት እንዲኖራቸው ለማድረግ ነው፡፡

የቤቱ እማወራዎች ለመጣው ሰውና ለእንግዳ ቅቤ በአፍንጫቸው እንዲስቡ አይሰጡም፡፡ ቤት ውስጥ ብዙ ቅቤ ካለ ልጆቻቸው  እንዲስቡ ሊሰጡ ይችላሉ፡፡ በዋናነት ግን ለአባወራውና ለአራስ ሴቶች የሚሰጥ ነው፡፡ በአፍንጫ ቅቤ እንዲስቡ መስጠትና አለመስጠት ሙሉ ፈቃድ ያላቸው የቤቱ እማወራዎች ናቸው፡፡ የኩሮ ቁስ አገልግሎትና ቅርፅን መነሻ በማድረግ ቁሱ የበቀለበትን ማህበረሰብ የመካከለኛውንና አሁኑን ወቅት የህይወት ገፅታ አሳያለሁ፡፡ በመጀመሪያ የመካከለኛውን በተከታይነት ደግሞ የአሁኑን ወቅት ነው፡፡

የሸክላ ባለሙያዎች የኩሮን ቁስ ባለ ሁለት ጡት አድርገው እንዲሰሩት ያስቻላቸው መነሻ ፍልስፋና የሰው ልጅ ሁለት የአፍንጫ ቀዳዳ ስላለው ነው፡፡ በኩሮ ቁስ ቅቤ በአፍንጫ መሳብ የማህበረሰቡ ሰርካዊ ህይወት ከእንስሳት ተዋፅኦ በተለይም ከወተትና ቅቤ ጋር የተሰናሰነ  መሆኑን የሚጠቁም ነው፡፡ የአፍንጫ ቅቤ ለመሳብ የሚያስችለው ጥገት ላሞች ሲኖሩ ነው፡፡ ላሞቹ ደግሞ ጥሩ ወተት የሚሰጡት መኖ ሲያገኙ ነው፡፡ መልካምድራዊ

ገፅታው ለእንስሳት እርባታ አመችነት ያለው ከመሆኑም ባሻገር የሚያገኙትን የወተት ተዋፅኦ እንዴትና ለምን እንደሚጠቀሙት ያስገነዝበናል፡፡

በሌላ መልኩ የቤቱ አባወራዎች ቅቤ በአፍንጫቸው መጠጣታቸው ብቻ ሳይሆን በጸጉሜ ወቅት የታለበው ወተት ተገፍቶና ተነጥሮ በልዩ ቦታ መቀመጡ አባወራዎች በቤቱ ውስጥ ትልቅ ክብር ይሰጣቸው እንደነበረና አይነኬነታቸውን ማመላከቻ ነው ብለው ያምናሉ፡፡

ማህበረሰቡ የነጠረ ቅቤ ለአይን፣ ራስና ጆሮ ህመም መድሃኒት ነው ብለው ያስባሉ፡፡ የነጠረው ቅቤ ከምግብ ጋር ተዋህዶ ቢቀርብ ህመሙን ቶሎ ላያስታግሰው ይችላል፡፡ የነጠረውን ቅቤ ቀጥታ በሁለቱም የአፍንጫ ቀዳዳዎች ሲስቡ ግን በሽታው ላይ አርፎ ከህመም ይፈውሳል ከሚል አስተሳሰብ የመነጨ ነው፡፡ በተጨማሪም አባወራዎች በህመም እንዳይጠቁ እንዲሁም በስራ ምክንያት አቅማቸው እንዳይዳከም የሚያደርጉትን ልዩ እንክብካቤ የሚጠቁም ነው፡፡

በማህበረሰቡ ውስጥ ሴቶች ሲወልዱ ወደ እናታቸው ቤት ሄደው ይታረሳሉ፡፡ አራስ ሴቶች እናታቸው ቤት በኩሮ ቁስ በአፍንጫቸው የነጠረ ቅቤ ይስቡ ነበር፡፡ የእናታቸውን ቤት የሚመርጡትም የተሻለ እንክብካቤ ስለሚደረግላቸው ነው፡፡ በባሎቻቸውና ቤተሰቦቻቸው ቤት ከታረሱ ተገቢውን እንክብካቤ አያገኙም ተብሎ ስለሚታሰብ ነው፡፡ የአፍንጫ ቅቤውን ከሩቅ ሀገር የመጡ እንግዶች እንዲስቡ አይሰጥም፡፡ ይህ ደግሞ ለአባወራዎችና አራስ ሴቶች የሚሰጠውን ክብር የሚያመላክት ነው፡፡

ቅቤ በአፍንጫ እንዲስቡ የሚፈቅዱት የቤቷ እማወራዎች ናቸው፡፡ እማወራዎች በቅቤ ዙሪያ ያላቸውን የውሳኔ ደረጃ የሚያሳይ ነው፡፡ እማወራዎች ከልጆቻቸው በተለይም ለአራስ ልጆቻቸው የአፍንጫ ቅቤ መስጠታቸው አራስ ሴቶች በወሊድ ጊዜ ምን ያህል ድካም እንደሚደርስባቸው የሚገነዘቡ መሆናቸውን ያሳየናል፡፡

በኩሮ ቁስ እማወራዎች ለአራስ ልጆቻቸው ቅቤ እንዲስቡ ሲያደርጉ እማወራዎቹ ልጆቻቸውን ሲወልዱ የነበረውን ሁኔታ ወደ ኋላ እንዲያስታውሱ ያደርጋቸዋል፡፡ ትውስታው ግን በወሊድ ጊዜ ያለውን ሁኔታ በማሰላሰል ለመጨነቅ ሳይሆን ድካሙን በመረዳት ጥሩ እንክብካቤ እንዲያደርጉ ለማስቻል ነው፡፡

በሌላ መልኩ አራስ በነበሩበት ወቅት እናቶቻቸው የሚያደርጉላቸውን እንክብካቤ ጭምር እንዲያስታውሱ የማድረግ አቅም አለው፡፡ በሚወልዱበት ወቅት ሆነ በአሁኑ ወቅት

እናቶቻቸውም ሆነ አባወራዎቹ በህይወት የሌሉ ከሆነ ትውስታን የመቀስቀስ አቅም አለው፡፡ ቁሱ በህይወት የሌሉ ሰዎችን ማስታወሱ ያለው ጠቀሜታ ከሰሩት መልካም ነገር ትምህርት ለመውሰድ እንጂ የሀዘን ድባብ ለመፍጠር አይደለም ይላሉ፡፡

የኩሮ ቁስ በአሁኑ ወቅት ፈላጊ የለውም፡፡ ለምን ቁሱ ፈላጊ አጣ? የሚለውን ጥያቄ ማንሳቱ ተገቢ ነው፡፡ ማህበረሰቦቹ ለምን ቁሱን የመግዛት ፍላጎታቸው አሽቆለቆለ ወይም ጭራሽ ጠፍ የሚለውን መጠይቅ መነሻ በማድረግ በማህበረሰቡ ውስጥ በአሁኑ ወቅት ያለውን የህይወት ገፅታ ለመመርመር የሚያስችል ነው፡፡

ቁሱ ይበቅልበት የነበረው ማህበረሰብ በአሁኑ ወቅት ከጥገት ላሞች የሚያገኙትን ቅቤ በመሸጥ ለእለት ተግባር ማዋላቸው እንዲሁም ቅቤን በአፍንጫ ከመጠጣት ይልቅ ለክትፎ መስሪያ መገልገላቸው ተጠቃሽ ነው፡፡ በአንዳንድ ቀበሌዎች ውስጥ ደግሞ ጥገት ላሞች ቁጥራቸው መቀነሱ የተወሰኑ ላሞች ቢኖሩም በአፍንጫ ቅቤ ለማሳብ የሚያደርስ ቅቤ የሚያስገኙ አለመሆናቸው ነው፡፡ የቅቤው ዋጋ ውድ መሆን ሌላኛው ተጠቃሽ ምክንያት ነው፡፡

በሌላ መልኩ ሴቶች ሲወልዱ በአሁኑ ወቅትም ወደ እናታቸው ቤት ይሄዳሉ፡፡ በአፍንጫቸው የሚስቡት ቅቤ ግን የሚያገኙበት ሁኔታ የተመናመነ ወይም ጭራሹን የጠፋ መሆኑን ይጠቁመናል፡፡ የተገኘውን ቅቤ ለምግብነትና ለራስ ፀጉር የሚጠቀሙበት እንደሆነ የሚያስገነዝብ ነው፡፡ የኩሮ ቁሶች ይሰጡት የነበረውን አገልግሎት በተለያየ ምክንያት ማቋረጣቸው ቁሶቹ በአሁኑ ወቅት ፈላጊ እንዲያጡ አስችሏል፡፡

**ኮለሊት፡-** የሸክላ ባለሙያዎች ጥበብ የተፈነጠቀበት ቁስ ነው፡፡ የቁሱን አሰራር አስመልክቶ ወ/ሮ ምንጬ ረጋሳ እንዲህ ገልፀዋል፡፡

> ያው ኮለሊት አበጃለሁ እንግድህ ሳበጅ አፈር ቆፍሬና ፈጭቼ ነው፡፡ አቦከዋለሁ እንደእህል በለው እየታሸ ይሰራል፡፡ ውሃና አፈሩ ይቀላቀላል ከዚያማ ውሃ ሲበዛ የሸክላ አፈር ብን አደርጋለኂ ከዛ በደንብ አዋህደዋለሁ፡፡ እቃው ትንሽ ስለሆነ በጥቂቱ ጭቃ ይበቃኛል፡፡ ከዛ አበጃለኂ ከቂጡ ነዋ የምጀምረው ወደላይ ያድጋል በእጄ ውስጡን አበጃለሁ ከዛ በመወጠኛዬ አስተካክላለሁ፡፡ ከዛ በጎን ጆሮ ከዚያ ጌጥ አበጅለታለሁ፡፡ ጥሩ እንዲሆን ነዋ ያው እንግድህ በጭራሮ መለብለብ ነዋ፡፡ የምለበልበውማ ጥሩ እንዲሆን ቶሎ እንዳይሰበር ነዋ ከዛማ ምን አለ መሸጥ ነው እቃው ብዙ ፈላጊ አለው ( ቃ.መ.22/7/09ዓ.ም)፡፡

 

ወ/ሮ ምንጩ ረጋሳ ቁሶችን ሲተኩሱና ሲያፀዱ

እኔም በመስክ ቆይታዬ እንደተመለከትኩት የኮለሊት ቁስ ሲሰራ በመጀመሪያ ባለሙያዎቹ ለሸክላ ስራ የሚሆን አፈር ይቆፍራሉ፡፡ የሸክላውን አፈር በመያዣ እቃ ውስጥ ይከቱታል፡፡ በመቀጠልም በጀርባቸው ተሸክመው ወደ ሚሰሩበት ቦታ ይወስዳሉ፡፡ በፀሃይ ያደርቁትና በትንሹ የድንጋይ ወፍጮ ይፈጩታል፡፡ አንዳንድ ጊዜም በዱላ ደብድበው ያደቁታል፡፡ በዚህ መንገድ የተፈጨው የሸክላ አፈር በውሃ ይቦካል፡፡ በሚቦካበት ወቅት የሸክላው አፈር ከበዛ ውሃ ይጨመርበታል፡፡ በተመሳሳይ ውሃ ከበዛ ደግሞ የሸክላ አፈር እየጨመሩ የማመጣጠን ስራ ይሰራሉ፡፡ የተቦካውን የሸክላ አፈር በእቃ ወደ ጥላ ቦታ ይዘው ሄደው መስራት ይጀምራሉ፡፡

ቁሱን መስራት የሚጀምሩት ከታች /ቂጡ/ ሲሆን ወደ ላይ እያሳደጉት ይሄዳሉ፡፡ የቁሱን ሆድ ለመስራት እጃቸውን በዱሽ ጨብጠው ያሰፍታል፡፡ የቁሱን ቅርፅ የሚያሲዙበት መወጠኛ ቁስ አላቸው፡፡ አንገቱን ሰርተው ከጨረሱ በኋላ ሁለት ትይዩ ጆሮ ይሰሩለታል፡፡ በማስከተልም በእሳት ይተኩሱታል፡፡ አንዳንድ ጊዜ በእጃቸው አንጠልጥለው በሌላ ጊዜ ደግሞ በጀርባቸው ተሸክመው ወደ ገበያ ይዘው ይሄዳሉ፡፡ የኮለሊት ቁስን አገልግሎት በተመለከተ ወ/ሮ ዘርጊ ተረዳ እንዲህ ገልፀውታል፡፡

> እኛ ክስታኔ በኮለሊት ነው ጎመን እምቀቅል፡፡ ሴት እጂ ወንድ ጎመን ተራ አይሄድም በኮለሊት ካልሆነ ጎመን አይቀቀልም፡፡ ልጆች ከኮለሊት ውቺ ከቀቀሉ እቆጣለሁ ባህላችን ነዋ በሌላ እቃ ጎመን መቀቀል ባህላችን አደለም፡፡ ጎመንማ ጎመን ነው ከኮለሊት ውቺ ግን አይቀቀልም፡፡ ነገርኩህ እማደል እንዴ ባህላችን ነው ያው ከኮለሊት ውቺ የተቀቀለ ጎመን ይታወቃል፡፡ አይጣፍጥም

> በኮለሲት ሲቀቀል ግን ጥሩ ነው። ሁሌ ጎመን ስለሚቀቀልበት ወዙ አይቀየር። ደሞ እኛ የምንወደው ቆጮና ቂጣ በመሆኑ ደረቅ ይላል። ጎመኑ ሲኖር ስለሚያርሰው ሽጋ ይሆናል። ይጣፍጣል። በዚያ እያራስን እንመገባለን። ኮለሲት ውስጥ ጎመን ስናስገባ ወገባችንን ጎንበስ አድርገን ነው። ቀጥ ተብሎ ተቆሞ ኮለሲት ውስጥ ጎመን አይገባም። ባህላችን ይከለክላል። በባህላችን ስለሚከለከል ነዋ እንዴ እንዴት ተገትረን ኮለሲት ውስጥ ጎመን እንጨምራለን። ያው በቆምንበት ጎመን ኮለሲት ውስጥ ካስገባን አይበስልም ጎመን ሲበስል መልኩን እንዳይለወጥ ደሞ አፈሳ አፈር በጥብጠን በውሃው ይሰራል (ቃ.መ.24/07/09 ዓ.ም ኬላ ዙሪያ ቀበሌ)።

የኮለሲት ቁስ ጎመንን ከመቀቃያነት ባሻገር የማህበረሰቡን እምነትና የአመጋገብ ሁኔታ ያመለክተናል። ማህበረሰቡ ጎመን በኮለሲት ቁስ ሲቀቀል እንጂ በሌላ ቁስ ሲቀቀል ጣዕምና የለውም እንዲሁም አይበስልም የሚል እምነት አላቸው። እሳቤአቸውን ግልፅ ለማድረግ የድስትን ቁስ በንፅፅርነት ማሳየት ይበጃል። ድስት ወጥ ይሰራበታል። አንዳንድ ጊዜም አብሲት የሚጣልበት ሁኔታ አለ። አብሲት የተጣለበት ድስት ወጥ ሲሰራበት አብሲት አብሲት የሚልበት አጋጣሚ ጠባብ ነው። የዚህ ምክንያት ወጥ ውስጥ ከሽንኩርት ጀምሮ ወጡን የሚያጣፍጡና ጥሩ ሽታ የሚያስገኝ ቅመማ ቅመም ስለሚጠቀሙ ነው።

በኮለሲት ጎመን ሲቀቀል ግን አብዛኛውን ጊዜ ከጎመን፣ ውሃና ጨው ውጪ ሌላ የሚገባበት ነገር የለም። በኮለሲቱ ከጎመን ውጪ ቢቀቀልበት በኋላ ጎመኑ ሲቀቀል ቀድሞ የተቀቀለበት ነገር ጣዕሙንና ሽታውን ስለሚጋራው ነው። በክስታኔ ማህበረሰብ ውስጥ ብዙ ጊዜ ለምግብነት የሚውሉት ቆጮና ዳቦ ናቸው። የተጠቀሱት የምግብ አይነቶች ደግሞ ደረቅ ያሉ በመሆናቸው ለስለስ ያለ ማብያ ይፈልጋሉ። ለዚህ ደግሞ ተመራጭ የሚያደርጉት ጎመንን ነው። ጎመን በማበረሰቡ ውስጥ ልዩ ትኩረት የሚሰጠው የአትክልት ዘር ነው። ይህ የአትክልት አይነት ተመራጭ የሆነበት ምክንያት አንድም ለስላሳ ስለሆነ በሌላም መልኩ እንደ ወጥና መሰል የማባያ አይነቶች የተለያዩ ቅመማ ቅመምን የሚፈልግ ባለመሆኑ ነው። ይህም የምግብ ማበያን በቀላሉ የሚያዘጋጁና የሚጠቀሙ መሆናቸውን የሚያስገነዝብ ነው።

የክስታኔ ማህበረሰብ ለጎመን ያላቸውን አመለካከት አስመልክቶ አቶ ታደለ ወርቁ (ቃ.መ.17/08/09ዓ.ም.ኬላ ዙሪያ) እንዲህ ገልፀውታል። ጎመን ለስላሳ ማብያ ነው። ለቆጮው እ ለዳቦው። በርካታ ጎመን እሚገኝ በክረምት ነው። እህል ክረምት ላይ ሲያልቅ ጎመን

ይደርስና ከሽግር ያላቅቃል። ለእንቁጣጣሽ እሸቱ ስለሚደርስ ‹‹የጎመን ምንቸት ውጣ የገንፎ ምንቸት ግባ›› ይባላል ፡፡

የክረምት ወቅት በበጋ የተመረተው እህል የሚመናመንበት ወይም ጨርሶ የሚያልቅበት ጊዜ ነው፡፡ በዚህ ወቅት ጎመን የሚደርስበት እንደመሆኑ መጠን ችግራቸውን ይወጡበታል፡፡ ጎመኑን ቀቅለው እየተመገቡ ክረምቱን ሙሉ ይወጣሉ፡፡ የእንቁጣጣሽ እለት ችቦ ሲበራ ‹‹የጎመን ምንቸት ውጣ የገንፎ ምንቸት ግባ›› ይላሉ፡፡ የጎመን ምንቸት ውጣ የሚባልበት ምክንያት እስካሁን ከችግር አላቀኸናል አሁን ደግሞ ወቅቱ መስከረም ስለሆነ እሸት ደርሷል፡፡ እሸቱን በገንፎም ሆነ በተለያየ መንገድ እያዘጋጀን እንመገባለን ይላሉ፡፡ የጎመን ምንቸት ውጣ ሲባል ከእንግዲህ በኂላ አንፈልግህም ማለት ሳይሆን እረፍት እንስጥህ እንደማለት ነው፡፡ ለዚህ ሃሳብ ማስረጃ ከእንቁጣጣሽ በኂላ ለመስቀል በዓል የጎመን ቀን ተብሎ ይከበራል፡፡ ከዚያም ባሽገር የክረምቱን ያህል ባይሆንም የእለት ማበያነቱ ቀጣይነት አለው ይላሉ፡፡

በክስታኔ ማህበረሰብ ጎመን ተራ ሴቶች እንጂ ወንዶች አይሄዱም፡፡ ወንዶች ለምንድን ነው ጎመን ተራ የማይሄዱት? የሚለውን ጥያቄ ማንሳት ተገቢ ነው፡፡ ጎመን በርከሽ ዋጋ የሚሸጥ ወይም የሚገዛ በመሆኑ ሴቶች የሚከውኑት ተግባር ነው፡፡ ሰንጋና ሙክት መሸጥም ሆነ መግዛት ደግሞ ብዙ ገንዘብ የሚጠይቅ ወይም የሚያስገኝ በመሆኑ የወንዶች ተግባር ነው፡፡ ይህ የሚያሳየው ኢኮኖሚውን በበላይነት የሚቆጣጠሩት ወንዶች መሆናቸውን ነው፡፡ አባወራውና እማወረዋ ገበያ ሄደው አባወራው ምግብና መጠጥ ቤት ሲገባ እማወረዋ ግን አብረውም ሆነ በግሏ አትገባም፡፡ የማትገባበት ምክንያት የእገሌ ሚስት ባለጌ ናት፡፡ ምግብና መጠጥ ቤት ገባች ይሉኛል ከሚል አስተሳሰብ መነሻ ነው ይላሉ፡፡

በሌላ መልኩ ጎመን ከመቀቀሉ በፊት የያዘውን መልክ በሚቀቀልበት ወቅት እንዲያገኝ ‹አፈሳ› አፈርን ይጠቀማሉ፡፡ ይህ የአፈር አይነት ከመሬት ተቆፍሮ የሚገኝ ነው፡፡ አፈሩን በውሃ ሲበጠብጡት ከላይ የሚንሳፈፈውን ውሃ ያጠሉታል፡፡ በተጠለለው ውሃ ጎመኑን በሚቀቅሉበት ወቅት ከማሳ ላይ ሲቀጠፍ የነበረውን መልክ ይይዛል፡፡ ከዚህ አፈር ውጪ ከተቀቀለ ግን መልኩን ይለውጣል፡፡ ይህ የሚያሳየው ጎመን መልኩን ሳይቀይር የሚያበስሉበትን መንገድ የሚጠቁም ነው፡፡ የአፈሳን አፈር እንዴት ሊጠቀሙ ቻሉ? ከምን አስተሳሰብ በመነሳት የአፈሳ አፈርን መረጡ? የሚለውን ሃሳብ ስናነሳ ያላቸውን አስተሳሰብ ያመለክተናል፡፡

የኮለሊት ቁስ እሳት ላይ ተጥዶ ጎመን ሲያስገቡ ከወገባቸው ጎንበስ ማለት እንደሚገባቸው በቃለ መጠይቅ ወቅት የተገኘው መረጃ ያመለክታል፡፡ ጎመን የሚቀቅሉ ሰዎች ጎመኑን ኮለሊቱ ውስጥ ሲያስገቡ ለምንድን ነው ጎንበስ የሚሉት? የሚለውን መጠይቅ ማንሳት አግባብነት ያለው ይመስለኛል፡፡ ክስታኔዎች በሰርካዊ ህይወታቸው ውስጥ የቆጮ ማባያ በመሆን የሚያገለግለው ጎመን ነው፡፡ ማህበረሰቡ ለጎመን ክብር እንዳላቸው የሚገልፁበትና ጎመን በኮለሊት ቁስ ውስጥ ለመቀቀል ሲያስገቡ ከወገባቸው ጎንበስ ካላሉ ጎመኑ እንደማይበስል ስለሚያምኑ ነው፡፡

ይህን ሃሳብ ግልፅ ለማድረግ ከአንድ ተጨባጭ መረጃ ጋር ላቆራኘው በክስታኔ ማህበረሰቡ ትልቁ የበዓላት ቀናቸው የመስቀል በዓል መሆኑን በባለፈው ክፍል ለመጠቆም ሞክሪያለሁ፡፡ ለመስቀል በዓል የክስታኔ ማህበረሰብ እንደ አቅማቸው መጠን ስጋ ያስገባሉ፡፡ ቅቤና አይቤውም ይዘጋጃል፡፡ ማህበረሰቡ ስጋና ቅቤ በቤታቸው ውስጥ እያለ የአትክልት ተዋፅኦ የሆነውን ጎመን አይዘነጉትም፡፡ እድሉን ለስጋ ሰጥተው ወደ ዳር አያደርጉትም፡፡ ይልቁንም የዘወትራቸው ምግብ የሆነውን ጎመን ቅድሚያ ሰጥተውት እናያለን፡፡ ቅድሚያ መሰጠቱን የሚያመለክተው በመስቀል በዓል  ዋዜማ ላይ ሆነው መስከረም 13 ቀን የጎመን ቀን የሚባል በዓል ስለሚያከብሩ ነው፡፡

በኮለሊት ቁስ ጎመን ተቀቅሎ ሴቶች ከጎረቤቶቻቸው ጋር ተጠራርተው በዓሉን ያከብሩታል፡፡ የጎመን ቀን ተብሎ መከበሩ ምን ያህል ለጎመን አክብሮት እንዳላቸው የሚያሳይ ነው፡፡ በሌላ መልኩ በኮለሊት ቁስ የተቀቀለውን ጎመን ጎረቤታሞች ተጠራርተው መመገባቸው ጉርብትናቸው በቆመው ቤት ብቻ ሳይሆን በሰዎቹ መካከል መሆኑን ያስገነዝበናል፡፡

በበዓሉ እለት ጎመን ከአይቤና ቅቤ ጋር ተዋህዶ ይቀርባል፡፡ ጎመን በሰርካዊ ህይወት ውስጥ ደግሞ ከውሃና ጨው ጋር ተዋህዶ ይሰራል፡፡ ጎመን በሁለቱ ውስጥ ያለውን ተምሳሌት መመርመር ያስፈልጋል፡፡ የጎመን ውህደት በሁለት ጎራ የተከፈለ ነው፡፡ የመጀመሪያው ጎራ ጎመን ከጨውና ውሃ ጋር ያለውን ግንኙነት የሚያሳይ ነው፡፡ አብዛኛው የማህበረሰብ ክፍል ጨውን በቀላል ወጪ እንዲሁም ውሃን ብዙ ጊዜ በነፃ የሚያገኙ ናቸው፡፡ በቀላል ወጪ የሚገኙ በመሆናቸው ብዙ ማህበረሰብ ይጠቀምባቸዋል፡፡

ሌላኛው ጎራ ደግሞ ጎመን ከክትፎና አይቤ ጋር ያለውን ግንኙነት የሚያሳይ ነው፡፡ እነዚህ የእንስሳት ተዋፅኦዎች ማንኛውም ሰው በቀላሉ የማያገኛቸው የምግብ አይነቶች ናቸው፡፡

እነዚህን የእንሰሳት ተዋፅኦ ለማግኘት ብዙ ገንዘብ ስለሚያስፈልግ ሁሉም የማህበረሰቡ ክፍል ሊያገኛቸው እንደማይችል ማሳያ ነው፡፡

ጎመን ከጨውና ከውሃ እንዲሁም ከክትፎና አይቤ ጋር ተዋህዶ መሰራቱ የኢኮኖሚ መጠናቸው ከፍተኛ ወይም ዝቅተኛ በሆኑ የማህበረሰቡ ክፍሎች ውስጥ አገልግሎት የሚሰጥ እንጂ ሀብታም ወይም ደሃ ብቻ የሚያገኘው አለመሆኑን የሚያሳይ ነው፡፡

ለጎመን ክብር የሚሰጡ የክስታኔ ማህበረሰብ ብቻ ላይሆኑ ይችላሉ፡፡ የክስታኔዎቹ የሚለየው የጎመን ቀን ተብሎ በዓመት አንድ ቀን የሚያከብሩ መሆናቸው እንዲሁም ጎመን ሲቀቅሉ ከወገባቸው ጎንበስ ማለታቸው ለጎመን ያላቸውን የክብር ደረጃ ያመለክታል፡፡ በሌላ መልኩ ጎመን የሚሸጡትም ሆነ የሚገዙት ሴቶች ብቻ መሆናቸው ነው፡፡

**ደንጋሳ፡-**ሌላኛው የሸክላ ባለሙያዎች የስራ ውጤት ነው፡፡ የቁሱን አሰራር አስመልክቶ በዋጮ ቀበሌ የሚኖሩት ወ/ሮ በዜ ሶሪ እንዲህ ገልፀውታል (ቃ.መ.25/07/09) ፡፡ ‹‹ደጋሳ ሳበጅ አፈር እቆፍርና ከዛ በኋላ እሽከማለሁ፡፡ ቀጥዬ ጠሀይ አስመታለሁ፡፡ እንደ እህል በወፍጮ እፈጫለሁ፡፡ ለጥቄ አቦከዋለሁ፡፡ ጥላ ላይ ቁጭ ብዬ አበጃለሁ፡፡ ከዛማ ለጥቄ እየጠፈጠፍኩ አበጀዋለሁ በእጄ አጎረጉደዋለሁ፡፡ መቆሚያ አበጅለታለሁ፡፡ ለጥቄ የሚሰቀልበትን መስቀያ አበጅለታለሁ፡፡ ከያማ ያው በእሳት ይለበለባል››፡፡

በመስክ ቆይታ የተመለከትኩት የደንጋሳን አሰራር በመጀመሪያ የሸክላውን አፈር የሚቆፍሩበት ዶማ እንዲሁም የሸክላውን አፈር የሚቋጥሩበትን እቃ ያዘጋጃሉ፡፡ የሸክላውን አፈር ቆፍረውና ተሸክመው ከመጡ በኋላ በፀሃይ ያደርቁትና የሸክላውን አፈር በዱላ እየደበዱ ያደቁታል፡፡ በውሃ ያቦኩና ወደ ጥላ ቦታ ይዘው ይሄዳሉ፡፡ ስራው የሚጀምረው ከታችኛው ክፍል/ከቂጡ/ ሆኖ ወደ ላይ እያደገ የሚሄድ ነው፡፡ ለምግብ ማስቀመጫ የሚሆነውን ክፍል በእጃቸው እያጎደጎዱ ይሰሩታል፡፡ ከታች ወድቆ እንዳይሰበርና መቆም እንዲችል ዙሪያ ክብ ያለው እግር ይሰሩለታል፡፡ በቤት ውስጥ ግድግዳ ላይ ለማንጠልጠል የሚያስችል ቀዳዳ ያበጁለታል፡፡ አስፈላጊው ጌጣጌጥ ታክሎበት በእሳት ይለበለባል፡፡ ቁሱን የሚተኩሱት ጥንካሬ እንዲኖረው እና በተጠቃሚዎቹ አይን ውብ ሆኖ እንዲታይ ለማስቻል ነው፡፡ የደንጋሳ ቁስን አገልግሎት በተመለከተ በዋጮ ቀበሌ ያገኘኋቸው ወ/ሮ ገረዶ ታዶ እንደሚከተለው ገልፀዋል፡፡

> በኛ በክስታኔ ደንጋሳ የልጆች መብያ እቃ ነው፡፡ ለመስቀል ይወርድና ታጥቦ ይበሉበታል፡፡ በቃው ባልና ሚስት አይበሉም፡፡ በባህሉ ነውር ነዋ፡፡ አይ ባልና

ሚስት በጣባ ነው፡፡ ሁሉም ልጆች የራሳቸው ደንጋሳ አላቸው፡፡ አንዱ የሌላኛውን ደጋሳ አንስቶ አይበላም፡፡ በራሱ ይበላል ከዛ ያው ጥቅምት አምስት ቀን ተመልሶ ይሰቀላል፡፡ ለሚመጣው መስቀል ይወርዳል ደሞ፡፡ እኔ አምስት ልጆች ስላሉኝ ያው አምስቱም ደንጋሳ አላቸው፡፡ ልጅ ሆኜ የራሴ ደንጋሳ ነበረኝ፡፡ ሁላችንም በራሳችን ደንጋሳ እበላ ነበረን፡፡ ልጆች ቢሞትም እናት በደንጋሳው የተዘጋጀውን ታረጋለች እንጂ አትተውም ታስታውሳለች ካጀት የወጡ አደሉ (ቃ.መ.26/7/09)፡፡

የደንጋሳ ቁስ በተበጀበት ማህበረሰብ ውስጥ ከተቀዳሚው አገልግሎቱ ጀርባ ያለው እሳቤ የማህበረሰቡን የህይወት ፍልስፍና የሚገልፅ ነው፡፡ ትላልቅ ሰዎች ለምንድን ነው በደንጋሳ የማይበሉት? በአንድ ወይም በሁለት ደንጋሳ ሁሉም ልጆች በህብረት ወይም በየተራ ለምን አይመገቡም? የሚሉ መጠይቆች በማንሳት ትንታኔ አቀርባለሁ፡፡

በክስታኔ ማህበረሰብ ቤት ውስጥ የሚሰቀሉ የደንጋሳ ቁሶች የልጆቻቸውን ብዛት የሚገልፁ ናቸው፡፡ በቤቱ የውስጠኛው ክፍል ግድግዳ ላይ የተሰቀሉትን ደንጋሳዎች በመቁጠር ስንት ልጆች እንዳሏቸው መገንዘብ ይቻላል፡፡ ስንት ልጆች አላች ብሎ መጠየቅ ብዙም የሚያስፈልግ አይሆንም፡፡ በቤቱ ውስጥ ስንት ልጆች እንደኖሩበትና እንዳደጉበት በግድግዳ ላይ የተሰቀሉ ደንጋሳዎች ምስክርነታቸውን ይሰጣሉ፡፡

ትላልቅ ሰዎች በደንጋሳ የማይበሉበት ምክንያት የልጅነት ጊዜኣቸው ያለፈባቸው ስለሆነ ነው፡፡ ቁሱን ሲመለከቱን ግን ወደ ልጅነት ዘመናቸው በትውስታ የሚመለሱበት ሁኔታ አለ፡፡ ምልሰቱ ደግሞ አሁን ባሉበት እድሜና በልጅነት ዘመናቸውን የነበረውን የበዓል አከባበር እንዲያነፃፅሩ የሚያደርግ ነው፡፡

በሌላ መልኩ ቤተሰቦቻቸውን በተለይም እናታቸውን እንዲያስታውሱ ያደርጋቸዋል፡፡ የደንጋሳ ቁሶች እናቶችን አብልጦ የሚያስታውሱት መስቀል መድረሱን ቁስን አውርደው ስለሚያበስሩና በቁሱ ለልጆች ምግብ የሚሰጡት እናቶች በመሆናቸው ምክንያት ነው፡፡

በአንዱ ልጅ ደንጋሳ ሌላኛው ልጅ የማይበላበት ምክንያት የራስ ያልሆነ ገንዘብ አላስፈላጊ መሆኑን ትምህርት የሚያስርፁበት መንገድ ነው፡፡ በተጨማሪም ለቁሶቹ ልዩ ትዝታ እንዲኖራቸው ለማድረግ ስለሚያስችል ነው፡፡

የደንጋሳ ቁሶች በቤት ግድግዳ ላይ የሚሰቀሉት መጠናቸውን መነሻ በማድረግ ነው፡፡ ከትንንሽ ወደ ትላልቅ በቅደም ተከተል ይሰቀላሉ፡፡ ተመሳሳይነታቸው በቁሶቹ አይነት እንጂ በመጠን አይደለም፡፡ ትናንሽ ደንጋሳዎች ለትናንሽ ልጆች፣መካከለኛ ደንጋሳዎች ደግሞ ለመካከለኛ ልጆች እንዲሁም ትላልቅ ደንጋሳዎች ለትላልቅ ልጆች ውክልና የሚሆኑ ናቸው፡፡ ቁሱ አንድ አይነት የሆነበት ምክንያት ልጆቹ የአንድ ቤተሰብ አባል ስለሆኑ ሲሆን መጠኑ የተለያየው ደግሞ ልጆቹ በእድሜ ስለሚለያዩ ነው፡፡ ልጆች ለአቅመ አዳምና ሄዋን ደርሰው ትዳር መስርተው ከቤት ቢወጡም እኳ ደንጋሳቸው ከቤት ግድግዳ ላይ አይጠፍም፡፡ ትዳር ወደ መሰረቱበት አዲስ ቤትም ይዘውት አይሄዱም፡፡

ትዳር የመሰረቱት ወንዶች ከሆኑ በቤተሰቦቻቸው ግቢ ውስጥ ቤት ይሰራላቸዋል፡፡ ራሳቸውን እንዲችሉ ቤተሰቦቻቸው ካላቸው ሀብት ላይ እየቀነሱ ይሰጧቸዋል፡፡ አባትና እናት በሚያረጁበት ወቅት ግን መንከባከብ ግዴታ ነው፡፡ እንክብካቤ ሳያደርጉላቸው ቢሞቱ ግን ከቀብር በኋላ ‹‹እሳሬ›› በሚባለው ስርዓት ላይ ይረገማሉ፡፡ ለቀስተኛው እግዚአብሄር ያጥናችሁ እንዳይላቸው ከለቃስተኛው መካከል እንዲወጡ ይደረጋል፡፡

በሌላ መልኩ ሴቶች ትዳር ሲመሰርቱ የባላቸው ቤተሰቦች ጣባ ያዘጋጁላቸዋል፡፡ የሴት ቤተሰቦች እንደ ወንድ ልጆቻቸው ካላቸው ሀብት ላይ ቀንሰው አይሰጡም፡፡ ልጆቹ ግን ቤተሰቦቻቸውን ይንከባከባሉ፡፡ ለወንዶች ልጆቻቸው ሀብት ሰጥተው ለሴት ልጆቻቸው ለምን አይሰጡም? የሚለውን ጥያቄ ማንሳት አስፈላጊ ነው፡፡ ለወንድ ልጆች በግቢ ውስጥ ቤት የሚሰሩበትና ሃብት የሚያካፍሉበት ምክንያት በሚያረጁበት ወቅት ከኖሩበት ቦታ ሳይለቁ እንዲጦሩ ስለሚፈልጉ ነው፡፡ ለሴት ልጆች ሀብት የማያካፍሉበት ምክንያት ባሏ ቤተሰቦቹ እንደሚካፍሉት ስለሚያውቁና ከኖሩበት ቤት ለቀው በአማች ቤት ውስጥ መጦር ስለማይፈልጉ ነው ይላሉ፡፡

ለመስቀል በዓል ቤተሰቦቻቸው ጋር ያልመጡ ልጆች ካሉ ደንጋሳቸው ከተሰቀለበት አይወርድም፡፡ በዚህን ጊዜ የሚመጣ እንግዳ ስንተኛው/ዋ/ ልጅ እንዳልመጣ/ች/ ደንጋሳው የተሰቀለበትን እንጨት በመቁጠር ይረዱታል፡፡ ያ/ያቺ/ የመጀመሪያ ፣መካከለኛ እና የመጨረሻ ልጃቻችሁ ለምን አልመጡም ብለው እንዲጠይቁ ያስችላቸዋል፡፡ ለመስቀል በዓል የተገኙና ያልተገኙት ልጆችን መለያም በመሆን ያገለግላል፡፡ ሁሉም ደንጋሳዎች ከተሰቀሉበት ግድግዳ ላይ ከወረዱ ለበዓሉ ሁሉም ልጆች እንደመጡ ይታወቃል፡፡

በደንጋሳ ቁስ ሲመገቡ የነበሩ ልጆች ከዚህ ዓለም በሞት ሲለዩ ቁሱ ከበዓል ውጪ ከተሰቀለበት ወርዶ ባዶ አይሆንም። በህይወት ያሉ ልጆች ከሚጠቀሙባቸው ደንጋሳዎች ጋር ሳይነጠሉ ይቀመጣሉ። የመስቀል በዓል ሲደርስ ደንጋሳዎቹ አብረው ይወርዱና ይታጠባሉ። እናቶች ክትፎና ጎመን ሲያዘጋጁ በህይወት ለሌሉ ልጆቻቸው በህይወት እያሉ ሲበሉበት በነበረው ደንጋሳ ላይ የድርሻቸው ነው ብለው ያስቀምጡላቸዋል። በህይወት እንዳሉ ይቆጥራሉ። ደንጋሳው ላይ ያደረጉትን ጎመንና ክትፎ እናቶች በህይወት የሌሉ ልጆቻቸውን እያስታወሱ ይመገቡታል። አንዳንድ ጊዜ የሟች ድርሻ ነው ብለው ለሌሎች ሰዎች የሚሰጡበት አጋጣሚ አለ።

የደንጋሳ ቁሶች በቤት ግድግዳ ላይ ዘወትር የተሰቀሉ በመሆናቸው በህይወት ያሉትንም ሆነ የሌሉትን ልጆች የማስተወስ አቅም አለው። የሰዎች አይን  ወደ ግድግዳ ቀና ባለ ቁጥር አንዳች ትውስታ ይዞ ይመጣል።

ቁሶቹ ለመስቀል በዓል መውረዳቸው ደግሞ ከመስቀል በዓል ጋር ከፍተኛ ትስስር ያላቸው መሆኑን ማመላከቻ ነው። ይህም እናቶች ቁሱን ከተሰቀለበት ግድግዳ ላይ አውርደውና አጣጥበው መስቀል መድረሱን ስለሚያበስሩበት ነው። ቁሶቹ በዓል ጠብቀው መውረዳቸው ማህበረሰቡ ለቁሶቹ ልዩ ክብር ያላቸው መሆናቸውን የሚያሳይ ነው።

የደንጋሳ ቁሶቹ በቤት ውስጥ ግድግዳ ላይ መጠናቸውን መሰረት አድርገው በሚደረደሩበት ወቅት ቤቱ በተመልካች አይን ውብ ሆኖ ይታያል። ይህን የተመለከቱ ሰዎች  የእማወረዋን ባለሙያነት ይገነዘቡበታል። ቁሶቹን በስርዓት የማይደረድሩ እማወራዎች በማህበረሰቡ እይታ ቤታቸውን አስጊጠው  የማይዙ ናቸው ይላሉ።

**ነክብ፡-** በሸክላ ባለሙያዎች የሚሰራ ቁስ ነው። የቁሱን አገልግሎት በተመለከተ በኬላ ዙሪያ ቀበሌ ያገኘኋቸው ወ/ሮ እልፍነሽ ደኔ እንደሚከተለው ገልፀዋል።

> ነክብ የአባወራ መብያ ነው። ትንሽ ተለቅ ይላል እጄ እንደ ጣባ ነው። ኮሶ በሚጠጣበት ወቅት ቅንጬ፣ገንፎና ክትፎ ሰውነት እሚጠግን ምግብ ትሰራለትና በነክብ ይበላል። እሷ አባወራው ካልፈቀደ በቃው አትበላም እነሱን ታስቀድማለች እጄ። ከሩቅ አገር እንግዳ ቢመጣም በነክብ አይሰጥም በኛ ክስታኔ በባህሉ ነውር ነው። በጣባ ይሰጣል በነክብ እማ አይሰጥም። አማች የሚበላበትም ጣባ ለብቻው አለ። በኛ በክስታኔዎች /አማች ይበላቦት/ ይባላል። ከእንግዳ ጣባ የሚለየውማ ጌጣም የበዛበት ነውና ነው (ቃ.መ.17/06/09ዓ.ም)።

የነክብ ቁስ አገልግሎት አባወራዎች በበዓልና ኮሶ በሚጠጡበት ወቅት ቅንጬ፣ገንፎና ክትፎ ለማቅረቢያነት የሚያገለግል ነው፡፡ አባወራ ኮሶ በሚጠጣበት ወቅት ሰውነቱ ጉዳት እንዳይደርስበት ጥሩ ጥሩ የሚባሉ የምግብ አይነቶችን ባለቤቱ ሰርታ በነክብ ታቀርባለች፡፡ አባወራው ካልፈቀደ በቀር የቤቱ እማወራ በነክብ አትመገብም፡፡ አማችም ሆነ ከሩቅ ሀገር የመጡ እንግዶች በነክብ አይመገቡም፡፡ በነክብ ቁስ መመገብ የሚችሉት አባወራው የፈቀዳቸው የራሱ ጓደኞች ናቸው፡፡ ቁሱ የአባወራነትን ደረጃ ለማግኘት የማጓጓት መንፍስ የመፍጠር አቅም አለው፡፡ አባወራ ያልሆኑ ሰዎች አባወራ ስንሆን እንመገብበታለን የሚል እሳቤ ይቀርፃል፡፡

በሌላ መልኩ እማወረዋ ጥሩ የሚባሉ የምግብ አይነቶችን እያዘጋጀች ለአባወራው መስጠቷ በአንድ በኩል ከህመሙ እንዲድን የሚጠቀሙትን መድሀኒት ያመለክታል፡፡ በሌላ መልኩ ደግሞ መድሃኒቱ ጉዳት እንዳያደርስ የሚያዘጋጁላቸውን ምግብ ይጠቁማል፡፡ እማወረዋ ለአባወራው የምታደርግለትን እንክብካቤና መልካም አስተሳሰብ የሚያሳይ ነው፡፡ አባወራው በህይወት ከሌለ ደግሞ ቁሱን እየተመለከቱ ቤተሰቦቹ ያስታውሱታል፡፡

በነክብ ቁስ ከአባወራው ፈቃድ ውጪ ሌሎች ሰዎች ለምን አይመገቡበትም? የሚለውን ጥያቄ መመርመር አስፈላጊ ነው፡፡ በክስታኔ በማህበረሰቡ ውስጥ ለአባወራው የሚሰጠውን ክብር፣ አይነኬነትና ያለውን ተደማጭነት የሚያመለክት ነው፡፡ ለአባወራ ክብር መስጠት በክስታኔ ማህበረሰብ ውስጥ ብቻ ላይሆን ይችላል፡፡ ነገርግን የክስታኔ አባወራዎች ሚስት ባለቤቷን በስሙ ወይም አንተ ብላ አትጣራም፡፡ ይልቁንም በአክብሮት መጠሪያ‹‹አንቱ›› እያለች ትጣራለች፡፡ አባወራው በቤቱ አካባቢ ባለ የእርሻ ቦታ ወይም ጎረቤቶቻቸው ጋር በሚሆንበት ወቅት ለመጣራት ስትፈልግ እጎዷ ስለሌለ አንቱ ብላ ለመጣራት ያስቸግራል፡፡ በዚህን ጊዜ ሁለት አይነት መንገዶችን ትጠቀማለች፡፡ አንደኛው የወለዱ ከሆነ በመጀመሪያው/ዋ/ ልጅ ስም ትጣራለች፡፡ የገሌ አባት ኑ ወይም መግለፅ የፈለገችውን ነገር ታስተላልፋለች፡፡ ልጆች ያላፈሩ ከሆነ ደግሞ አባወራው አለበት ቦታ ድረስ በመሄድ ወይም በአካባቢው የሚገኙ ልጆችን በመላክ መልእክቷን ታስተላልፋለች፡፡

በሌላ መልኩ ባልና ሚስት በመንገድ ላይ ሲጓዙ ባል ከፊት ሚስት ደግሞ ከኋላ ተከትላ ትሄዳለች፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ማህበረሰቡ ለቅሶ፣ሰርግና መሰል ማህበራዊ በሆኑ ጉዳዮች ለመሳተፍ በሚሄዱበት ወቅት አባወራዎቹ ከፊት እማወራዎቹ ደግሞ ከኋላ እየተከተሉ ነው የሚሄዱት ይላሉ፡፡ ይህ የሚያሳየው የአባወራውን መሪነትና የአክብሮት ደረጃ የሚገልፅ ነው፡፡

ጣባ፡- ስለቁሱ አሰራርና መነሻ ቅርፅ በተመለከተ ወ/ሮ ኮከብ አርጋቸው እንደሚከተለው ገልፀዋል፡፡ ‹‹በእንሰት ቅጠል ክትፎ ይበላል፡፡ እኛ ያው እሱን አይተን ጣባ ሰራና፡፡ አሰራሩ ያው እግድህ አፈር ነው ይፈጫል፡፡ በውሃ ቡክት ይደረጋል፡፡ ከዛ ደሞ ይሰራል፡፡ ያው ሲሰራማ ከታች ነው እኮ ጭቃውን በማድበልበል ከዛ ጎድጎድ ከዛ ትንሽ መቆሚያ ይበጃል፡፡ ከዛ ማሳመር ጥሩ ማረግ ነው፡፡ ከዛ መሸጥ ነው›› (ቃ.መ.26/07/09ዋጮ ቀበሌ)፡፡

የሸክላ ባለሙያዎች ጣባን እንዲሰሩ መነሻ የሆናቸው እሳቤ የእንሰት ቅጠል ነው፡፡ የእንሰት ተክል በማህበረሰቡ ውስጥ የሚገኝ ነው፡፡ በድሮ ጊዜም ሆነ በአሁኑ ወቅት በሰርግ፣ክርስትና እንዲሁም በማህበር ቤት የእንሰት ቅጠልን በክብ ቅርፅ በመቁረጥ በእጅ መዳፍ ላይ በማድረግ ክትፎ ይደረግበታል፡፡ ከጎንና ከጎን በሁለት እጅ መዳፍ ደግፎ ክብ ቅርፅ በመስራት በአፋቸው ይመገባሉ፡፡ የክትፎው መጠን ጥቂት ከሆነ ደግሞ በአንድ እጅ ደግፎ በመያዝ በሌላኛው እጅ ክትፎውን ይመገባሉ፡፡ ይህን የተመለከቱ የሸክላ ባለሙያዎች ከታች እንደእንሰቱ ቅጠል ዝርግ ከጎንና ከጎን ደግሞ ክትፎውን ደግፎ በያዘው ክብ የእጅ ቅርፅ መነሻነት ጣባን ለመስራት አስችሎናል ይላሉ፡፡

የእንሰት ቅጠልን በክብ ቅርፅ ተቆርጦና በእሳት ትንሽ ለብ ለብ ተደርጎ እንደ ምግብ ማቅረቢያ ቁስ ሆኖ ያገለግላል፡፡ የተቆረጠውን ክብ ቅጠል ማህበረሰቡ‹‹ጥረት››እያሉ ይጠሩታል፡፡ እንሰት ለምግብነትና ለመመገቢያ ቁስነት የሚጠቀሙበት መሆኑን ይገልፃል፡፡ ይህ ደግሞ እንሰት ከማህበረሰቡ ህይወት ጋር ቁርኝነት እንዳለው የሚገልፅ ነው፡፡

የጣባ ቁሶችን አማችና የሩቅ ሀገር እንግዶች የሚመገቡበት በማለት ተጠቃሚዎቹ ይከፍሉታል፡፡ ጣባው መጠኑ ተመሳሳይ ሆኖ ለምን መክፈል አስፈለገ? የሚለው ጥያቄ ማንሳት አስፈላጊ ነው፡፡ አማች የሚመገብበት ጣባ በመጠኑ ከእንግዳ መመገቢያ ጣባ ጋር እኩል ይሁን እንጂ የአማች መመገቢያ ጣባ በተለያዩ ጌጣጌጦች ያሸበረቀ ነው፡፡ በማህበረሰቡ አጠራር/አማች ይበላቦት/ በመባል ይታወቃል፡፡ ይህ የሚያሳየው በማህበረሰቡ ውስጥ ከአባወራ ቀጥሎ ትልቅ ክብር ለአማች የሚሰጡ መሆናቸውን ነው፡፡ ለአማች ትልቅ ክብር የሚሰጡት ለምንድን ነው? የሚለውን ጥያቄ ማንሳት አስፈላጊ ነው፡፡ በክስታኔ ማህበረሰብ ለአማች ከዘመድ በላይ ክብር ይሰጣሉ፡፡

“አማችና ቂጥ ትርፍ ነው” ፤“ያልወለደ አማች ያልገደለ ዘማች አይባልም” የሚሉት ተረትና ምሳሌዎች የአማሮች ሲሆኑ በክስታኔ ማህበረሰቦች ውስጥ ግን ቦታ የላቸውም፡፡ ክስታኔዎች ለአማች ትልቅ ክብር የሚሰጡበት ምክንያት አማች የሴት ልጅ ባል በመሆኑ ሲያከብሩት

ልጃቸውን በፍቅርና በእንክብካቤ እንዲይዝላቸው ከማሰብ የመነጨ ነው። የሴት ቤተሰቦች ለአማቻቸው መመገቢያ ቁስ ለብቻው ማዘጋጀታቸውና በእሱ ቁስ ሌላ ሰው አለመብላቱ የተሰጠውን ክብር ማሳያ ነው። በሚስቱ ቤተሰቦች ትልቅ ክብር እንደሚሰጠውና እንደቤተሰብ እንደሚያዩት ስለሚረዳ ሚስቱን በክብር ይይዛል።

ሚስት በአንዳንድ ነገሮች ከባለቤቷ ጋር እሰጣ ገባ ሲፈጥሩ ባል ቤተሰቦቿ ለእሱ የሚሰጡትን ክብር በማስታወስ ግጭቱን ከማክረር ይልቅ ረገብ እንዲል ያደርጋል። የባዳነት መንፈስ አይሰማውም። ትዳራቸው በተለያዩ ምክንያቶች እንዳይፈርስ ይጥራል። የአንደኛው ወገን መልካም ተግባር የሌላኛውን ወገን ድክመት የሚሸፍን መሆኑን አመላካች ነው።

ማህበረሰቡ ለወለደም ይሁን ላልወለደ አማች ክብር ይሰጣሉ። የወለደ ከሆነ የሴቷ ቤተሰቦች እንደ ጎሳቸው ይቆጥሩታል። ያልወለደ ከሆነ ደግሞ ከወለደው አማች በላይ ክብር ይሰጠዋል። ሁለቱም አማች ሆነው ላልወለደው አማች የበለጠ ክብር የሚሰጡበት ምክንያት እንዲወልድና ልጃቸው በትዳሯ ተረጋግታ እንድትኖር ለማድረግ በማሰባቸው ነው። ልጃቸውን በአግባቡ የማይዝና ፍቅር የማይሰጣት ከሆነ ደግሞ እንደጠላት ይታያል ይላሉ።

ከሩቅና ቅርብ አካባቢ የመጡ እንግዶች የሚመገቡበት የራሳቸው ጣባ አላቸው። ውበቱ ግን አማች ከሚመገብበት ጣባ ያነሰ ነው። ይህ የሚያመለክተው የሩቅም ሆነ የቅርብ ዘመድ ከበሬታ ቢሰጣቸውም ከአማች ጋር ሲነፃፀር ግን ያነሰ መሆኑን የሚያመለክት ነው።

የቤቱ አባወራ፣አማችና እንግዶች የሚመገቡበት የየራሳቸው ቁስ ሲኖራቸው እማወረዋ የግሏ የምትመገብበት ቁስ የላትም። የአባወራውን ፈቃድ ካላገኘች በነክብም አትመገብም። ይልቁንም በተሰባበረ ወይም በተሰነጠቀ ቁስ ትመገባለች። የራሷን መመገቢያ ቁስ እንዳታዘጋጅ ተከልክላም አይደለም። ቁሶቹን በየአይነታቸው የምታደራጃቸው እማወረዋ እንደመሆኗ መጠን ለእራሷ መመገቢያ ቁስ የማዘጋጀት እድሉ ነበራት። ይልቁንም ለሌሎች ክብር ቅድሚያ መስጠትን፣ራስን ዝቅ ዝቅ ማድረግንና ራስ ወዳድ አለመሆንን የሚጠቁም ነው።

**ጀበና፡-**ይህ ቁስ የሸክላ ባለሙያዎች ጥበብ ያረፈበት ነው። ቁሱ ሁለት ጡት አለው። አሁን አሁን ደግሞ ባለ አንድ ጡት ጀበና አለ። ስለቁሱ አሰራር በተመለከተ ወ/ሮ በለጡ አርጋው እንደሚከተለው ገልፀዋል።

> አሰራሩ ኮ እንደ አንድ መቅጃ ጀበና ነው። ያው ንጥህና ያሸዋል ስራው አፈሩ ሲቆፈርም ሲበጅም ንጥህናው አይለየውም። ንጥህናማ ከተለየው ሸጋ

> አይሆን፡፡ አፈሩ ተቆፍሮ ይመጣል፡፡ ከዛ ይቦካል፡፡ ጣይ እንዳይመታን ደግሞ ጥላ ቦታ ቁጭ ብለን እናበጃለን፡፡ ያው ከቂጡ ነው ሲሰራ የሚጀምረው፡፡ ለጥቆ ቡና የሚቀመጥበት በእጅ ይጎረጎዳል፡፡ ከዛማ የእጅ መያዣ ይበጅለታላ፡፡ ለጥቆ ማ ቡና የሚወርድበት ተቀራራቢ ቀዳዳ ይበጃል እቃው በጭራሮ ይለበለባል፡፡ አሁን አሁን እኳ ቅቤ ስለጠፋ ባለሁለቱ ቀዳዳ እየቀረ ነው (ቃ.መ.29/7/09 ሱተን ዙሪያ)፡፡

የሸክላ ባለሙያዎች ተመራጬን የሸክላ አፈር ቆፍረው ካመጡ በኋላ ይፈጫሉ፡፡ የተፈጨው የሸክላ አፈር በውሃ አማካኝነት ያቦካሉ፡፡ የተቦካውን የሸክላ ጭቃ ቤት ውስጥ ወይም ጥላ ስር ተቀምጠው መስራት ይጀምራሉ፡፡ ቁሱን ሲሰሩ የሚጀምሩት እንደሌሎች ቁሶች ሁሉ ከታች ነው፡፡ ቀጥሎም ወደ ላይ እያደገ የሚሄድ ይሆናል፡፡ የጀበናውን ሆድ በእጃቸው በማጎድጎድ ይሰሩታል፡፡ የጀበናውን ሁለት ጡት ተቀራራቢ በማድረግ ይሰራሉ፡፡ ጌጣጌጡ ተሰርቶላቸው በእሳት ይለበልባሉ፡፡ ስለ ባለሁለቱ ጡት ጀበና አገልግሎት ወ/ሮ የትም ወርቅ ሲሳይ እንደሚከተለው ገልፀውታል፡፡

> ሁለት መቅጃ ያለው ጀበና ቡና እና ቅቤ ለማፍያነት እሚጠቅም ነበር፡፡ አሁን እኳ ያው ቂቤው ከየት ተገኝቶ የወተት ላም እየተፍ ነው፡፡ አፈላሉ እማ ቡናው ተፈልቶ አተላው ይለያል፡፡ ከያማ ቡናና ያልተነጠረ ቂቤ አብሮ ይፈላ ነበር፡፡ ከያማ በንጡህ እሰት ቅጠል አንዱን ቀዳዳ ይሸፈናል፡፡ ከያ በፌጃሉ ላይ ትንሽ ትንሽ ከላይ ጠብ ጠብ ሲደረግ ቂቤው ይወርዳል፡፡ ከያ ይኸን እንደ ገና በቅጠሉ ይሸፈንና በያኛው ቡናው እንዲወርድ ይደረጋል፡፡ በዚህ መንገድ ቡናና ቅቤ ይጠጣ ነበር፡፡ አሁን እኳ እቃው ባለሙያ ቤት ነው የሚገኘው፡፡ ሰው አንድ መቅጃ ያለውን መረጠ፡፡ የቡና ማውረጃውን ታዳ አንዱ ምን ይወርድበታል፡፡ ቂቤ እየጠፍ ነው፡፡ የድሮ ነገር እየጠፍ ነው (ቃ.መ23/7/09 ኬላ ዙሪያ)፡፡

የባለ ሁለት ጡት ጀበና ተቀዳሚው አገልግሎት ቡና በቅቤ ለማፍሊያነት የሚውል ነው፡፡ በመጀመሪያ ቡናው ይፈላል፡፡ የተፈላውን ቡና ከአተላው ይጣራል፡፡ በማስከተል የተጣራው ቡና ባለሁለት ጡት ጀበና ውስጥ ይገባና ይጣዳል፡፡ በመቀጠልም ያልተነጠረ ቅቤ ይገባል፡፡ ቡናው ሲፈላ ይወርድና ከሰከነ በኋላ አንዱን ጡት በእንሰት ቅጠል በመሸፈን በሌላኛው ጡት ከላይ ያለው ቅቤ እንዲወርድ ቀስ በማድረግ ዘንበል ይደረግና በመጠኑ ለመጠጫ በተዘጋጀው ቁስ ላይ ይቀዳል፡፡

በእንስት ቅጠል ተጠቅጥቆ የነበረውን የጀበና ጡት ውታፋን በማላቀቅ በሌላኛው ጡት ይወተፋል፡፡ ቡናው ደግሞ ባልተወተፈው ጡት በኩል እንዲቀዳ በሚደረግበት ወቅት ቅቤው አብሮ እንዳይወርድ ወደ ቅቤው ማውጫ ጡትና ወደ አንገቱ በኩል ዘንበል ያደርጉታል፡፡ ይህን መንገድ ተጠቅመው ቡና በቅቤ ታዳሚዎቹ ይጠጣሉ፡፡ ሁለት ጡት ሚናቸው ምንድን ነው? ለምን ሁለት ጡት አስፈለገ? የሚሉትን ጥያቄዎች ማንሳት ተገቢ ነው፡፡

በጀበናው ላይ ያለው ሁለት ጡት ሚና በአንደኛው ጡት ቅቤው በሌላኛው ጡት ደግሞ ቡናውን ለመቅዳት እንዲያገለግል ነው፡፡ ይህን ተግባር ባለአንድ ጡት ጀበና መተግበር የማይቻልበት ምክንያት ቡና በቅቤ ሲጠጣ ቅቤው ከላይ የመንሳፈፍ ባህርይ ስላለው ለተወሰኑ የቡና ታዳሚዎች ብቻ ቅቤ ሲደርስ ለሌሎቹ ታዳሚዎች ደግሞ ቅቤ የሌለበት ቡና ይደርሳል፡፡ ከዚህም ባሻገር ቅቤው በወረደበት ጡት ላይ ቡናው ቢወርድ የቅቤው ወዝ ቡናውን እንደልብ ስለማያስቀዳው ባለ አንድ ጡት ጀበና ተመራጭ አይሆንም ይላሉ፡፡

ይህ የሚያሳየው የማህበረሰቡ ሰርካዊ ህይወት ከእንስሳት ተዋፅኦ በተለይም ከቅቤ ጋር የተያያዘ የነበረ መሆኑን ነው፡፡ በተጨማሪ ከእንሰሳት ተዋፅኦ የሚያገኙትን ቅቤ ለምንና እንዴት እንደሚጠቀሙበት የሚያሳይ ነው፡፡ በሌላ መልኩ ቅቤ ከላይ የሚጠል ቡና ደግሞ ከታች የሚዘቅጥ መሆኑን በመረዳታቸው ባህላዊ እውቀታቸውን ተጠቅመው ለማጣራት ያስቻላቸውን አስተሳሰብ ያሳያል፡፡ ቅቤው ከአተላ ጋር እንዳይነካካ በመጀመሪያ ቡናውን ከአተላው የመለየት ስራ ከውነዋል፡፡ የተጣራውን ቡና እንደገና በማፍላት ቅቤ ተጨምሮበት አተላ የሌለው ንፁህ ቡና በቅቤ መጠጣት አስችሏቸዋል፡፡

ቁሱ በአሁኑ ወቅት በጥቂት ሀብታም ሰዎች ቤት ውስጥ ነው አገልግሎት የሚሰጠው፡፡ ቁሱ በውስን ሰዎች ቤት ውስጥ አገልግሎት መስጠቱ ጥገት ላም ያላቸውና ቅቤውን ከቡና ጋር የሚጠቀሙ ሰዎች የተወሰኑ መሆናቸውን የሚያመላክት ነው፡፡

**ጉልላት፡-**በሸክላ ባለሙያዎች ከሚሰሩ ቁሶች መካከል አንዱ ነው፡፡ ስለ ቁሱ አሰራር በተመለከተ በሱተን ዙሪያ ቀበሌ ውስጥ የሚኖሩት ወ/ሮ መሰሉ እንዳለ እንደሚከተለው ገልፀዋል፡፡

> እንግዲህ አፈር እቆፍራለሁ፡፡ እንደው በአሮጌ እቃ እሸከምና ቤቴ አመጣለሁ ከያ ጥሩ አርጌ አቦካለሁ፡፡ የምሰራበትን እቃ አቀርባለሁ፡፡ ጭቃውን እየጠፈጠፍኩ ሸጋ አርጌ አበጃለሁ፡፡ በመወጠኛዬ አበጃለሁ፡፡ ከያ ጥሩ እንዲሆን በንጥህና ነው እምሰራ በቢላወ እፍቀዋለሁ፡፡ አንገቱ ላይ ሁለት

> ወይም ደሞ አራት መቃነት አበጅለታለሁ፡፡ በእሳት እለበልበውና አመዱን አራግፈዋለሁ፡፡ ከያ ጥሩ ይሆናል (ቃ.መ.02/8/09)፡፡

በመስክ ቆይታዬ እንደተመለከትኩት የሸክላ ባለሙያዎቹ ለሸክላ ስራ ተመራጭ የሆነውን አፈር በዶማና መሰል መቆፈሪያዎች ተጠቅመው ይቆፍራሉ፡፡ አፈሩን በእቃ ተሸክመው ካመጡ በኋላ ፀሀይ ላይ ያሰጡታል፡፡ ለሸክላ አፈር መፍጫ ብቻ በተዘጋጀው ትንሽ ወፍጮ ላይ ይፈጫል፡፡ በዋዳት ውሃ በማቅረብ ከታች ማዳበሪያ ዘርግተው ያቦኩታል፡፡ ከዚያም ቁጭ ብለው ይሰራሉ፡፡ የሚሰሩት መወጠኛ ቁስን ተጠቅመው ነው፡፡ የሚጠቀሙትም መወጠኛ የእንስራ ቁራጭ አንገትን ነው፡፡በቁሶቹ አንገት ላይ ባለ ሁለትና አራት መቃነት መሰል ዙሪያውን  ተሰርቶላቸው ይተኮሱና ለተጠቃሚዎች ይደርሳሉ፡፡ ስለ ጉልላት ቁስ አገልግሎት በኬላ ቀበሌ ያገኘኋቸው አቶ ታደለ ወርቁ  እንዲህ ገልፀውታል፡፡

> ጉልላት ሀብት ያላቸው ሰዎች ናቸው የሚሰቅሉት፡፡ እንግዲህ ትልቅ ሳር ቤት ላይ ይሰቀላል፡፡ ትልቅ ቤት የሚሰሩማ ሀብት ያላቸው ናቸው፡፡ ደሃ በምኑ ይሰራል ብለህ ነው፡፡ ጉልላት የሚሰቀለው ትልቅ ቤት ላይ አሞራ እንዳያበላሽ ነው፡፡ አራት ቀለበት ያለው በጣም ትልቅ ሰው ሁለት ቀለበት ደሞ መካከለኛ ሰው እ ደሃ ቤት ጉልላት አይሰቅልም በባህሉ ነውር ነው፡፡ ያው እግዲህ የሚሰቅለው ኦርቶዶክስ ነው፡፡ እስላም አይሰቅልም ጉልላት(ቃ.መ.27/07/09 )፡፡

የጉልላት ቁስ ከተሰራበት ተቀዳሚ ዓላማ ባሻገር የማህበረሰቡን አስተሳሰብ፣እምነትና የኑሮ ደረጃ የሚያመለክት ነው፡፡ የክስታኔ ማህበረሰቡ ጉልላትን ባለ አራትና ሁለት ቀለበት ያለው በማለት ይለዩታል፡፡ በጉልላቱ ላይ ዙሪያ ክብ የሆነ አራት ቀለበት ካለው ሀብታምና በማህበረሰቡ ውስጥ የትልቅነትን ክብር የተጎናፀፉ ሰዎች ቤት መሆኑን ይጠቁማል፡፡ ጉልላቱ ላይ ባለ ሁለት ቀለበት ካለው ደግሞ በማህበረሰቡ ውስጥ የሀብት መጠናቸውና የክብር ደረጃቸው መካከለኛ የሚባሉ ሰዎች ቤት እንደሆነ ያሳውቀናል፡፡

በሌላ መልኩ ትናንሽና ጉልላት የሌለባቸው ሳር ቤቶች ደግሞ በማህበረሰቡ ውስጥ ደሃ የሚባሉ ሰዎች ቤት መሆኑን የሚያመለክት ነው፡፡ ከድሃ ቤት ላይ ጉልላት የማይሰቀልበት ምክንያት የጉልላት ዋጋው ውድ ስለሆነ ሳይሆን ቁሱ ማህበራዊ ደረጃን የሚጠቁም በመሆኑ በባህሉ የተከለከለ ነው፡፡

ከዚህም በተጨማሪ ጉልላት ቤታቸው ላይ የሚሰቅሉ የኦርቶዶክስ ክርስትና ሃይማኖት ተከታይ  ናቸው፡፡ ጉልላትን ሊያደርጉ የቻሉበት ምክንያት ጉልላት ቤተክርስቲያን ላይ

ስለሚደረግ ነው፡፡ ትላልቅ ሳር ቤት እያላቸው ጉልላት ካላደረጉበት ከኦርቶዶክስ ክርስትና ሃይማኖት ተከታይ ውጪ መሆናቸውን ያሳውቃል፡፡

ሳር ቤት ሲሰራ የወጋግራ እጨት ከምሰሶው ጫፍ ጋር ሲገናኝ ጠባብ ሆኖ የተወሰነ ወደ ላይ ከፍ ይላል፡፡ ቤት ሰሪዎቹም ሲጨርሱ ጎለልን ይላሉ፡፡ የተሰራው ቤት ሳር ይከደንና መጨረሻ ላይ ያለው ሳር ጉልላት ይሉታል ይህ የስያሜው መነሻ ነው፡፡ በሌላ መልኩ ጉልላትን ከምን አስተሳሰብ በመነሳት በሳር ቤታቸው ላይ ይሰቅላሉ? የሚለውን ጥያቄ ማንሳት አስፈላጊ ነው፡፡ ጉልላት የሚሰቀለው በሳር ቤት ላይ ነው፡፡ አሞራዎችና መሰል አዕዋፋት በአብዛኛው የሚያርፉት እቤቱ ጉልላት እንጨት ላይ ነው፡፡ በሳር ውስጥ ደግሞ ትል ይኖራል፡፡ ትሉን ደግሞ አሞራ ይበለዋል፡፡ አሞራዎች ደግሞ ትሉን ሲፈልጉ ሳሩን ይጭሩታል፡፡ ሳር ከተበታተነ ደግሞ ዝናብ በሚመጣ ወቅት ቤቱ ያፈሳል፡፡

ጉልላት ሲያደርጉ ግን ሰዎቹ በዝናብ አይመቱም፡፡ በተጨማሪም ሳሩ በንፍስ እንዳይወሰድ ያስችለዋል፡፡ በሌላ መልኩ ጉልላት የማያደርጉ ሰዎች ድሃ እንደሆኑ ተጠቁሟል፡፡ አሞራው ሳር ቤታቸውን ስለሚጭርባቸው ዝናብና ፀሀይ የሚመታቸው መሆኑን የሚያመለክት ነው፡፡ ትልቅ ሳር ቤት ያላቸውና ከኦርቶዶክስ ክርስትና ሃይማኖት ውጪ የሆኑት ደግሞ ጉልላቱ ላይ ያለው ሳር እንዳይበታተን በጠፍር ይጠቀልላሉ ይላሉ፡፡

ገንቦ፡-የሸክላ ባለሙያዎች የስራ ውጤት ነው፡፡ ማህበረሰቡ ቁሱን ባለ ሶስትና ሁለት ጆሮ በማለት ይከፍሉታል፡፡ ስለ ቁሱ አሰራር ወ/ሮ ቡላል ሶሪ እንደሚከተለው ገልፀዋል፡፡ ‹‹ባለ ሁለትም ጆሮ ባለ ሶስት ጆሮ አሰራሩ አንድ ነው፡፡ ያው አፈን ቆፍሬ አመጣለሁ፡፡ ከዛ ውሃ እየጨመርኩ አቦካለሁኝ፡፡ የኛ ስራ ከጭቃ ጋር ነው፡፡ የመወጠኛ እቃዬን ተጠቅሜ አበጃለሁ፡፡ ውስጡን አጎደጉዳለሁ፡፡ አንገቱን ጠበብ አደርጋለሁ፡፡ ከዛማ ባለሁለት ጆሮና ሶስት ጆሮ አበጃለሁ በእሳት እተኩሳለሁ፡፡ ከዛ ለፈላጊ ይሸጣል›› (ቃ.መ.4/08/09 ዋጮ)፡፡

የሸክላ ባለሙያዎች ገንቦን በሁለት መልክ ይሰሩታል፡፡ አንደኛው ሁለት ጆሮ ያለው ሲሆን ሌላኛው ደግሞ ባለ ሶስት ጆሮ ነው፡፡ የቁሱ አሰራር የሸክላ አፈር ተቆፍሮ ከመጣ በኋላ ወዲያውኑ ወይም በፀሀይ ከደረቀ በኋላ ይፈጭና ይቦካል፡፡ በመቀጠልም ከታች ተጀምሮ እየተሰራ ወደላይ ያድጋል፡፡ ቁሱ ሲሰራ መወጠኛ ቁስ ተጠቅመው ነው፡፡ ሆዱን በእጃቸው ያጎደጉዱታል ወደ አንገቱ አካባቢ ይጠባል፡፡ በማስከተልም አንዳንድ ጊዜ ሁለት ጆሮ ሌላ ጊዜ ደግሞ ሶስት ጆሮ ይሰሩለትና ይተኮሳል፡፡ የገንቦ ቁስን አገልግሎት በተመለከተ ወ/ሮ ዘርጊ ተረዳ እንደሚከተለው ገልፀዋል፡፡ ‹‹ጠላ በጋን ይጠመቃል፡፡ ከጋኑ የተጣራው ጠላ

ገንቦው ውስጥ ሆኖ እንግዳ ፊት ጨርቅ ለብሶ ይቀርባል፡፡ የመጡት እንግዳዎች የሀገር ሽምጋዩች ከሆኑ በባለ ሶስቱ ጆሮ ይቀርባል ባህል ስለሆነ ነው፡፡ በባለሁለቱ ጆሮ የሚቀርብላቸው እማ ከሀገር ሽማግሌዎች በታች ለሆኑ ነዋ፡፡ በጣም ደሃ ለሆነ በገንቦ ጠላ አይቀረብም፡፡ በሽክና ነው››(ቃ.መ.5/08/09 ኬላ ዙሪያ)፡፡

የገንቦ ቁስ የተሰራበት ተቀዳሚ ዓላማ ከጋን ውስጥ የተጠለለውን ጠላ እንግዶች ፊት ለማቅረቢያነት የሚያገለግል ነው፡፡ ቁሱ ባለ ሁለትና ሶስት ጆሮ መሆኑ ከማንጠልጠያነት ባሻገር ማህበራዊ ደረጃን የሚያሳዩ ናቸው፡፡ ቁሱ በፈለቀበት ማህበረሰብ ውስጥ ትልቅ፣መካከለኛና ዝቅተኛ የክብር ደረጃ የሚሰጣቸው ሰዎች በማለት ይከፍሏቸዋል፡፡ ትልቅ ክብር ከሚሰጣቸው ሰዎች መካከል፡- ሀብታም፣የሀገር ሽማግሌዎችና ሀገር እንዳይወረሩ የተዋጉ ሰዎች ተጠቃሽ ናቸው፡፡ እነዚህንና ሌሎች መልካም ነገር ለሀገር ያበረከቱ ሰዎች ጠላ የሚቀርብላቸው በባለ ሶስት ጆሮ ገንቦ ነው፡፡ እንግዶቹም ጠላው የቀረበበትን የገንቦ ጆሮ በማየት የተሰጣቸውን የክብር ደረጃ ይገነዘቡበታል፡፡

መካከለኛ የክብር ደረጃ ለሚሰጣቸው ሰዎች ደግሞ ባለ ሁለት ጆሮ ገንቦ ጠላ ይቀርብላቸዋል፡፡ እንግዶቹም የገንቦውን ጆሮ ተመልክተው ማህበረሰቡ የሚሰጣቸውን ደረጃ ይረዱበታል፡፡ በማህበረሰቡ ውስጥ የሚሰጣቸው ደረጃ ዝቅተኛ ከሆኑ ደግሞ ጠላ በገንቦ አይቀርብላቸውም፡፡ ይልቁንም በሽክና ይሰጣቸዋል፡፡ ይህ የሚያሳየን ማህበረሰቡ በቁሶቹ አማካኝነት ለእንግዶቹ ያላቸውን የክብር ደረጃ ይገልፁበታል፡፡ እንግዶችም ቢሆኑ የቀረበላቸውን ቁስ ተመልክተው የተሰጣቸውን ደረጃ ያውቃሉ፡፡

በማህበረሰቡ ውስጥ ያልታወቀ የክብር ደረጃን በራሳቸው ፍላጎት አግኘው የተቀመጡ ሰዎች ካሉ የክብር ደረጃቸው የት ጋር እንደሆኑ ጠላ የቀረበበትን የገንቦ ጆሮ በመመልከት ይረዳሉ፡፡ ራሳቸው ለራሳቸው እንዲሁም ማህበረሰቡ ለእነሱ የሰጧቸውን የክብር ደረጃ ያመዛዝኑበታል፡፡ በሌላ መልኩ በማህበረሰቡ ውስጥ ትልቅ ክብር የሚሰጣቸው ሰዎች ግን ያላቸውን ክብር የማያውቁ ከሆነ ቁሱን በመመልከት ማህበረሰቡ የሰጣቸውን የክብር ደረጃ ይረዱበታል፡፡

**ጥወ፡-**በሽክላ ባለሙያዎች የሚሰሩ ቁሶች ሲሆኑ ሁለት አይነት ናቸው፡፡ አንደኛው ቤተክርስቲያን ውስጥ አገልግሎት የሚሰጥ ነው፡፡ እኔ የተመለከትኩት ግን የነጠረ ቅቤ ለማስቀመጫነት የሚያገለግለውን ነው፡፡ ቁሱ መጠኑ ትንሽ ሲሆን አንገቱ አካባቢ ሶስት ጆሮ አለው፡፡ ጆሮው ቁሱን ለመስቀያነት የሚያገለግል ነው፡፡ ማስቀመጫ እግር አለው፡፡ የጥወ አገልግሎትን በተመለከተ ወ/ሮ መዓዛ ቡርቃ እንደሚከተለው ገልፀዋል፡፡ ‹‹ጥወ የነጠረ ቅቤ

ማስቀመጫ ነው፡፡ ወዳውም የቤት ጌጥ ነው፡፡ ቤት ግድግዳ ላይ ይሰቀላል ሁሌ ስለሚሰቀል ቂቤው ያዣል፡፡ አሁን እኳን ሊያዥ ያለበትም አይታወቅ፡፡ ጥወ በቤቷ የሰቀለች ሴት ባለሙያ እንደሆች ይገለጣል፡፡ ከጥወ ቅቤ እየተቀነሰ ለጥቅም ይውላል፡፡ ጥወ የሚሰቅሉ ላም ያላቸው ሀብታሞች ናቸው››(ቃ.መ 15/05/09 ዓ.ም ኬላ ዙሪያ)፡፡

የጥወ ቁሱ ተቀዳሚው አገልግሎቱ የነጠረ ቅቤ ለማስቀመጫነት ነው፡፡ ቁሶቹ የሚጠቁሙት አመጋገባቸው ከወተት ተዋፅኦ በተለይም ከቅቤ ጋር ቁርኝት እንዳላቸው ነው፡፡ ቅቤው ደግሞ የማህበረሰቡን አኗኗር ምን እንደሚመስል የሚገልፅ ነው፡፡ ቁሶቹ በቤታቸው ውስጥ የሚገኙና በስርዓት የሚሰቅሉ እማወራዎች በተለይ የወተት ተዋፅኦዎችን በተለያየ መንገድ የማዘጋጀት ሙያ እንዳላቸው ይገልፃሉ፡፡

ቁሶቹ ከተሰቀሉበት በታች የእያዣ የሚወርደው ቅቤ ወዝ ያሳያል፡፡ ከቁሶቹ በታች ወዝ በማየት ጥወው ቅቤ ያለበትና የሌለበትን መሆኑን ማረጋገጫ ነው፡፡ ጥወው ስለተሰቀለ ብቻ ብዙ ቅቤ አለበት አይባልም፡፡ ከተሰቀሉት ቁሶች ግርጌ ያለው የቅቤ ወዝ ቤታቸው ውስጥ ጥገት ላሞች እንዳሉ እና ኑሯቸውም ከወተትና ቅቤ ጋር የተሰናሰነ መሆኑን የሚያስገነዝብ ነው፡፡ በአሁኑ ወቅት ግን ጥወው ቢኖርም የሚቀመጥበት ቅቤ አዥቶ ለመውረድ የሚያበቃ አይደለም፡፡ ይህ የሚያሳየው ቅቤ በብዛት አለመገኘቱን ነው፡፡

**እንጨቡዬ፡-**ይህ ቁስ በሽክላ ባለሙያዎች የሚሰራ ነው፡፡ የጥወ ቅርፅ ያለው ሲሆን በመጠኑ ግን ትንሽ ነው፡፡ የቁሱን አገልግሎት በተመለከተ አቶ ታከለ ደኔ እንዲህ ገልፀውታል፡፡ ‹‹እንጨቡዬ ጥወ ይመስላል እኮ እንግዲህ ትንሽ ቂቤ ማኖሪያ ነው፡፡ ሀብታም በጥወ እጂ በእንጨቡዬ አይዙም፡፡ እንደነገሩ ሽተት ለማድረግ ትንሽ ቅቤ በእንጨቡዬ ድሃ ሰዎች ይይዛሉ›› (ቃ.መ.16/06/09 ኬላ ዙሪያ ቀበሌ) ፡፡

የቁሱ ቅርፅ ከጥወ ጋር ተመሳሳይ ሲሆን በመጠን ግን እንጨቡዬ ትንሽ ነው፡፡ የቁሱ አገልግሎት መጠኑ ትንሽ የሆነ ንጥር ቅቤ ለማስቀመጫነት የሚውል ነው፡፡ ሀብታም ቤት ንጥር ቅቤ በእንጨቡዬ አይቀመጥም፡፡ የነጠረ ቅቤ ሀብታም ቤት ውስጥ የሚቀመጠው በጥወ ሲሆን ድሃ ቤት ውስጥ ደግሞ በእንጭቡዬ ይሰቀላል፡፡

ቁሱ በፈለቀበት ማህበረሰብ ውስጥ እንጨቡዬ በቤት ግድግዳ ውስጥ የሰቀሉ ሰዎች የኑሮ መጠናቸው ዝቅተኛ የሆኑ ሰዎች ቤት መሆኑን የሚጠቁሙ ናቸው፡፡ በቤት ውስጥ ግድግዳ ላይ የተሰቀሉትን የእንጨቡዬ ቁሶች በመመልከት ኑሯቸው ዝቅተኛ እንደሆነና ቁሱም ትንሽ ቅቤ ያለበት ወይም ጭራሽ የሌለበት መሆኑን ይጠቁማል፡፡

**ክርን፡-** በሽክላ ባለሙያዎች የሚሰራ ቁስ ነው፡፡ የቁሱን አሰራር በተመለከተ ወ/ሮ እሸቴ ኩራዝ እንዲህ ገልፀውታል፡፡‹‹ክርን ስሰራ የተወሰነ የተፈጨ አፈር አቦካለሁ፡፡ ከዛማ አድበለብለዋለሁ፡፡ አጠርና ሰፍ አደርገዋለሁ፡፡ ከዛ አጎደጉዳለሁ፡፡ እግር አበጃለሁ ለመስቀያ ጆሮ አበጃለሁ፡፡ ከያ እንዳይነቃ በእሳት ልብልብ አደርግ ነበር፡፡ አሁን እንኳ ገዥ የለም ጠፍቷል›› (ቃ.መ.20/05/09/ዓ.ም ቆላ ኑረና ቀበሌ)፡፡

ክርን ድሮ የሚሰራ ቁስ ነበር፡፡ በአሁኑ ወቅት ግን የሚሰራበት ሁኔታ በጣም የተመናመነ ነው፡፡ የቁሱ ቁመቱ አጠር ያለ ሲሆን ሆዱ አካባቢ ደግሞ ሰፍ ያለ ቅርፅ የያዘ ነው፡፡ በቀረበው ቃለ መጠይቅ ምላሽ መነሻነት የሸክላው አፈር ተቆፍሮ ከመጣ በኋላ በውሃ ይቦካል፡፡ መጠኑ ትንሽ ስለሆነ የተወሰነ የሸክላ ጭቃ በማድበልበል በእጅ የማጎድጎድ ተግባር ይከናወናል፡፡ በማስከተልም የሚቆምበት እግር ይሰራለታል፡፡ በተጨማሪም ለመስቀያነት ወዲያውም ለጌጥ የሚያገለግል ጆሮ ይሰራለታል፡፡ በእሳት ተለብልቦና አመዱ ተራግፎ ለሽያጭ ዝግጁ መሆኑን የሚያስገነዝብ ነው፡፡ የክርን አገልግሎት በተመለከተ ወ/ሮ እንዳሻሽ ጌታሁን እንደሚከተለው ገልፀዋል፡፡‹‹ ክርን  ለወተት ለእርጎም መጠጫ ይሆናል፡፡ ላሞች ሲወልዱ ጥጆች ይፈነጥዛሉ፡፡ ወተት ብዙ ብዙ ይታለብ ነበር አሁን እኳ ወተቱም እየጠፋ ነው፡፡ ላም ደግ ነበር፡፡ ለቂቤው ለወተቱ ጥሩ ነበር››(ቃ.መ.13/08/09 ሱተን ዙሪያ) ፡፡

የክርን ቁስ ተቀዳሚ አገልግሎት የእንሰሳት ተዋፅኦ የሆኑት በተለይም ወተትና እርጎ ለመጠጫነት የሚውል ነው፡፡ ቁሱ የሚያመለክተው ይጠጡት የነበረው ወተት እና እርጎ መሆኑን የሚገልፅ ነው፡፡ በክርን ቁስ ውስጥ ያለው ወተትና እርጎ ደግሞ ኑሯቸውን የሚጠቁም ነው፡፡ የማህበረሰቡ ኑሮ ከወተት ተዋፅኦ ጋር የተቆራኘ መሆኑን የሚገልፅ ነው፡፡ ቁሱ ድሮ ለምን ይሰራል? በአሁኑ ወቅት ደግሞ ለምን መሰራቱ ተቋረጠ? እነዚህ መጠይቆች የመካከለኛውንና አሁኑን ጊዜ በንፅፅር እንድናይ ያስችለናል፡፡ ቁሱ በፊት ይሰራ የነበረው በማህበረሰቡ ውስጥ የወተት ተዋፅኦ በብዛት ይገኝ እንደነበረ ያመለክታል፡፡ ላሞች ይታለባሉ፡፡ በአሁኑ ወቅት ቁሱ መሰራት የተተወበት ምክንያት ቁሱ በበቀለበት አካባቢ ላይ ወተትና እርጎ በተፈላጊው መጠን ማግኘት አለመቻሉ እና የተገኘውን ወተት በዘመንኛ ቁሶች አገልግሎቱ መተካቱን የሚያስገነዝብ  ነው፡፡

**ትክየ፡-**በሽክላ ባለሙያዎች የሚሰራ ቁስ ነው፡፡ የቁሱን አሰራርና አገልግሎት በተመለከተ ወ/ሮ ገረዶ በጃበጅ እንዲህ ገልፀውታል፡፡

> እንግዲህ ትክየ ሳበጅ ጭቃ ያስፈልጋል፡፡ ያው የሸክላ አፈር ቆፍሬ ነው፡፡ ከዛማ ያው ካመጣሁ በኋላ አቦከዋለሁ፡፡ ጣህይቱ እንዳትመታኝ ጥላ ቦታ እወስዳለሁ፡፡ ከያ እሰራለኋ በሱ አደል እጀራዬ፡፡ የሚጀመረው ከታች ሲሆን እያሳደኩ እሄዳለሁ፡፡ አፍ ጠበብ ሆዱ ሰፍ አረገዋለሁ፡፡ መያዣ ይሰራል በእሳት ይተኮሳል፡፡ ለጥዋ ማህበርና ለሰርግ ንፍሮም እንዲሁም ስጋ ይቀቀልበት ነበር፡፡ አሁን እኳ እየጠፍ ነው (ቃ.መ.8/06 /09 ዋጮ )፡፡

የትክዬ ቁሶች ተቀዳሚ  አገልግሎት ስጋና ንፍሮ ለመቀቀያነት የሚውሉ ናቸው፡፡ በሰርግና ፅዋ ማህበር ላይ በትክዬ ቁሶች ስጋና ንፍሮ ይቀቀልባቸው ነበር፡፡  ቁሶቹ ማህበረሰቡ በሰርግና በፅዋ ማህበር ላይ ያላቸውን የአመጋገብ ሁኔታ ሲያመለክት ንፍሮውና ስጋው ደግሞ ኑሮኣቸውን የሚጠቁም ነው፡፡ ቁሶቹ የፈለቁበት አካባቢ የሚመረተው  ጥራጥሬ እንዴትና ለምን ጥቅም ላይ እንደሚውል ያስገነዝባል፡፡ በሌላ መልኩ በሰርግና በፅዋ ማህበር ላይ ንፍሮ እንደሚዘጋጅ ይጠቁማል፡፡ በአሁኑ ወቅት ቁሱ ፈላጊ ያጣበት ምክንያት ጥራጥሬውን ወደ ሌላ የምግብ አይነት ለውጠው በመጠቀማቸውና ቁሱ በዘመንኛ ቁስ ስለተተካ ነው ይላሉ፡፡

**መስመስያ፡-** በሸክላ ባለሙያዎች የሚሰራ ቁስ ሲሆን ስለ ቁሱ አገልግሎት በተመለከተ ወ/ሮ ክቡ እንዳለ እንደሚከተለው ገልፀዋል፡፡ ‹‹መስመስያማ ጠላ መጠጫ ነዋ፡፡ ያው በእሱ ይጠጣ ነበር አሁን የቆርቆር መጥቷል የበተስኪያን መጠጫ አይነት ነው እኮ ሲያዝ ደስ ይላል፡፡ በዛ ላይ ጠላው ሸጋ ነበር አቤት የገሌ ሚስት የምትጠምቀው ጠላ ይባል ነበር፡፡ እግር አለው አፉ ጠበብ ያለ ነው፡፡ በዛ ይጠጣ ነበር›› (ቃ.መ.11/06/09 ዋጮ ቀበሌ) ፡፡

ቁሱ በበቀለበት ማህበረሰብ ውስጥ መስመስያ ለጠላ መጠጫ የሚያገለግል ነው፡፡ ሳር ቤቶች ሲሰሩ በውስጥ ግድግዳ ላይ ቀጫጭን እንጨት ይሰካል፡፡ የእንጨቱ አገልግሎት መስመስያውንና መሰል ቁሶችን ለመስቀያ ነው፡፡ የመስመስያው የቁጥር ብዛት ይለያይ እንጂ በድሃም ሆነ በሀብታም ቤት ውስጥ ይገኛል፡፡ ቁሱ በማህበረሰቡ ውስጥ ደሃና ሃብታም በሚባሉ ሰዎች ቤት መገኘቱ ጠላ ሲዘጋጅ በአካባቢያቸው በተመጣጣኝ ዋጋ ወይም ደግሞ በማሳቸው ላይ የሚያመርቷቸውን የእህል አይነቶችን ተገልግለው የሚሰሩት  መሆኑን ይጠቁማል፡፡ በሌላ መልኩ ጠላ ባህላዊ መጠጣቸው መሆኑን የሚያመለክት ነው፡፡

**ጋውዝየ /ጉልቻ/** በሸክላ ባለሙያዎች ከሚሰሩ ቁሶች መካከል አንዱ ነው፡፡ የጋውዝየ አሰራርንና የቅርፁ መነሻ በተመለከተ ወ/ሮ እሸቴ ኩራዝ እንደሚከተለው ገልፀውታል፡፡

ድሮ የድንጋይ ነበር ጋውዝየው፡፡ ሶስት ድንጋይ ተደርጎ ይሰራ ነበር፡፡ ከያማ ድጋዩ አስቸገረ እየፈነዳ ነዋ እኛ አፈር አቡክተን ሰራን፡፡ ይኸው ይጠቀሙበታል ጋውዝየ የጌጥ ጋውዝየ አለ፡፡ የመስሪያም ጋውዝየ አለ፡፡ የጌጡ ጋውዝየ ለጌጥ ነው፡፡ እኛ የተለያየ እቃ እንሰራለን፡፡ አሰራሩ እንግዲህ አፈር ይቦካል፡፡ ከያ በእጅ ውስጡ ማጎድጎድ ጉጡ ይሰራለታል፡፡ በሸንበቆ ይላጋል፡፡ ከያ በእሳት ይለበለባል (ቃ.መ.9/05/09/ ቆላ ኑረና ቀበሌ)፡፡

የጋውዝየ /ጉልቻ/ ቁሱ አሁን የያዘውን ቅርፅ እንዴት ሊይዝ ቻለ? የሚለውን ጥያቄ ማንሳት አስፈላጊ ነው፡፡ ባለሙያዎቹ ጉልቻን ለመስራት መነሻ የሆናቸው ቅርፅ የድንጋይ ጉልቻ ነው፡፡ ከሸክላ አፈር ጉልቻን ሰርተው ለተጠቃሚው የማህበረሰብ ክፍል ከማድረሳቸው በፊት ማህበረሰቡ ሦስት ድንጋይ አራርቀው በመጎለት/በማስቀመጥ/ ቁሶቹ የምግብና መጠጥ ማብሰያ ቁሶችን የሚሸከም ነበር፡፡ በአሁኑ ወቅትም በተወሰነ መልኩ አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛል፡፡ የድንጋዩ ጉልቻ በተደጋጋሚ ሲግል እየፈነዳ ሲያስቸግራቸው የሸክላ ባለሙያዎች ከተመረጠ አፈር አሁን ያለውን ጉልቻ ሊሰሩት ችለዋል፡፡

በማህበረሰቡ ውስጥ ሁለት አይነት ጋውዝየ /ጉልቻ/አለ፡፡ እነሱም፡- ቁሶች የሚሸከምና የጌጥ ጋውዝየ በሚል ባለሙያዎቹ ይከፍሉታል፡፡ የጌጥ ጋውዝየ/ጉልቻ/ በእልፍኝ ቤት ውስጥ ለጌጥ በተሰራው የጭቃ ምድጃ ላይ የሚቀመጥ ሲሆን ቁሶቹን የሚሸከመው ጉልቻ ደግሞ እሳት ጎን ተጎልቶ የማብሰያ ቁሶችን የሚሸከሙ ናቸው፡፡ ማህበረሰቡ ጉልቻን የቤት ውስጥ ውበት ማጎናፀፊያነት ይጠቀሙበታል፡፡ የጌጥ ጉልቻ ቤታቸው ላይ በስርዓት ያስቀመጡ እማወራዎች የቤታቸውን ውበት የሚጠብቁ ስለሆኑ ባለሙያ የሚል ክብር ይሰጣቸዋል ይላሉ፡፡

**ድፊት፡-**ስለ ቁሱ አሰራርና መነሻ ቅርፅ በተመለከተ ወ/ሮ ቡላል ሶሪ እንደሚከተለው ገልፀዋል፡፡ ‹‹ድፊት አሁን ፈላጊው በዝቷል፡፡ ያው ሸክና አይተን ሰራን፡፡ ሸክና ባፉ ሲደፋ አደል የሚቆም፡፡ ጭቃ ተቦክቶ ነው እሚሰራ ትንሽ ጭቃ ይበቃል፡፡ መጠኑ እኮ ትንሽ ነው ውስጡን ጎርጎድ አደርጋለሁ፡፡ አንገት አበጃለሁ ከያ ጆሮ የለውም፡፡ እሳት እለበልባለሁ አረቂ የሚሰሩ ሴቶች ይገዛሉ›› (ቃ.መ 28/07/09 ዋጮ ቀበሌ)፡፡

ድፊት የሸክላ ባለሙያዎች የጥበብ ውጤት ነው፡፡ አሁን የያዘውን ቅርፅ ይዞ እንዲሰራ ያስቻለው እግር የሌለው ሸክናን መነሻ በማድረግ ነው፡፡ ሸክና ከቅል ተክል የሚገኝ ሲሆን በአካባቢው ላይ ይበቅላል፡፡ ሸክና ለጠላና ውሃ መጠጫነት የሚያገለግል ቁስ ነው፡፡ ቁሱ

ከተጠጣበት በኋላ በአፉ በመድፍት ያስቀምጡታል። በአፉ የሚደፋበት ምክንያት በአብዛኛው የሚቆምበት እግር ስለሌለው እንዳይሰበርና ቆሻሻ እንዳይገባበት ለማድረግ ነው።

የሸክላ ባለሙያዎች እግር የሌለውን ሸክና መነሻ ቅርፅ በማድረግ ድፋትን ልንሰራ ችለናል ይላሉ። ድፋት አረቄ በሚወጣበት ወቅት በእንስራ አፍ ላይ በመግጠም እንፍሎት እንዳይወጣና መሳቢያውን ለመያዝ የሚያገለግል ነው። ድፋት የሚለውን ስያሜም ያገኘው እንስራ አፍ ላይ ስለሚደፍ ነው።

***ዋዳት /ሸሸት/*** ስለቁሱ አሰራርና መነሻ ቅርፅ በተመለከተ ወ/ሮ ገረዴ በጃበጅ እንደሚከተለው ገልፀዋል። ‹‹ቆሪ አይተን አፈር አቡክተን ሸሸትን ሰራን። አሰራሩማ ጭቃውን አቦካና ቆሪው ላይ አደርጋለሁ። ንጡህ ጨርቅ መሃል በማረግ ነው። ከዛማ በቆሪው መልክ እጠፈጥፈዋለሁ ከዛ ደረቅ ካለ ጨርቁን አላቅቀዋለሁ። በዚች ቢላ እፍቀዋለሁ። ከዛ እሳት ይተኮሳል። አረቄ ሰሪ ውሃ በማረግ ኮዳ ያኖሩበታል። ጠብ አያረግም›› (ቃ.መ. 28/07/09 ዋጮ ቀበሌ)።

ሸሸት፡- ከሸክላ አፈር የሚሰራ ቁስ ነው። አሁን ይዞት ለሚገኘው ቅርፅ መነሻ የሆነው የቆሪ ቅርፅ ነው። ቆሪ ከእንጨት ተጠርቦ የሚሰራ ቁስ ሲሆን ከብቶች ውሃ የሚጠጡበት ነው። የሸሸት ቁስ አገልግሎት አረቄ በሚወጣበት ወቅት ሸሸቱን ውሃ በመሙላት የአረቄን ኮዳ የሚይዝና እንዲቀዘቅዝ የሚያስችል ነው።

***እንስራ /ሻማ/*** በሸክላ ባለሙያዎች የሚሰራ ቁስ ነው። የቁሱን አሰራርና መነሻ ቅርፅ በተመለከተ ወ/ሮ ገረዴ ታዴ እንዲህ ገልፀውታል። ‹‹እንስራ የሰራነው ጎታን አይተን ነው። የጭቃ ጎታ ነዋ። አንገቱ ጠባብ ነው። የሸክላ አፈር ይፈጫል። ከያ ይቦካል። መበጀቱ የሚጀምረው ከቂጡ ነው። ሆዱን አጎደጉዳለሁ። ከያማ አገቱን አበጀዋለሁ። በመወጠኛ አበጃለሁ። ጆሮ አበጃለሁ ከያ እተኩሰዋለኍ። እቃው ፈላጊ አለው›› (ቃ.መ. 10/06/09ዓ.ም ዋጮ ቀበሌ)።

የሸክላ ባለሙያዎች እንሰራን ሲሰሩ መነሻ ያደረጉት ቅርፅ የጭቃ ጎታን ነው። የአካባቢው ማህበረሰብ ከማንኛውም የአፈር አይነት የጭቃ ጎታን ሰርተው እህልና ዱቄት ያስቀምጡበታል። ይህን የተመለከቱ የሸክላ ባለሙያዎች ከተመራጭ አፈር እንስራን ለመስራት ችለዋል። እንስራ ውሃ ለመያዣነት ሲያገለግል ሲነቃ ደግሞ ዱቄት ይያዝበታል። ቁሱ አረቄ በሚወጣበት ወቅት የሚያስፈልጉ የእህል አይነቶች ተፈጭተው እንስራው ውስጥ ይጨመራል። አረቄውም እየተጣራ ወደ ኮዳው ውስጥ ይገባል።

የድፊት፣እንስራና ሸሸት ቁሶች በአሁኑ ወቅት ለምን በብዛት ይሰራሉ? የሚለውን ጥያቄ ማንሳት ተገቢ ነው። ይህ የሚያሳየው በአሁኑ ወቅት አረቂ እያወጡ የሚሸጡ ሴቶችንና የሚጠጡ ሰዎችን ህይወት ያሳየናል። አረቄ ማውጣትና መሸጥ በማህበረሰቡ አመለካከት አነስተኛ ኑሮን የሚገፉ ሰዎች የሚሰሩት ስራ ነው። ሀብታም የሆኑ ሰዎች አረቄ አውጥተው ሳይሆን ገዝተው በቤታቸው ውስጥ ያስቀምጣሉ። አረቄ በሚወጣበት ወቅት በእሳት መለብለብ ስላለው ተመራጭ ስራ አይደለም ይላሉ።

## 4.2. በሸክላ ቁሶችና በሰው ልጅ መካከል ያለው ተፈጥሯዊ ተዛምዶ

የሸክላ ቁሶች የበቀሉበትን ማህበረሰብ የህይወት ፍልስፋና ከማሳየት ባሻገር በሰውና ቁሶቹ መካከል  ተፈጥሯዊ ተዛምዶ አላቸው።

ሊቀ መዘምራን ሞገስ ዕቁበ ጊዮርጊስ መጽሃፈ ሥነ ፍጥረት በሚለው የኦርቶዶክስ ክርስትና ሃይማኖታዊ መፅሃፍ ላይ የሚከተለውን ሃሳብ ገልፀዋል። ‹‹እግዚአብሔር እሁድ ቀን በመጀመሪያው ሰዓተ ሌሊት ፬ቱ ባህሪያት ፰ኛ ጨለማን እምኃ አልቦ ኃበቦ /ካለመኖር ወደ መኖር/አምጥቶ ፈጠረ። ፬ ባህሪያት የተባሉትም ውሃ ፣መሬት፣ነፍስና እሳት ናቸው›› የእሁድ ስነፍጥረት (1987፣13)።

የሸክላ ቁሶች በሚሰራበት ወቅት የሚያስፈልጉ ነገሮችን በተመለከተ ወ/ሮ ዋጋነሽ ኢታሞ እንደሚከተለው ገልፀዋል። ‹‹ያው ሸህላ ሲበጅ በባዶው እመዋል። ደህናው አፈር ይቆፈራል። በውሃ ማቡካት፣እቃውን በንፍስና ጠሃይ ማድረቅ ወዳውም በሳት መተኮስ ነው። እንግዲህ እንዳ ነው። የሰው ነፍስያ በአፈር፣በውሃ፣ በነፍስና በሳት ነው። ብለው የለ መሪጌታ። እኛ ስንሰበር እደ ሸህላ ነን አችል›› (ቃ.መ.14/08/09 ቆላ ኑረና ቀበሌ)።

የሸክላ ቁስ ሲሰራ የሸክላ አፈር፣የሸክላ አፈሩን ማቡኪያ ውሃ፣የተሰራውን ቁስ ማድረቂያ ንፍስ /ፀሀይ/ እንዲሁም ቁሱ ውበት እንዲኖረውና እንዲጠነክር ለማስቻል ደግሞ በእሳት መለብለብ ያስፈልጋል። ይህ የሚያሳየው የሸክላ ቁሶችም ሲሰሩ አፈር፣ውሃ፣ነፍስና እሳት የሚያስፈልጉ መሆናቸውን ነው።

የሰው ልጅ አፍ፣አንገት፣ሆድ፣ጆሮና እግር የሚባል የሰውነት ክፍል መጠሪያ አለው። በተመሳሳይ ከሸክላ የሚሰሩ ቁሶች በዚህ ስያሜ ይጠራሉ። ይህ የሚያሳየው በሸክላ ቁሶችና ሰዎች መካከል  ቁርኝት መኖሩን ነው።

## 4.3. የሸክላ ባለሙያዎች ለመስሪያነት የሚጠቀሙባቸው ቁሶች ስምና ተግባር

ቀይና ዋልካ አፈር፦- የተለያዩ የአፈር አይነቶች ቢኖርም ለሸክላ ስራ ተመራጭ ከሚባሉ የአፈር አይነቶች ውስጥ ቀይና ዋልካ አፈር ይገኙበታል፡፡ ከቀይ አፈር ከሚሰሩ ቁሶች ውስጥ ድፋት፣ደንጋሳ፣ጀበና፣ሸሸትና ጣባ ይገኙበታል፡፡ በሌላ በልኩ ከዋልካ አፈር ከሚሰሩ ቁሶች ውስጥ ደግሞ ገንቦ፣ጉልላትና ሻማ ይጠቀሳሉ፡፡

የድንጋይ ወፍጮ፦- ይህ የወፍጮ አይነት መጠኑ ትንሽ ሲሆን ለቁሶች መስሪያ የሚያገለግለውን የሸክላ አፈር ለመፍጫነት የሚውል ቁስ ነው፡፡

ትንሹ ማሰሮ፦-ለሸክላው አፈር ማቡኪያና ማለስለሻ ውሃ የሚቀርብበት ቁስ ነው፡፡

መወጠኛ፦- ቁሶችን በተለያየ መጠንና ቅርፅ ለመስራት ሲፈልጉ የቁሱን ቅርፅ ለማውጫ የሚያገለግል ትንሽ ቁስ ነው፡፡

የተሰነጠቀ ሸንበቆ፦-በተለያየ መጠንና ቅርፅ የሰሯቸውን ቁሶች በመላግ የቁሶቹን ውፍረትና ስስነት ለማመጣጠን የሚያስችል ነው፡፡

ቁራጭ የአቡጀዴ ጨርቅ፦- ቁሶቹ ጥንካሬንና ውበትን በጥምርታ እንዲያገኙ ለማድረግ በውሃ እየተራሰ ለማሸት የሚያገለግል ነው፡፡

ቢላዋ፦-በተለያየ መጠንና ቅርፅ የተሰሩ ቁሶችን በመፈቅፈቅ ጌጥ ለማውጫነት የሚጠቀሙበት ነው፡፡

## 4.4. የሸክላ ስራ ደረጃዎች

በሸክላ ባለሙያዎች የሚሰሩ ቁሶች ከቁስነት ደረጃ የሚደርሱት ብዙ ሂደቶችን በማለፍ ነው፡፡ የሸክላ ስራ ደረጃዎችን በተመለከተ Copper(1981፣25)፣Noble(1966፣15)እና Bricks(1967፣12) ቅርፅ የማውጣት ተግባር /Forming/፣የማስጌጥ ተግባር /Decorating/ እና የመተኮስ ተግባር/Firing/ መሆናቸውን ጠቁመዋል፡፡ በመስክ ምልከታዬ ወቅት ግን የሸክላ አፈር የመቆፈር ተግባር እና የሸክላ አፈርን ለስራ የማዘጋጀት ተግባር የሚሉትን ለመመልከት ችያለሁ፡፡ እያንዳንዱ የአሰራር ሂደት ውስጥ የባለሙያዎቹን ጉልበት፣ጊዜ፣ገንዘብና ጥበብ የሚጠይቅ ነው፡፡ ሂደቶቹ ተያያዥነት ያላቸው ናቸው፡፡ የሸክላ ስራ ደረጃዎችን ከክስታኔ ማህበረሰብ ጋር ላስተሳስረው የፈለኩት የአሰራር ደረጃዎቹ ያላቸውን ተወራራሽነት ለመጠቆም እንጂ የጥናቴ ትኩረት በሆነበት አካባቢ ላይ ብቻ ያለ ነው ለማለት አይደለም፡፡

### 4.4.1. የሸክላ አፈርን የመቆፈር ተግባር

የሸክላ ባለሞያዎች ቁሶችን ለመስራት ሲያቅዱ ተቀዳሚው ተግባር የሸክላ አፈርን የመቆፈር ተግባር መከወን ነው። በዚህ ወቅት ለመቆፈሪያነት የሚያገለግለው መሳሪያ መረጣ ትኩረት የሚሰጠው ጉዳይ ነው። አፈሩን ለመቆፈሪያና ለመያዣ የሚያገለግሉ ቁሶችን በመያዝ ወደ ቦታ ያመራሉ።

በሶስቱም ቀበሌዎች ውስጥ የሸክላ አፈሩ የሚገኘው ከባለሙያዎቹ መኖሪያ በርቀትና ተራራማ አካባቢ ላይ በመሆኑ ለመረዳዳት በህብረት የሚቆፍሩ እንዳሉ ሁሉ በግላቸውም የሚቆፍሩ አሉ። ባለሙያዎቹ በቡድን የሸክላ አፈር የሚቆፍሩት የሚከተሉት ቅድመ ሁኔታዎች ሲመቻቹ ነው። እነሱም፡- ባለሙያዎቹ ጎረቤታሞች ከሆኑ፣ እርስበርሳቸው የሚግባቡና በማህበራዊ ህይወታቸው ውስጥ የሚተጋገዙ ከሆነ ነው።

በሱተን ዙሪያ ቀበሌ የሚገኙ የሸክላ ባለሙያዎች በቁጥር ስድስት ሲሆኑ በአንድ አካባቢ የሚኖሩና መልካም ማህበራዊ ግንኙነት ያላቸው በመሆኑ በወር ሁለት ጊዜ ይቆፍራሉ። የሚቆፍሩት ከሰንበት ቀንና ከወር ባዕላት ውጪ ነው። በእለተ እሁድ የማይቆፍሩት ክርስቲያን ስለሆኑ እሁድ ደግሞ በክርስትና ሃይማኖት የሰንበት ቀን በመሆኑ እሱን ለማሰብ ነው። ለአፈሩ የሚከፈል ዋጋ የለም ምክንያቱም የሸክላው አፈር የሚገኝበት ቦታ የወል መሬት ስለሆነ ነው።

በቆላ ኑረና የሚኖሩ የሸክላ ባለሙያዎች በቁጥር ስምንት ናቸው። ባለሙያዎቹ የመኖሪያ አካባቢያቸው በተወሰነ መልኩ የተራራቀ በመሆኑ የሸክላውን አፈር የሚቆፍሩት በሚመቻቸው ቀን በግላቸው ነው። ባለሙያዎቹ የሸክላውን አፈር የሚቆፍሩት እያንዳንዳቸው በወር ሃምሳ ብር ለባለ መሬቱ በመክፈል ነው። በተመሳሳይ በዋጮ ቀበሌ የሸክላ ባለሙያዎች በቁጥር አስር ሲሆኑ በግላቸው የመቆፈሩን ተግባር ይከውናሉ። ለሸክላው አፈር እያንዳንዳቸው በወር ሰላሳ ብር ለመሬቱ ባለቤት/ ግለሰብ /ይከፍላሉ። ለሸክላው አፈር የሚከፈለው ገንዘብ እንደ ወቅቱ የሚጨምርበት ሁኔታ አለ።

### 4.4.2. የሸክላ አፈርን ለስራ የማዘጋጀት ተግባር

የሸክላ ባለሙያዎች ለቁሶች መስሪያ የሚያገለግለውን አፈር ካመጡ በኋላ ያለውን ሂደት የሚቃኝ ነው። ለሸክላ መስሪያ የሚያገለግለው አፈር ፀሃይ ላይ ከተሰጣ በኋላ በወፍራም

እንጨት በመደብደብ እንዲደቅ ይደረጋል፡፡ ለሸክላ አፈር መፍጫነት በተዘጋጀው ትንሽ ወፍጮ ላይ ይፈጫል፡፡

የተፈጨውን የሸክላ አፈር ለማቡኪያነት በተዘጋጀው ቁስ ላይ በማድረግ ከላይ ውሃ እየተጨመረበት እንደ ጤፍ ዱቄት በእጅ ይታሻል፡፡ የሚቦካው አፈር መጠኑ ብዙ ከሆነ ደግሞ በእግር እየታሸ ለአንድ ሰዓት ያህል ይቆያል፡፡ አቦካኩም አፈርና ውሃውን ተመጣጣኝ በማድረግ ነው፡፡ ውሃ ሲበዛ ከላይ የሸክላ አፈር ይደረጋል፡፡ የሸክላው አፈር በዝቶ የመድረቅ ሁኔታ ሲያመጣ ደግሞ ውሃ እየተደረገበት የማመጣጠን ስራ ይሰራል፡፡

## 4.4.3. ቁሶችን በተለያየ መጠንና ቅርፅ የመስራት ተግባር

የሸክላው አፈር ቁሶችን ለመስራት አመቺነት ባለው መልኩ ከተቦካ በኋላ ቀጣዩ ተግባር በንፁህ ጨርቅ ጭቃውን ወደ ጥላ ቦታ ይዞ መሄድ ነው፡፡ በማስከተልም ቁሶቹን በተለያየ መጠንና ቅርፅ የመስራት ተግባር ይጀመራል፡፡ የቁሶቹ የተወሰነ ክፍል ከተሰራ በኋላ በፀሃይና ንፋስ ጭቃው መጠጥ እንዲል ይደረጋል፡፡ በማስከተልም ቁሱ እየተቀጠለበት ተጨማሪው ክፍሉ ይሰራል፡፡ የቁሶቹ ውፍረትና ስስነትን ለማመጣጠን በተሰነጠቀ ሸንበቆ ይላጋል፡፡ የተፋቀው ቁስ በቁራጭ አቡጀዴ ጨርቅ ውሃ እየተራሰ በማሸት ልስላሴን እንዲጎናፀፍ ይደረጋል፡፡ በሌላ መልኩ በፀሀይና ንፋስ መጠጥ ያለውን ቁስ ለመፈቅፈቅ ቢላዋን ጥቅም ላይ ያውሉታል፡፡ በማስከተል ሌላኛው የቁሱ ክፍል ይታከልበታል፡፡ ቁሶቹን ሲሰሩ ቅርፁን የሚያወጡበት መወጠኛ እቃ ይጠቀማሉ፡፡

የቁሶቹ መጠንና ቅርፅ በማህበረሰቡ ውስጥ ምን ትዕምርት አላቸው? ቁሶቹ አሁን የያዙትን ቅርፅ እንዴት ሊይዙ ቻሉ? ባለሙያዎች በቁሶቹ ላይ የተለያዩ ቅርፆችን የሚያክሉት ለምንድን ነው? ባለሙያዎቹ ቁሶቹን በተለያየ ቅርፅና መጠን የሚሰሩት ከምን አስተሳሰብ የመነጨ ነው? የቁሶቹ መጠንና ቅርፅ የማህበረሰቡን የህይወት ፍልስፍና በምን መልኩ ያሳያሉ? አዳድስ ቁሶችን ሲሰሩ መነሻ የሚያደርጉት ቅርፅ ምንድን ነው? ተጠቃሚዎቹ በተለያየ መጠንና ቅርፅ የተሰሩ ቁሶችን የሚገለገሉት ከምን አስተሳሰብ በመነሳት ነው? የሚሉትን ጥያቄዎች ለመመርመር የሚያስችል ነው፡፡

## 4.4.4. ቁሶቹን በተለያየ ቦታ ላይ የማስጌጥ ተግባር

ባለሙያዎቹ ቁሶቹን በተለያየ መጠንና ቅርፅ ከሰሩ በኋላ ያለውን ሂደት የሚያሳይ ነው፡፡ የሸክላ ቁሶቹ እርጥበታቸው መጠጥ ማለቱ ከተረጋገጠ በኋላ በቢላዋ ጫፍ በተጠቃሚው

እይታ አስደሳች የሆነ ቅርፅ ያወጡለታል፡፡ ቁሶቹ ላይ የሚታከሉ ጌጣጌጥ የማህበረሰቡን ባህል መነሻ በማድረግ የሚሰሩ ናቸው፡፡ በባለሙያዎቹ የሚሰሩ ቁሶች ቅርፃቸው ከጌጥነት ባለፈ የማህበረሰቡን የህይወት ፍልስፋና የሚገልፁ ናቸው፡፡

### 4.4.5. ቁሶችን የመተኮስና የማሰር ተግባር

ቁሶቹ ተሰርተው አስፈላጊው ጌጣጌጥ በተፈላጊው ክፍል ላይ በወገ ከተደረገ በኋላ ቀጣዩ ተግባር ቁሶቹን በእሳት መተኮስ ነው፡፡ የሸክላ ቁሶቹ በቤት ውስጥና ከቤት ውጭ በተዘጋጀው ቦታ ላይ በእሳት የመተኮሱ ተግባር ይከናወናል፡፡ የቁሶቹ በእሳት የመለብለብ ሂደት በመጀመሪያ ቀጫጭን ደረቅ እንጨት ቁሶቹን ለመለብለቢያነት በተዘጋጀው ቦታ ላይ በስርዓት ይዘረጋል፡፡ ቀጥሎም ደረቅ ሳርና ቅጠል ይጎዘጎዛል፡፡ በማስከተልም የተሰሩት ቁሶች በአግባቡ እሳሩ ላይ ይኮለኮላሉ፡፡ ከቁሶቹ በላይ እርጥብ ቅጠል ይደረግና ይሸፈናል፡፡ እሳቱን በማቀጣጠል ቁሱ ይለበለባል፡፡ በመቀጠል ቁሶቹን የማሰር ተግባር ይከወናል፡፡

## 4.5. የሸክላ ቁሶች ጠቀሜታ

### 4.5.1. ማህበራዊ ጠቀሜታ

የሸክላ ባለሙያዎች በተለያየ መጠንና ቅርፅ ቁሶችን ሲሰሩ ለተጠቃሚው ማህበረሰብ ዘርፈ ብዙ ፋይዳ ይሰጣሉ፡፡ የቁሶቹን የአሰራር ጥበብና ያዘሉትን ሃሳብ በአግባቡ ለመገንዘብ ደግሞ በየዘውጉ ማደራጀት ተገቢ ነው፡፡ እኔም ከቁሶቹ ባለቤቶች ጋር በመሆን በሚከተለው መንገድ ከፍለናቸዋል፡፡

#### 4.5.1.1. ፈሳሽ ነገሮችን ለማዘጋጃነትና ለማቅረቢያነት የሚያገለግሉ ቁሶች

የሸክላ ባለሙያዎች ለተለያዩ አገልግሎት የሚውሉ ቁሶችን ይሰራሉ፡፡ ፈሳሽ ነገሮችን ለማዘጋጃነትና ለማቅረቢያነት ከሚውሉ ቁሶች መካከል የሚከተሉት ይገኙበታል፡፡ እነሱም፡- ኩሮ፣ጀበና፣ገንቦ፣መስመስየና ክርን ተጠቃሽ ናቸው፡፡ ባለሙያዎቹ እነዚህን ቁሶች በተለያየ መጠንና ቅርፅ በመስራት ለተጠቃሚው ማህበረሰብ ያደርሳሉ፡፡

#### 4.5.1.2. ምግብ ለማዘጋጃነትና ለማቅረቢያነት የሚያገለግሉ ቁሶች

በሸክላ ባለሙያዎች ከሚሰሩ ቁሶች መካከል ለምግብ ማዘጋጃና ማቅረቢያ የሚሆኑ ቁሶች አሉ፡፡ እነሱም፡-ትክዬና ነክብ የሚሉት ተጠቃሽ ናቸው፡፡ ቁሶቹ የተለያየ መጠንና ቅርፅ

ያላቸው በመሆናቸው መጠኑ ብዙ ወይም ትንሽ የሆነ ምግብ ለማዘጋጃና ለማቅረቢያ የሚውሉ ቁሶች ናቸው፡፡

### 4.5.2. የሸክላ ቁሶች ባህላዊ አገልግሎት

የሸክላ ቁሶች ለተጠቃሚው ማህበረሰቡ የእለት ከእለት ተግባራትን ከመከወኛነት ባሻገር በአንድ ዘመን የነበረና ያለ የማህበረሰብ ክፍል የአኗኗር ዘይቤን፣ወግ፣ፍልስፍና፣ማንነት፣ ማህበራዊ ደረጃና ባህልን ለተተኪው ትውልድ በማሳወቅ በኩል አበርክቶ አላቸው፡፡ በዚህ መነሻ እሳቤ የሸክላ ቁሶች በማህበረሰቡ ውስጥ ያላቸው ትዕምርት እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

#### 4.5.2.1. ሀብታምነትን የሚያመለክቱ የሸክላ ቁሶች

በሸክላ ባለሙያዎች የሚሰሩ ቁሶች ከሚሰጡት አገልግሎት አንፃር የተገልጋዮቹን የሀብት መጠን መጠቆም አንዱ ነው፡፡ በማህበረሰቡ ውስጥ ሀብታም በሚባሉ ሰዎች ቤት ከሚገኙ ቁሶች መካከል የሚከተሉት ይገኙበታል፡፡ እነሱም፡- ጥወ፣ነክብ፣ጉልላትና ኩሮ ናቸው፡፡

#### 4.5.2.2. ድህነትን የሚያመለክቱ የሸክላ ቁሶች

በማህበረሰቡ ውስጥ አረቄ የማውጣት ስራ በዝቅተኛ ኑሮ ውስጥ ያሉ ሴቶች ተግባር እንደሆነ ይገልፃሉ፡፡ የሸክላ ባለሙያዎችም ለአረቄ ማውጫ የሚውሉ ቁሶችን ይሰራሉ፡፡ ሸሸት፣ ድፊትና የአረቄ እንስራ በሌላ መልኩ የእንጨቡዬ ቁሶች የተገልጋዮችን ድህነት የሚጠቁሙ ናቸው፡፡ እነዚህ ቁሶች አብዛኛውን ጊዜ የሚገኙት የሀብት መጠናቸው አነስተኛ በሆነ የማህበረሰብ ክፍል ቤት ውስጥ ነው ፡፡

### 4.5.3. ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ

የሸክላ ባለሙያዎች ቁሶችን በተለያየ መጠንና ቅርፅ በመስራት ለተጠቃሚው የማህበረሰብ ክፍል ያቀርባሉ፡፡ ቁሶቹን ለሚያበጁቸው ባለሙያዎች እንዲሁም ለተጠቃሚው የማህበረሰብ ክፍል አገልግሎት ይሰጣሉ፡፡ ለባለሙያዎቹ የሰሩትን ቁሶች በመሸጥ የራሳቸውንና ቤተሰቦቻቸውን ህይወት ለመምራት የሚያግዝ ገንዘብ ያገኙበታል፡፡ ለቁሶቹ ተጠቃሚዎች ደግሞ በሚፈልጉት መጠንና ቅርፅ ቁሶቹን በትዕዛዝ አሰርተው መጠቀም መቻላቸው ተጠቃሽ ነው፡፡ የሸክላ ቁሶችን ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ በማስመልከት ወ/ሮ ምንጩ ረጋሳ እንደሚከተለው ገልፀዋል፡፡ ‹‹እኔ ሁለት ወንድና ሶስት ሴት ልጆቼን የማሳድገው ሸህላ በመሸጥ ነው፡፡ ሽያጩ ርካሽ ቢሆንም ያው እሰራለሁ፡፡ ያው የሸህላ ቁሶቹን በየሳምንቱ

ባልሸጥ ልጆቼን ምን አቃምሳቸው ነበር፡፡ እንኳን ሳይሸጥ ተሸጦም ጠብ የሚል ብር አልተገኘም፡፡ ያው በአፈር ነው የምበላው መልሶም አፈር ይበላኛል›› ቃለ መጠይቅ (5/06/2009 ዓ.ም ቆላ ኑረና)፡፡

## 4.6. በሸክላ ስራ ላይ የባለሙያዎቹ ፆታዊ ተሳትፎ

የጥናቴ ትኩረት በሆነባቸው ቀበሌዎች ሁሉ የሸክላ ስራ የሚከውኑት ሴቶች ናቸው፡፡ የሸክላ ስራ በሴቶች የሚከናወንበት ምክንያት በተመለከተ ወ/ሮ እሸቴ ኩራዝ እንዲህ ገልፀውታል፡፡

> ወንድ የሴት ስራ አይሰራ ነውር ነው፡፡ ሸህላ እምናበጅ ሴቶች ነን መፍጨት ማቡካት ወንድ አይሰራ እኛ እህል ስለምንፈጭና ስለምናቦካ እናውቀዋለን፡፡ እቃው እኛ ነን ቤት እንዲምርና ለትካር የምናውል፡፡ ወንድ ጭቃ አቡክቶ አይሰራም፡፡ እኛ ሸህላዎቻችንን እብስብስ እያደረግን ቅልጥፍጥፍ አርገን እናበጃለን፡፡ መጠራረግ ወንድ መቼ ያቀላጥፋል፡፡ ወንድ በባህሉ ነውር ነው (ቃ.መ.5/06/09 ቆላ ኑረና ቀበሌ)፡፡

የሸክላ ስራ በሴቶች የሚከናወን ተግባር ነው፡፡ የሸክላ ስራ በሴቶች የሚሰራው ለምድን ነው? የሚለውን ጥያቄ ማንሳት ተገቢነት አለው፡፡ በማህበረሰቡ ውስጥ የሴትና ወንድ ተግባር የሚል የስራ ክፍፍል አለ፡፡ በሸክላ ስራ ላይ የሴቶች ሚና ከፍተኛ የሆነበት ምክንያት በባለሙያዎቹ የሚሰሩ ቁሶች ከቤት ውስጥ ስራ ጋር ስለሚያያዙ ነው፡፡ የሸክላ ቁስ ሲሰራ አፈር መፍጨት፣ማንጓለልና ማቡካት የሚባሉ ሂደቶች አሉት፡፡ በተመሳሳይ ሴቶች የእንጀራ እህል ለማዘጋጀት እህል ማንጓለል፣መፍጨትና ማቡካት የሚባሉ ሂደቶችን ማለፍ ይጠይቃል፡፡ በሁለቱ ተግባራት መካከል ተመሳሳይነት ይታይበታል፡፡ መፍጨትና ማቡካት በማህበረሰቡ ባህል ሴቶች የሚተገብሩት ተግባር ስለሆነ ነው፡፡

በሌላ መልኩ በባለሙያዎቹ የሚሰሩ ቁሶች አብዛኛዎቹ በቤት ውስጥ ለምግብ፣መጠጥ ማዘጋጃነትና ማቅረቢያነት የሚያገለግሉ ቁሶች ናቸው፡፡ በማህበረሰቡ ባህል ደግሞ ምግብና መጠጥ የማዘጋጀትና ማቅረብ ተግባር በአብዛኛው የሚተገበረው በሴቶች አማካኝነት መሆኑ ሌላኛው ተጠቃሽ ምክንያት ነው፡፡

ከዚህም በተጨማሪ የሸክላውን አፈር ከመቆፈሩ ተግባር በስተቀር ብዙ ጉልበት የሚጠይቅ ተግባር ባለመሆኑና ፀሃይ ሳይመታቸው ስለሚሰሩ ተመራጭ ያደርጉታል፡፡ የሸክላ ስራ ከጭቃ ማድበልበል ጋር የተያያዘ በመሆኑ የእጅ ቅልጥፍና የሚጠይቅና ጌጣጌጥ

የሚደረግበት ስራ በመሆኑ ምርጫችን ነው ይላሉ፡፡ በዚህ መነሻ ምክንያት ሴቶች እናታቸው የምትሰራውን ቁስ እየተመለከቱ እንደ እድሜአቸውና ግንዛቤአቸው መጠን ይሰራሉ፡፡ ወንዶች ግን የሸክላ አሰራርን እንዲለምዱ አይደረጉም ይልቁንም አባቶቻቸው የሚሰሩትን ተግባር እንዲለምዱ ይደረጋል፡፡

## 4.7. የሸክላ ባለሙያዎች እምነት

የሸክላ ባለሙያዎች አደይ ሲፈነዳና ከዘራቸው ውስጥ ሰው ሲሞት የሚነሳባቸው መንፈስ አለ ይላሉ፡፡ ይህን መንፈስ ማህበረሰቡ የ‹ሚየት› መንፈስ እያሉ ይጠሩታል፡፡ አደይ መፈንዳት ሲጀምር መንፈሳቸውም አብሮ ይነሳባቸዋል ይላሉ፡፡ በዚህን ጊዜ ስራቸውንና ቀያቸውን ለቀው ወደ ሌላ ቀበሌ ለልመና በጋራ ይዞራሉ፡፡ ማህበረሰቡም ቤት ያፈራውን ነገር ይሰጧቸዋል እንጂ አይከለክሏቸውም፡፡ ካልሰጠን የእነሱ መንፈሱ በልጆቻችን ላይ ያርፍል ብለው ያምናሉ፡፡ እነሱም የተሰጡትን ነገር ይቀበላሉ እንጂ አነሰ በዛ አይሉም፡፡ መስቀል በዋለ ቅዳሜ የአዳብና በዓል ሲከበር በጋራ ሆነው ገበያውን ሶስት ጊዜ ይዞራሉ፡፡ በማስከተልም ክብ ሰርተው የራሳቸውን ዘፈን ይዘፍናሉ፡፡ ከበሮ ይዘው ይጨፍራሉ፡፡ ከእነሱ ዘር ውጪ አይቀላቀላቸውም ይላሉ፡፡ በዚያን ወቅት የሚናገሩትን ልዩ ንግግርን ከእነሱ ዘር ውጪ የሚያውቀው ሰው የለም፡፡ ማህበረሰቡ ንግግራቸውን ‹‹የሚየት ቋንቋ›› በማለት ይጠሩታል፡፡ ከጥቅምት አምስት ቀን በኋላ ግን ልዩ ንግግር /argot/ አይጠቀሙም ይላሉ፡፡

ቀጭን ቡራቡሬ ዘንግ ይይዛሉ፡፡ በበትሩ አናት ላይ እና ፀጉራቸው ላይ አበባ ይሰካሉ፡፡ በጋራ ይሄዳሉ፡፡ የተወሰኑት ለምነው ያመጡትን ለሌላኞዎቹ ያካፍላሉ፡፡ የሚየት መንፈስ በዘር ይተላለፍል ይላሉ፡፡ አንዱ ሲሞት በሌላኛው ላይ ያርፋል፡፡ ከዘር ሀረግ ውጪ ቢሆንም ሄዶ ያርፋል ፡፡ እነሱን በሚያስተናግዳቸውና በሚቀርባቸው ሰው ላይ ያርፍል ይላሉ፡፡ ሴትና ወንድ አይለይም፡፡ በዘር ሀረጋቸው ውስጥ እናትና አባት የማይወዷቸው ልጆች ካሉ በእነሱ ላይ መንፈሱ አያርፍም ይላሉ፡፡

በሌላ መልኩ ከሸክላ ባለሙያዎች ዘር ውስጥ ሰው ከሞተ ማንም ሰው ሳይነግራቸው ይሰባሰባሉ፡፡ በዚህ ወቅት ህፃን ልጅ እንኳ ቢይዙ ሊጥሉት ይችላሉ፡፡ ያለተ ፍታት ተደርጎ እንዲቀበር ግብር ይሰጣቸዋል፡፡ ግብራቸውን ካገኙ በኋላ ከአካባቢው ይርቃሉ፡፡ ግብር ካልተሰጣቸው ግን አስከሬን አይሰጡም ይላሉ፡፡ የሸክላ ባለሙያዎች ለምን የተጠቀሱትን ተግባር ይፈፅማሉ? ሌላውስ የማህበረሰብ ክፍል እንዴት ሊያውቁ ይችላሉ? የሚለውን ጥያቄ ማንሳት ተገቢ ነው፡፡ የሸክላ ባለሙያዎች የሚኖሩት ከማህበረሰቡ ጋር በመሆኑ ባለሙያዎቹ

መንፈሳቸው ሲነሳ የማየት እድሉ አላቸው፡፡ ከዘራቸው ውስጥ አንድ ሰው ሲሞት የሚሰባሰቡት እንደሌላው የማህበረሰብ ክፍል መርዶ ነጋሪ ተልኮ አለመሆኑንም የሚያውቁትም ከማህበረሰቡ ውስጥ የተላከ ሰው እንደሌለ በመነጋገር ነው፡፡ ማህበረሰቡም በሸክላ ባለሙያዎቹ ላይ ያለው መንፈስ ከላይ የተጠቀሱትን ተግባራት ያስፈፅማቸዋል ብለው ያምናሉ ይላሉ (ታደለ ወርቁ ቃ.መ.30/07/09 ኬላ ዙሪያ)፡፡

## 4.8. በአንጥረኛ ባለሙያዎች የሚሰሩ ቁሶች መረጃ ትንተና

በዚህ ክፍል በአንጥረኛ ባለሙያዎች የሚሰሩ ቁሶች አሰራር፣ አገልግሎትና በቁሶቹ አማካኝነት የማህበረሰቡን የህይወት ፍልስፍና መመርመር ነው፡፡ የቁሶቹን መነሻ ቅርፅ መግለፅና በቁሶቹ ስራ ላይ ያለውን ያታዊ ተሳትፎ ሁኔታ ትንታኔ የተሰጠበት ነው፡፡

## 4.9. በአንጥረኛ ባለሙያዎች የሚሰሩ ቁሶች አሰራር፣ አገልግሎትና የማህበረሰቡ የህይወት ፍልስፍና

የአንጥረኛ ባሙያዎች በተለያየ መጠንና ቅርፅ ቁሶችን ሲሰሩ በአካባቢያቸው የሚያዩት ነገር መነሻ በማድረግ ነው፡፡ ለማህበረሰቡ የእለት ከዕለት ተግባራትን ከመከወኛነት ባሻገር ባህልና አኗኗራቸውን በሚገልፅ መልኩ ቁሶችን ይሰራሉ፡፡

**ሰንዳ፡-** በአንጥረኛ ባለሙያ የሚሰራ ቁስ ነው፡፡ የቁሱን አሰራር በተመለከተ በኬላ ቀበሌ የሚኖሩ አቶ መንግስቴ አብዬ(ቃ.መ.17/05/09)እንደሚከተለው ገልፀዋል፡፡ ‹‹ሰንዳ ስሰራ ብረት አሰሪዎቹ ይመርጣሉ፡፡ ብረቱማ ላሜራ ወይም ፌሮ ብረት ነዋ፡፡ ስራው አድካሚ ነው፡፡ ጉልበት ጨራሽ ነው፡፡ ከሰሉን ተቀጣጥሎ ብረቱ ይገባል፡፡ እንዲሁም ጥሩ ሆኖ ሲግል ይወጣና ይሰነጠቃል፡፡ በመዶሻ ይመታል፡፡ ይሳላል፡፡ እጨት ይገባለታል ጥሩ እንስት ቆራጭ ይሆናል››፡፡

የሰንዳ ቁስ ሲሰራ መጀመሪያ ከሰሉ በወናፍ አማካኝነት ይቀጣጠላል፡፡ እሳቱ በጥሩ ሁኔታ ከተቀጣጠለ በኋላ ተመራጩ የብረት አይነት ይገባል፡፡ ብረቱ ሲግል በጉጠቱ አማካኝነት ወደ ውጭ ይወጣል፡፡ ‹‹መስፋው›› ላይ በማድረግ በሜሰር/ብረት መሰንጠቂያ/ ይሰነጠቃል፡፡ ተመልሶ በተቀጣጠለው ከሰል ውስጥ ይገባል፡፡ ብረቱ ሲግል ይወጣና በመዶሻ እየተቀጠቀጠ በሁለቱም በኩል ስለት እንዲኖረው ተደርጎ ይሰራል፡፡

የሰንዳ ቁስን አገልግሎት በተመለከተ አቶ ቡርቃ በዳሶ የሚከተለውን ሃሳብ ገልፀዋል፡፡ ‹‹ሰንዳ ትልቅም ትንሽም አለ፡፡ በቅርፅ አንድ ናቸው፡፡ አንዱ ትንሽ አንዱ ትልቅ ነው እንጂ አገልግሎቱ እንሰት መቁረጫ ነው፡፡ ትንሹ ሰንዳ ለየእለት ቆጮ የሚሰራበትን እንሰት መቁረጫ ነው፡፡ ትልቁማ ብዙ እንሰት ለመቆራረጫ የሚውል ነው፡፡ አገልጋይ እቃ ነው፡፡ የእንሰቱ ቅጠል ለከብት መኖ ይቆረጥበታል›› /ቃ.መ.18/05/09 ኬላ/፡፡

የሰንዳ ቁስ ከመጠን አኳያ ተጠቃሚዎቹ በሁለት ይከፍሉታል ፡፡ እነሱም፡-ትልቁና ትንሹ ሰንዳ በሚል ነው፡፡ ትልቁ ሰንዳ ቆጮ ለመስራት የሚያገለግለውን ቀስላ/የእንሰት ሽፍን/፣ እውታ/ሃሚቾ/ እና ስራ ስሩን ለመቁረጥ ጥቅም ላይ የሚውል ቁስ ነው፡፡

ትንሹ ሰንዳ ደግሞ በቅርፅ ከትልቁ ሰንዳ ጋር ተመሳሳይ ሲሆን የመጠን ልዩነት አላቸው፡፡ አገልግሎቱም በየቀኑ የሚጋገረውን ቆጮ ቃጫውን ለመቆራረጥ የሚውል ነው፡፡ የቁሱን አገልግሎት መሸጋገሪያ በማድረግ የማህበረሰቡ የህይወት ፍልስፋና ከእንሰት ስራ ጋር ቁርኝነት እንዳላቸው የሚጠቁም ነው፡፡ የእንሰት ስራ አንዱ መተዳደሪያቸው መሆኑን፣ከእንሰቱ የሚገኘውን ቅጠል ለከብቶቻቸው ሃሚቾና ግንዱን ደግሞ ለተለያዩ የምግብ አይነቶች ሰርተው እንደሚመገቡ ያመለክታል፡፡ ቁሱ ምግባቸውን ከምንና እንዴት ባለ ብልሃት እንደሚያዘጋጁ ሲጠቁመን ሃሚቾውና ቆጮው ደግሞ ሰርካዊ ኖሯቸውን የሚገልፅ ነው፡፡

**ወለት፡-** በአንጥረኛ ባለሙያዎች የሚሰራ ቁስ ነው፡፡ ቁሱ ሲሰራ በመጀመሪያ ለከሰል የሚሆነው እንጨት ተመርጦ ይፈለጣል፡፡ በማስከተልም ከሰሉ ይከስልና በእሳት ይቀጣጠላል፡፡ የባሌስትራ ወይም ፌሮ ብረት ይገባና በእሳት ይቀጣጠላል፡፡ ብረቱ ሲግል ይወጣና በሜሴር ይቆረጣል፡፡ በማስከተል በመዶሻ ይቀጠቀጥና ጫፉ ሹል ተደርጎ ይሰራል፡፡ ስለቁሱ አሰራር አቶ ግዛው ኡርጌሳ እንደሚከተለው ገልፀዋል፡፡ ‹‹ወለት ስሰራ ከሰል እፈልጣለሁ፡፡ እንዲሁም አቀጣጥለዋለሁ፡፡ እሳቱ ሽጋ ሆኖ ሲያያዝ ብረቱ ይገባል፡፡ ከዛ ለጥቆ ብረቱ በቀጭኑ ይቆረጣል፡፡ ከዛማ በመዶሻ እየመታሁ አድበለብላለሁ፡፡ ከዛማ ጫፉን ሹል አደርጋለሁ፡፡ ከዛ ጥሩ አርጎ እንሰት መንቀያ ይሆናል›› (ቃ.መ.9/08/09 ዓ.ም ዳሞ ቀበሌ)፡፡

ቁሱን ለመስራት ባሌስትራና ላሜራ ብረት ጥቅም ላይ ይውላሉ፡፡ የብረቱን አይነት የሚመርጡት ተጠቃሚዎቹ ናቸው፡፡ የተመረጠው ብረት እሳቱ ውስጥ ይገባል፡፡ በጥሩ ሁኔታ ሲግል በጉጠት ተይዞ ይወጣና በትልቁ መዶሻ በመደብደብ ድብልብል ቅርፅ

እንዲይዝ ያደርጋሉ፡፡ ከቂጡ ወፈር ያለና ወደ ጫፍ ሹል እየሆነ የሚሄድ ነው፡፡ ለእንጨት ማስገቢያ የሚሆነው አንገት የብረቱን ጎንና ጎን በተወሰነ መልኩ አጠፍ አጠፍ ይደረጋል፡፡

የወለት ቁስ አገልግሎት የደረሰ እንሰት ከስሩ ለመንቀያነት የሚውል ነው፡፡ ቁሱ የእለት ከእለት ተግባራትን ከመከወኛነት በሻገር የማህበረሰቡን አኗኗር የሚያሳይ ነው፡፡ ይህም የእንሰት ስራ የማህበረሰቡ የስራ መስክ መሆኑን፣እንሰትን ለምግብነት የሚያውሉበት ጥበብን እንዲሁም የእንሰት ተክል ከማህበረሰቡ ህይወት ጋር የተቆራኘ መሆኑን ይጠቁመናል፡፡ በሌላ መልኩ በወለት ቁስ እንሰት ሲነቀል በአንድ ሰው ብቻ የሚከውን አይደለም፡፡ ይልቁንም የአካባቢው ሰዎች በደቦ ስርዓት የሚከውኑት ተግባር ነው፡፡ ይህ ደግሞ ማህበረሰቡ ስራዎችን በመረዳዳት የሚተገብሩ መሆናቸውንና አሰፋፈራቸውም ለደቦ ስራ አመቺነት ያለው መሆኑን ያስገነዝበናል፡፡ እንሰትን በጋራ በሚነቅሉበት ወቅት እንሰቱን ከመንቀል ባሻገር ስለ አነቃቀሉና አረባቡ ልምድ ይለዋወጣሉ፡፡ ከዚህም ባሻገር ስለ ማህበራዊ ህይወታቸው የሚወያዩበት ምቹ ሁኔታን ይፈጥርላቸዋል፡፡

**ሁለት ጣት ዶማ /ቆፋሪ/፡-** በአንጥረኛ ባለሙያዎች የሚሰራ ቁስ ነው፡፡ ስለቁሱ አሰራርና አገልግሎት አቶ ሞላ እንዳለ እንደሚከተለው ገልፀዋል፡፡ ‹‹እግድህ ቆፋሪ ስንሰራ ባለቤቱ ብረቱን ምርጫ ያረጋል፡፡ ብረቱ ይገባና ሲግል ይወጣል፡፡ ለጥቆም ይቆረጣል፡፡ ብረቱ መሃል ላይ ስንጥቅ ይደረጋል ከዛ በመዶሻ እየመታን ሁለት ጣት አርገን ሺጋ እንሰት መኮትኮቻ አርገን  ለባለቤቱ እንሰጣለን፡፡ እንሰት ምግቡ መዳኒቱ ሁሉ ነው››(ቃ.መ.4/06/09 ኬላ)፡፡

የቁሱ አገልግሎት ለእንሰት ተክል መኮትኮቻነት የሚውል ነው፡፡ ይህ ግልጋሎቱ የሚያሳየው ደግሞ የማህበረሰቦቹ ህይወት ከእንሰት ተክል ጋር ትስስር ያላቸው መሆናቸውን ነው፡፡ እንሰት ለክስታኔ ማህበረሰቦች አንዱ የኢኮኖሚ ምንጫቸው እንደሆነ ያሳየናል፡፡ የእንሰት ተክል በአካባቢው ላይ  የሚገኝ መሆኑንና እንዴትና ለምን እንደሚጠቀሙት ያስገነዝባል፡፡ የእንሰቱን ችግኝ እንዴት እንደሚያራቡትና እንደሚያሳድጉት የሚጠቁም ነው፡፡ በሌላ መልኩ እንሰት በተለያየ ምክንያት ሰዎች ገላ ውስጥ ተሰባብረው የቀሩ አጥንቶችን በመግል መልክ የሚያወጡበትና የሳል በሽታን ያድናል ብለው ተግባራዊ የሚያደርጉትን አስተሳሰብ የሚያስገነዝብ ነው፡፡

**የብረት ሲቢሳ፡-**በአንጥረኛ ባለሙያዎች የሚሰራ ቁስ ነው፡፡ የቁሱን አሰራርና ለውጡን በተመለከተ አቶ ለማ አጨሞ እንዲህ ገልፀውታል፡፡ ‹‹ፊትማ የእንሰቱን ቃጫ እሚለይ ያው ሸንበቆ ነበር፡፡ ያው ከእግድህ ሸንበቆ ወቅቱ ሲቆይ ይሰበራል፡፡ በብረት እኛ አበጀን የብረቱ

ብዙ እድሜ አለው፡፡ ያው ከዛ መጀመሪያ ብረቱን ይቆረጣል፡፡ ከያማ ከዳርና ዳሩ ላይ ብረቱን በመጠቅለል የእጅ መያዣ ይበጅለታልና ይሳላል፡፡ ከያ የእንሰት ቃጫ ጥሩ አርጎ ይለይበታል›› (ቃ.መ.9/06/09 ዳሞ ቀበሌ)፡፡

የእንሰት ተክልን ለምግብነት በሚዘጋጅበት ወቅት የተሰነጠቀ ሸንበቆ አገልግሎት ላይ ይውል ነበር፡፡ ሸንበቆው እንጨት እንደመሆኑ መጠን ከተወሰነ ጊዜ በኂላ ይሰበራል፡፡ የእንሰት ስራው የተቀላጠፈ እንዳይሆን ያደርጋል፡፡ ይህን ችግር የተረዱ የአካባቢው አንጥረኞች የሸንበቆውን የእንሰት ቃጫ መፋቂያ በመለወጥ በብረት ሰርተውታል፡፡ ይህም በቁሶቹ ላይ የተከሰተውን ለውጥ ያመለክተናል፡፡

የብረት ሲቢሳ አሰራር ቁሱ እንዲሰራላቸው የፈለጉ ሰዎች የብረት አይነቱን ይመርጣሉ፡፡ ብረቱን በተቀጣጠለው ከሰል ውስጥ በማስገባት ከጋለ በኂላ ይወጣና በሜሴር ይቆረጣል፡፡ ለእጅ መያዣ ያህል ዳርና ዳር ላይ ይጠቀለላል፡፡ በእጅ መያዣው መካከል ያለው ክፍል በሁለቱም በኩል ይሳላል፡፡ አገልግሎቱም ለእንሰት ቃጫ መፋቂያነት ነው፡፡

ቁሱ ከእለት ግልጋሎቱ ባሻገር ማህበረሰቡ ከእንሰት ስራ ጋር ያላቸውን ግንኙነት ያስገነዝበናል፡፡ ማህበረሰቡም ባህላዊ እውቀታቸውን ተጠቅመው ከእንሰት ተክል ልዩ ልዩ ምግቦችን የሚያዘጋጁበትን መንገድ ያመላክተናል፡፡

**ቁንጥል፡-**በአንጥረኛ ባለሙያዎች ከሚሰሩ ቁሶች አንዱ ነው፡፡ ስለ ቁሱ አሰራርና አገልግሎት በተመለከተ አቶ ተመስገን ዳልዳቦ እንዲህ ገልፀውታል፡፡ ‹‹ይቺ ቁስ ትንሽ ሆና ስለሆነ ቁንጥል ተባለች፡፡ ያው ሲሰራ እንግድህ ትንሽ ብረት ይቆረጣል፡፡ ከያ አራት መዓዘን ተደርጎ ነው፡፡ እሚቆረጥ ከያ ከጎንና ጎን ስለት ይደረጋል፡፡ በእሳት አግለን ነው እምንቆርጠው፡፡ ከታች በኩል ለመያዣ እንጨት እናገባበታለን፡፡ ከያ እማ ‹ቀስላ› ለማውጫ ይሰራል››(ቃ.መ.19/06/09 ዳሞ)፡፡

የቁንጥል ቁስ የቀስላውን/የእንሰቱን ሽፍን/ ቅርፅ ለማውጫ የሚያገለግል ነው፡፡ የእንሰት ቅጠል፣ቀስላውና የሃሚቸው ክፍል/ቂጡ/ አለው፡፡ የቁሱ አገልግሎት የሚያሳየን ቁሱ የበቀለበት ማህበረሰብ የእንሰት ተክል ግንድ ሽፍኖ የያዘውን‹‹ቀስላ›› በምን መንገድ ቅርፅ አውጥተው ለምግብነት እንደሚያውሉት የሚያመለክት ነው፡፡

**የብረት ዣግባ፡-** በአንጥረኛ ባለሙያዎች የሚሰራ ቁስ ነው፡፡ ስለ ቁሱ አሰራርና አገልግሎት አቶ ሰብስቤ በየነ እንዲህ ገልፀውታል፡፡ ‹‹እግድህ የብረት ዣግባ በፊት እንጨት ነበር፡፡ ያው

አሁን እኳ ብረት አደረግን እኛ አንጥረኞች ነና፡፡ አሰራሩ እኮ ብረቱን እሳት አስገብተን ይግላል፡፡ ከያ በመዶሻ ይጠፈጠፍል፡፡ ትንሽ ስለት ይሰጣል፡፡ ከያ ከታች ጉጥ አበጃለሁ፡፡ ያው እንግድህ እሚጠቅመው ሴቶቹ ሃሚቾ እንዲቀጠቅጡበት ነው››(ቃ.መ.14/05/09 ቡኢ)፡፡

የቁሱ አገልግሎት ሃሚቾ የሚባለውን የእንሰት ክፍል ለመቆራረጫነት ነው፡፡ ይህ የሚያሳየው እንሰት በማህበረሰቡ ውስጥ ለተለያየ አገልግሎት የሚውል መሆኑን ነው፡፡ እንሰት የመትከልና ሲደርስ መንቀል የወንዶች ተግባር ሲሆን ወደ ምግብነት የሚለውጡት ግን ሴቶች መሆናቸውን የሚገልፅ ነው፡፡ ሴቶች እንሰትን ወደ ምግብነት የለወጡት መንገድ የሚያመላክት ነው፡፡

የእንሰት ተክል በተለያዩ አካባቢዎች ላይ ሊገኝ የሚችል ቢሆንም ልዩ ትርጉም ላይኖረው ይችላል፡፡ በክስታኔ ማህበረሰብ ውስጥ የሚገኘው እንሰት ግን ከውጭ ሆነን የምናየውን እንሰት ብቻ ሳይሆን ከጀርባው ያለው እሳቤ ከማህበረሰቡ ህይወት ጋር በእጅጉ የተቆራኘ ነው፡፡ በጓሯቸው የሚገኘው እንሰት ድርቅን የመቋቋም አቅም ያለው ነው፡፡ ከስሩ እስከ ጫፉ ድረስ ያለውን ክፍል በተለያየ መንገድ በማዘጋጀት ግልጋሎት እንዲሰጥ ያደርጉታል፡፡ የእንሰት ተክል ከሚሰጣቸው አገልግሎቶች መካከል የሚከተሉት ይገኙበታል፡፡ በቤት ውስጥ ለምንጣፍነት የሚያገለግለው ጅባ ይሰራበታል፡፡ ቆጮ፣ሃሚቾና ቡላ የሚባሉ የምግብ አይነቶችን ያዘጋጁበታል፡፡ ምግቡ ደግሞ ህይወታቸው ነው፡፡ በሌላ መልኩ ቅጠሉ ለቆጮ መጋገሪያ፣ቅቤና አይቤ ለመያዣነት እንዲሁም ለከብቶች መኖ በመሆን ያገለግላል፡፡ የእንሰት ተክል ከምግብነትና ቤት ውስጥ መገልገያ  ባለፈ ለተለያዩ በሽታዎች መድሃኒት እንዲሆን አድርገው ያዘጋጁታል፡፡





እንሰት በሰንዳ ቁስ ሲቆረጥ





እንሰት በወለት ቁስ ሲነቀል

እንሰት በመፋቅ ላይ

**ጦር**፡-የአንጥረኛ ባለሙያዎች ጥበብ አርፎበት የሚሰራ ቁስ ነው፡፡ ስለቁሱ አሰራርና አገልግሎት አቶ ባለእዳ ተካ እንደሚከተለው ገልፀዋል፡፡ ‹‹ጦር በሶስት አይነት ነው፡፡ ጨልጨል ጦር አለ ሰንዳ ጦር አለ ደሞ ማሊሲ ጦር አለ፡፡ አሰራሩ ጨልጨል ጦር ከሆነ

ጫፉን ሾል ወዲያውም የሚቦጭቅ ሰንጥ ነገር ይሰራል እንስሳትን ማደኛ ነው፡፡ ሰንዳ ጫፉን በማሾል ይሰራል ጉጥ የለውም እንስሳትን ለማደኛ ያገለግላል፡፡ ማሊሲ ጦር ለጌጥ ነው አናሳ ነው›› /ቃ.መ.18/05/09 ቡኢ ዙሪያ ቀበሌ/፡፡

በአንጥረኛ ባለሙያዎች ከሚሰራ ቁሶች መካከል አንዱ ጦር ነው፡፡ ባለሙያዎቹ ቁሱን በሶስት ይከፍሉታል፡፡ እነሱም፡-ጨልጨል፣ሰንዳና ማሊሲ ጦር የሚሉት ናቸው፡፡

**ጨልጨል ጦር፡-** ጫፉ አካባቢ ሹል ከመሆኑም ባሻገር ጉጥ ጉጥ ቅርፅ ያለው ቁስ ነው፡፡ የቁሱ አገልግሎት ስጋቸው የማይበሉ እንስሳትን ለማደኛ የሚያገለግል ነው፡፡ ጦሩ እንስሳቱን ከወጋ በኂላ ለማውጣት ጉጡ ያስቸግራል፡፡ ጦሩ የሚወጣበት ሁኔታ እንኳ ቢኖር ስጋቸውን ቦጭቆ ይወጣል፡፡

**ሰንዳ ጦር፡-** ጫፉ ሹል የሆነ ቁስ ነው፡፡ እንደ ጨልጨል ጦር ጉጥ የለውም፡፡ የቁሱ አገልግሎት ስጋቸው የሚበሉ እንስሳትን ለማደኛነት የሚውል በመሆኑ ስጋቸውን ቦጭቆ እንዳይወጣ ሹል ብቻ ያደርጋሉ፡፡

**ትንሹ ጦር/ማሊሲ ጦር/፡-** ይህ ቁስ ከሌሎቹ በመጠን ያነሰ ነው፡፡ የቁሱ አገልግሎት ከፈረስ ጋር ለጌጥ የሚያዝ ነው፡፡ አንዳንድ ጊዜም መጠናቸው ትናንሽ የሆኑ እንስሳትን ለማደኛነት የሚውል  ነው ይላሉ፡፡

**ቃጭል፡-**በአንጥረኛ ባለሙያዎች የሚሰራ ቁሱ ነው፡፡ ለቁሱ መነሻ ቅርፅና አሰራር በተመለከተ አቶ አጉሌ ጣሳው እንደሚከተለው ገልፀዋል፡፡ ‹‹ቃጭል የሰራነው በቤተክርሲታን ላይ የተሰቀለውን ምርዋ በማየት ነው፡፡ ለቃጭል ስራ ተመራጩ ብረት ላሜራ ነው አሰራሩ ያው ብረቱን አጠፍና ክብ ይደረጋል፡፡ ክቡ ውስጥ ቀጭን ብረት ይገባል እንዲቅጨለጨል ነዋ፡፡ ከዛ ወንድ ፈረስ ያለው ሰው ይገዛል›› (ቃ.መ. 8/05/09/ ዳሞ ቀበሌ)፡፡

ቃጭል የአንጥረኛ ባለሙያዎች የጥበብ አሻራ ያረፈበት ቁስ ነው፡፡ የቁሱ መነሻ ቅርፅ ቤተክርስቲያ ላይ የሚሰቀለውን ምርዋ/ደወል/ መሰረት ያደረገ ነው፡፡ ቃጭል በአፍ የተደፋ የብርጭቆን ቅርፅ የያዘ ሲሆን መካከል ላይ ቀጭን ብረት የተንጠለጠለበት ቁስ ነው፡፡ የቁሱ አገልግሎት በወንድ በፈረስ አንገት ላይ የሚንጠለጠል ነው፡፡ ቃጭሉ ሁልጊዜ  ከፈረሱ አንገት ላይ ስለማይወልቅና በተንቀሳቀሰ ቁጥር ስለሚቅጨለጨል ንቁ ይሆናል ይላሉ፡፡

በሌላ መልኩ ደወል የኦርቶዶክስ ክርስትና ሃይማኖት ተከታዮች ወደ ቤተክርስቲያን እንዲመጡ የሚያነቃ/የሚቀሰቅስ/ ነው፡፡ ቃጭል ከምርዋ ጋር ያለው ተዛምዶ ከቅርፅ ባሻገር አገልግሎትንም ያቀፈ ነው ማለት ይቻላል፡፡

በቁሱ አማካኝነት ወንድ እና ሴት ፈረስን በቀላሉ የሚለዩበት መንገድን የሚጠቁም ነው፡፡ ፈረስ ከመጓጓዣነቱ በሻገር ማህበራዊ ደረጃን ይጠቁማል፡፡ በክስታኔ ማህበረሰብ የተጣሉ ሰዎችን የሚያስታርቁ፣ችግረኞችን የሚረዱ፣ሀገር የሚጠብቁና መልካም ተግባራትን ያከናወኑ ወንዶች ሲሞቱ ለቅሷቸው በፈረስ ይታጀባል፡፡

ፈረሶቹን ‹‹መጣብር›› ተብሎ የሚጠራውን የማዕረግ ልብሳቸውን ያለብሷቸዋል፡፡ ይህ የማዕረግ ልብስ በአዘቦት ቀን አይደረግላቸውም፡፡ ቃጭልና ጌጣጌጥ ተደርጎባቸው ይቀርባሉ፡፡ በፈረሶቹ ላይ ሆነው ሟች በህይወት በነበሩበት ወቅት የሰሩትን መልካም ነገር እየተነገረላቸው ይለቀስላቸዋል፡፡ ይህ የሚያደርጉበት ምክንያት ተተኪ ጀግኖችን ለማፍራት በማሰብ ነው ይላሉ፡፡

**ድግር፡-**ስለ ቁሱ አሰራርና አገልግሎት አቶ ትርፌ ጌታሁን እንደሚከተለው ገልፀዋል፡፡ ‹‹ፊት የእንጨት ድግር ነበር፡፡ አሁንማ እምታየው ነው በብረት ቀየርነዋ መልኩ ተመሳሳይ ነው፡፡ ብረቱ እድሜ አለው፡፡ ደሞ ከጎን እየቀደደ ይሄዳል ደግ እቃ ነው፡፡ አሰራሩማ ብረቱ እሳት ይገባና ይሰነጠቃል፡፡ ከያማ በኋላ ከጫፍ ጠበብ ይደረጋል፡፡ ጥቅርት የሚያስገባ ጆሮ ይበጃል፡፡ ከዛ ይሸጣል›› (ቃ.መ.6/06/09 ኬላ ዙሪያ)፡፡

ድግር በአንጥረኛ ባለሙያዎች የሚሰራ ቁስ ነው፡፡ ቁሱ የግራና ቀኝ ክፍል አለው፡፡ ቅርፁ ጠፍጣፋ ሲሆን ጠበብ ጠበብ እያለ ወደፊት የሚሄድ ቁስ ነው፡፡ የቁሱ አገልግሎት እርፍ ላይ የተገጠመውን ማረሻ አቅፎ የሚይዝ ነው፡፡ ቁሱ በአሁኑ ቅርፅ እንዲሰራ መሰረቱ የእንጨት ድግር ነው፡፡ ከእንጨት የሚሰራው ድግር ከአንድ አመት በኋላ አገልግሎቱ ይቀንሳል፡፡ ከዚህም ባሻገር ማረሻውን ደግፎ ከመያዝ በዘለለ በጎንና ጎን እያረሰ አይሄድም፡፡

ከላሜራ ብረት የሚሰራው ድግር ግን ማረሻውን ደግፎ ከመያዝ ባሻገር በጎንና ጎን እያረሰ ይሄዳል፡፡ የሚያርሱትን በሬዎች እንዳይጎዳቸው ተግባራዊ የሚደረገው እዳሪ መሬት ላይ ሳይሆን አፈሩ ለስላሳ በሆነ መሬት ላይ ነው፡፡ የአገልግሎት ጊዜውም ከእንጨቱ ድግር የተሻለ ነው፡፡ የብረት ድግሩ በሚሳሳበት ወቅት ወደ ቢላዋና መሰል ቁሶች ተቀይረው ግልጋሎት ይሰጣሉ፡፡ የእንጨት ድግር ወደ ብረት ድግር ያደረገውን ሽግግር ያሳየናል፡፡

**ማጭድ፡-**የቁሱን አሰራርና መነሻ ቅርፅ አቶ ገዛኸኝ እምነቱ እንደሚከተለው ገልፀዋል፡፡ ‹‹ያው ማጭድ የጋማ ከብትን ጥርስ ቅርፅ መነሻ ያደረገ ነው፡፡ ጋማ ከብት ከወዳ ወዲህ ይነጫል፡፡ እኛ ያየነውን እሰራለን፡፡ አሰራሩ እማ ብረቱ እሳት ገብቶ በመዶሻ ይታጠፍል፡፡ እጀታ ይሰራለታል፡፡ ከዛ በኋላ ጥርስ ይወጣለትና በሞረድ ይሞረዳል››(ቃ.መ.8/05/09 ዳሞ)፡፡

ይህ ቁሱ የአንጥረኛ ባለሙያዎች የጥበብ ውጤት ነው፡፡ ማጭድ አሁን የያዘውን ቅርፅ ይዞ እንዲሰራ መነሻ የሆናቸው ቅርፅ በጋማ ከብት ላይ የተደረደሩ ጥርስ ናቸው፡፡ የጋማ ከብት ደግሞ በማህበረሰቡ ውስጥ ይገኛሉ፡፡ የጋማ ከብት ጥርስና ማጭድ ተዛምዶኣቸው በሦስት መልኩ ነው፡፡ አንደኛው ከቅርፅ አንፃር ሲሆን የማጭድ ጥርስ በጋማ ከብት ድድ ላይ ከተደረደሩ ጥርሶች ጋር ይመሳሰላሉ፡፡

ሁለተኛው ተዛምዷቸው ደግሞ ከስያሜ አንፃር ነው፡፡ ጥርስ የሚለው መጠሪያ ስም ለሁለቱም በጋራ የሚያገለግል ነው፡፡ በሌላ መልኩ ደግሞ የማጭድ ጥርስ ብዙ አገልግሎት ከሰጠ በኋላ ወይም በሌላ ምክንያት ጥርሱ ሲረግፍ  ጥርሱ አለቀ ይባላል፡፡ ይህ እሳቤ ለጋማ ከብትም ያገለግላል፡፡ ሦስተኛው ተዛምዶአቸው ደግሞ ከአገልግሎት አንፃር ነው፡፡ የጋማ ከብቶች ሳርን በጥርሳቸው አማካኝነት ይግጣሉ፡፡ የአጋጋጣቸው ሂደት አንገታቸውን ወደ ሳሩ በማስቀደም ሳሩን ወደ አንገታቸው በጥርሳቸው ይስባሉ፡፡ ማጭድ ደግሞ ሳርና መሰል ነገሮችን ለማጨጃነት የሚያገለግል ቁስ ነው፡፡ የአስተጫጨዱ ሂደት ማጭዱን ወደ ሚታጨደው ሳር በማስቀደም ወደ አጫጁ ሰው ጠርጎ ያመጣል፡፡ ማጭድ በጋማ ከብቶች ላይ በስርዓት የተደረደሩ ጥርሶችን መነሻ ሲያደርግ በቅርፅ፣ስያሜና አገልግሎት ተመሳሳይነት ስላላቸው ነው፡፡ ማጭድ በሌሎችም ማህበረሰቦች ዘንድ እንዳለ ይታወቃል፡፡ ልዩነቱ ሌሎች ይህን ትርጓሜ ማወቅ አለማወቃቸው ላይ ነው፡፡

**ቢላዋ፡-**የቁሱን አሰራርና መነሻ ቅርፅ በተመለከተ አቶ ተሾመ ደበላ እንደሚከተለው ገልፀዋል፡፡ ‹‹ድሮ ድሮ ስጋ እሚዘለዘል በተሰነጠቀ ሸንበቆ ነበር፡፡ እግድህ ከያ በኋላ ሸበቆ እየቀረ ቢላ ሰራን፡፡ ቢላ ሲሰራ ላሜራ ብረትን እሳት በማስገባት አበጃለሁ፡፡ ለጥቁ በሞዶሻ እየተቀጠቀጠ ይበጃል፡፡ እጀታ አበጅለታለሁ፡፡ በሞረድ ሲሞረድማ ሸጋ ይሆናል››(ቃ.መ.1/06/09 ኬላ ) ፡፡

የቁሱ ቅርፅ መነሻው የሸንበቆ ስንጣቂ ነው፡፡ የሸንበቆ ተክል በማህበረሰቡ ውስጥ  ይገኛል፡፡ የሸንበቆውን ሁለት አንጓ በመቁረጥና በመሰንጠቅ ስጋ ይዘለዘልበት ነበር፡፡ ከዚህም ባሻገር ለጎመን መክተፊያና ለእንሰት ቅጠል መለምለሚያነት ሲጠቀሙበት ኖረዋል፡፡ ጠንከር ያሉ ነገሮችን ለመቁረጥ ስላስቸገራቸው በተሰነጠቀ ሸንበቆ ቅርፅ ከፌሮ ብረት ቢላዋን እንዲሰሩ

አስችሏቸዋል፡፡ የቢላዋ ቁስ አሰራር የፌሮ ብረትን እተቀጣጠለው እሳት ውስጥ በማስገባት እንዲግል ይደረጋል፡፡ በማስከተልም ብረቱን በመቁረጥ በትንሹ መዶሻ እየተቀጠቀጠ ይሰራል፡፡ የእጅ መያዣ እንጨት ገብቶለት  በሞረድ ስለት ይወጣለታል፡፡ ቢላዋ በሌሎች ማህበረሰቦች ውስጥ ይታወቃል፡፡ የክስታኔ ማህበረሰብ ብቻ አይደለም፡፡ ልዩነቱ ሌሎች ማህበረሰቦች ይህን መነሻ ቅርፅ ማወቅ አለማወቃቸው ላይ ነው፡፡

**የብረት ምድጃ፡-**የቁሱን አሰራርና መነሻ ቅርፅ አስመልክቶ አቶ ዱሬሳ ተመስገን እንደሚከተለው ገልፀዋል፡፡ ‹‹ቁሱ ከምድጃ ታይቶ የተሰራ ነው፡፡ ያው ሲሰራ ፌሮ ይቆረጣል፡፡ በመቀጠልም አጠፍ አጠፍ ይደረጋል፡፡ ከዛም ይጋጠማል፡፡ ዙሪያ ክብ ይደረግና ማለት ነው፡፡ ከዛም እግር ይበጅለታል፡፡ እቃ የሚሸከምበት ጉጥ ይሰራለታል፡፡ ከያማ ጥሩ እቃ ሆኖ ይሸጣል (ቃ.መ1/06/09 ኬላ)፡፡

የአንጥረኛ ባለሙያዎች የብረት ምድጃን ሲሰሩ መነሻቸው የጭቃ ምድጃ ነው፡፡ ይህ የሚያሳየው የቁሱን ለውጥ ነው፡፡ የብረት ምድጃን ሲሰሩ ፌሮ ብረትን በመቁረጥና በመገጣጠም ክብ ቅርፅ እንዲይዝ አድርገው ይሰሩታል፡፡ ከዚህም ባሻገር ሦስት እግር ይሰራለታል፡፡ የቁሱ አገልግሎት ምጣድና ብረት ምጣድን ላዩ ላይ በማስቀመጥ ተፈላጊውን ነገር ለማብሰል የሚያስችል ቁስ ነው፡፡ የብረትና ጭቃ ምድጃ በቅርፅና ስያሜና ተመሳሳይነት አላቸው፡፡

## 4.10. ለአንጥረኛ ባለሙያዎች መስሪያ የሚያስፈልጉ ቁሶች ስምና አገልግሎት

ወናፍ፡-ይህ ቁስ የብረትና ቆዳ ውጤት ሲሆን አገልግሎቱ ከሰሉ እንዲቀጣጠል አየር የሚሰጥ ነው፡፡

የበሬ ቀንድ፡- ከወናፉ ጋር በማገናኘት የሚታሰር ሲሆን የአስተሳሰር ሂደቱም የቀኙ ቀንድ ቀኙ ወናፍ ላይ የግራው ቀንድ ደግሞ ግራው ወናፍ ላይ ይታሰራል፡፡ የበሬው ቀንድ ከወናፉ የሚላከውን አየር ተቀብሎ ወደ ብረት ቱቦ የሚያስተላልፍ ነው፡፡

የብረት ቱቦ፡- ባለሙያዎቹ ሁለት ቀጫጭን ቱቦዎችን በበሬው ቀንድ ላይ ይሰካሉ፡፡ የቁሱ አገልግሎት ወደ በሬው ቀንድ የመጣውን አየር ተቀብሎ ወደ ከሰሉ በማድረስ እሳቱ እንዲቀጣጠልና ብረቱ እንዲግል የሚያስችል ቁስ ነው፡፡

መስፋ፡-የቁሱ ቅርፅ ጠፍጣፋ ሲሆን አገልግሎቱ የሚሰሩትን ቁሶች ከታች ደግፎ የሚይዝ ነው፡፡

ጉጠት፡-የቁሱ አገልግሎት የጋለውን ብረት ከእሳት ውስጥ ለማውጣትና አጣብቆ ለመያዝ የሚያገለግል ነው፡፡

ሜሴር፡-ይህ ቁስ ጫፍ እንደ ጦር ሹል የሆነ ነው፡፡ የቁሱ አገልግሎቱ በተለያየ መጠንና ቅርፅ ብረታ ብረት ለመቆራረጥ የሚያገለግል ነው፡፡

ትንሹ መዶሻ፡-ይህ ቁስ የእንጨትና ብረት ድምር ውጤት ነው፡፡ የቁሱ አገልግሎት በእሳት የጋለውን ትንንሽ ብረታ ብረት ተፈላጊው ቅርፅ እንዲይዝ የሚቀጠቀጥበት ነው፡፡

ትልቁ መዶሻ፡- ትልልቅ ቁሶችን ቀጥቅጦ ቅርፅ ለማውጣት የሚያስችል ቁስ ነው፡፡

መክብ፡-ይህ ቁስ የመወጣጫ ደረጃ/መሰላል/ አይነት ቅርፅ ያለው ነው፡፡ የቁሱ አገልግሎት የተለያዩ ብረታ ብረትን በተፈላጊው ቅርፅ ለማጠፍ የሚያስችል ቁስ ነው፡፡

ሞረድ፡- በተለያየ መጠንና ቅርፅ የተሰሩ ቁሶችን ስለት የሚያወጣ ቁስ ነው፡፡

ብረታብረት፡-የአንጥረኛ ባለሙያዎች ለቁሱ መስሪያነት የተለያዩ የብረታ ብረት አይነቶችን ይጠቀማሉ፡፡ እነሱም፡-ባሌስትራ እና ላሜራ ብረት ተጠቃሽ ናቸው፡፡

## 4.11. በአንጥረኛ ባለሙያዎች የሚሰሩ ቁሶች የሚያልፏቸው ደረጃዎች

በአንጥረኛ ባለሙያዎች የሚሰሩ ቁሶች የቁስነት ደረጃን የሚጎናፀፍት የተለያዩ ሂደቶችን ስርዓት ባለው መንገድ አልፈው ነው፡፡ በእያንዳንዱ ሂደት ውስጥ የባለሙያዎቹን ጥበብ፣ገንዘብ፣ጊዜና ጉልበትን የሚጠይቅ ነው፡፡

በመስክ ቆይታዬ ወቅት እንደቃኘሁትና ባለሙያዎቹም የነገሩኝን መነሻ በማድረግ ቁሶቹ አምስት ደረጃዎች ያልፋሉ፡፡ እነሱም፡-የከሰል እንጨት መፍለጥና በወናፍ ከሰሉን ማቀጣጠል ፣ብረታ ብረቱን በተቀጣጠለው ከሰል ውስጥ ማስገባትና ማገለባበጥ ፣የጋለውን ብረት በጉጠት ማውጣትና መቆራረጥ፣በመዶሻ ቅርፅ ማውጣት በመጨረሻም በሞረድ አማካኝነት ተፈላጊውን ስለት የማውጣት ተግባር መከወን የሚሉት ተጠቃሽ ናቸው፡፡ ከላይ የተጠቀሱት የአሰራር ደረጃዎች ከሌሎች አካባቢዎች ጋር ያላቸውን ተወራራሽነት ለማመልከት እንጂ የክስታኔ ማህበረሰብ ልዩ መገለጫ ሆነው አይደለም፡፡

### 4.11.1. የከሰል እንጨት ፈለጣና በወናፍ ከሰሉን የማቀጣጠል ተግባር

በብረታ ብረታ ስራ ላይ ተቀዳሚው ተግባር የከሰል እንጨት/ጉቶ/ ከጫካና ማሳ ውስጥ የማምጣትና መፍለጥ ተግባር ነው፡፡ ለከሰል ተመራጩ የእንጨት አይነት የግራርና ቁርቁራ ጉቶ ነው፡፡ የጉቶውን ዳርና ዳር በዶማ በመቆፈር  በፋስ ስሩ ተቆርጦ ወደ ሚሰሩበት ቦታ ይወስዱታል፡፡ በመቀጠልም በፋስ እየተፈለጠ በፀሃይ እንዲደርቅ ይደረጋል፡፡ የተፈለጠው ጉቶ ከስሎ ደረቅ ቦታ ላይ ይቀመጣል፡፡ የብረት ስራው ሲጀመር ከሰሉ እየተመጠነ ይገባል፡፡ በወናፉ አየር እየተሰጠው ይቀጣጠላል፡፡

### 4.11.2. ብረታ ብረቱን እሳት ውስጥ የማስገባትና ማገለባበጥ ተግባር

ከሰሉ ከጥቁርነት ወደ ቀይነት እየተለወጠ ባለበት ሁኔታ ላይ ባሌስትራ፣ፌሮና ላሜራ የሚባሉ ብረታ ብረት በጉጠቱ አማካኝነት እሳቱ ውስጥ ይገባሉ፡፡ ወናፉ የሚያናፋው ባለሙያ በአግባቡ እያናፋ አየር ለከሰሉ እንዲደርሰው ያደርጋል፡፡ ብረታ ብረቱን በተቀጣጠለው እሳት ውስጥ የሚያስገባውና የሚያወጣው ባለሙያ ከሰል ሲያንስ እየመጠነ ይጨምራል፡፡ በጉጠቱ አማካኝነት ብረታ ብረቱን እያገላበጠ እስከሚግል ድረስ የሚጠበቅበት ክፍል ነው፡፡

### 4.11.3. የጋለውን ብረታ ብረት በጉጠት የማውጣትና መቆራረጥ ተግባር

በጥሩ ሁኔታ በተቀጣጠለው ከሰል ውስጥ የገባው ብረታ ብረት ሲግል በጉጠቱ አማካኝነት በማውጣቱ ‹መስፋ› ላይ የማድረግ ተግባር ይከናወናል፡፡ ቀጣዩ ተግባር ሜሴሩን በጉጠት መያዝና በመዶሻ በመምታት ብረታ ብረቱን በተለያየ ቅርፅና መጠን የመቁረጥ ተግባር የሚከወንበት ክፍል ነው፡፡

### 4.11.4. ብረታ ብረቱን በመዶሻ በመቀጥቀጥ ቅርፅ የማውጣት ተግባር

የተለያየ አገልግሎት እንዲሰጥ በሚያስችል መልኩ የተቆራረጠው ብረታ ብረት እተቀጣጠለው ከሰል ውስጥ ይገባል፡፡ ብረታብረቱ በጥሩ ሁኔታ ሲግል በጉጠት በማውጣት መስፋ ላይ ይደረጋል፡፡ እሳቱ ውስጥ የገባ ብረት ሁሉ በአንድ ጊዜ ወደ ዳር አይወጣም፡፡ አንድ ቁስ በመዶሻ ተቀጥቅጦ አስፈላጊውን ቅርፅ ከያዘና ወደ ሞራጁ ባለሙያ ከተላከ በኋላ ተረኛው ብረት ከእሳቱ ውስጥ ይወጣል፡፡ እሳት ውስጥ የገባው ብረት ሁሉ በአንድ ጊዜ የማይወጣበት ምክንያት ብረቱ በትኩስነቱ ካልተሰራ አስፈላጊውን ቅርፅ ማስያዝ ስለሚያስቸግር ነው፡፡

ባለሙያው የጋለውን ብረት በጉጠት በማውጣትና በመያዝ ወደኋላ፣ወደፊት፣ወደጎን እና ወደ መሃል ምቱ እያለ ለረዳቶቹ በመናገር በትልቁና ትንሹ መዶሻ የሚመቱበት ክፍል ነው፡፡

## 4.11.5. ቁሶቹን የመሞረድ ተግባር

ቁሶቹ በተለያየ መጠንና ቅርፅ ከተሰሩ በኋላ ያለውን ሂደት የሚመለከት ነው፡፡ የመሞረድ ተግባርን የሚከውነው ባለሙያ ቁሶቹን እንጨት ላይ በማስደገፍ በሞረዱ ስለት ይሰጣቸዋል፡፡ ቁሱን ለመስራት በሚታለፍ አምስት ደረጃዎች ውስጥ የባለሙያዎቹ አቀማመጥ ክብ ነው፡፡ ክብ የሆነበት ምክንያት ቁሱን ለመቀባበል እንዲያመቻቸውና አንዱ ባለሙያ የሌላኛውን ባለሙያ አሰራር በመቃኘት ልምድ እንዲለዋወጡና ስህተቶችን ለማረም እንዲያስችላቸው ነው፡፡ በብረት ስራ ላይ ሁሉም ባለሙያዎች የተለያየ የስራ ድርሻ አላቸው፡፡ እነዚህም፡-ወናፍ የሚያናፋ፣ብረታብረቱን በተቀጣጠለው ከሰል ውስጥ የሚያስገባና የሚያወጣ፣ብረታብረቱን የሚቆራርጥና ቅርፅ የሚያወጣ፣በመዶሻ ብረቱን የሚደበድቡ እና በሞረድ ስለት የሚሰጡ ባለሙያዎች ተጠቃሽ ናቸው፡፡

## 4.12. በአንጥረኛ ባለሙያዎች የሚሰሩ ቁሶች ጠቀሜታ

የአንጥረኛ ባለሙያዎች ቁሶችን በተለያየ መጠንና ቅርፅ ሲሰሩ ኖረዋል፡፡ በአሁኑ ወቅትም በመስራት ላይ ይገኛሉ፡፡ የተሰሩት ቁሶች አገልግሎታቸው ሲቀንስ የማደስ ተግባር በመከወን ወደ ቀድሞው ተግባራቸው እንዲመለሱ ያደርጋሉ፡፡ በባለሙያዎቹ የሚሰሩ ቁሶች ተቀዳሚው ተግባራቸው ለማህበረሰቡ የእለት ከእለት ተግባራትን ለመከወኛነት ማዋል ነው፡፡

### 4.12.1. ማህበራዊ ጠቀሜታ

በአንጥረኛ ባለሙያዎች የሚሰሩ ቁሶች ለበቀሉበት የማህበረሰብ ክፍል የተለያዩ አገልግሎቶችን ይሰጣሉ፡፡ ከተቀዳሚው አገልግሎታቸው አኳያ ተጠቃሚዎቹ በሁለት ከፍለዋቸዋል፡፡ እነሱም፡-ከእንሰት ስራ እና እንሰሳት ጋር የተያያዙ ቁሶች የሚሉት ናቸው፡፡

#### 4.12.1.1. ከእንሰት ስራ ጋር የተያያዙ ቁሶች

በክስታኔ ማህበረሰብ ውስጥ የእንሰት ተክል ይገኛል፡፡ የእንሰቱን ተክል ወደ ምግብነት በሚለወጥበት ሂደት ላይ ከሚያስፈልጉ መሳሪያዎች ውስጥ በአንጥረኛ ባለሙያዎች የሚሰሩ ቁሶች ይገኙበታል፡፡ ቁሶች በእንሰቱ ስራ ላይ የራሳቸው አበርክቶ አላቸው፡፡ ሰንዳ ቁስ

የደረሰውን እንሰት ለመቁረጫ፣ወለት ቁስ ደግሞ የደረሰው እንሰት የሚነቀልበት እንዲሁም ቆፋሪ እንሰቱ እንዲያድግ የሚኮተኮትበት ቁስ ነው፡፡

ሌላኛው ደግሞ የብረት ሲቢሳ ሲሆን የእንሰቱ ቃጫ የሚለይበት ነው፡፡ ቁጥል ደግሞ የእንሰቱን ሽፍን በቅርፅ ለማውጣት የሚያገለግል ነው፡፡ የብረት ዣግባ ሃሚቾውን ለመቀጥቀጥ የሚያገለግል ቁስ ነው፡፡ ቁሶቹ የተለያዩ ተግባራትን በመከወን እንሰትን ወደ ምግብነት እንዲለወጥ በማድረግ በኩል ፍይዳ አላቸው፡፡

## 4.12.1.2. ከእንሰሳት ጋር የተያያዙ ቁሶች

በአንጥረኛ ባለሙያዎች የሚሰሩ ቁሶች የተለያየ አገልግሎት ይሰጣሉ፡፡ ቁሶቹ ከሚሰጡት አገልግሎት ውስጥ አንደኛው እንሰሳት ንቁ እንዲሆኑ ማስቻል ነው፡፡ እንሰሳትን ንቁ ከሚያደርጉ ቁሶች ውስጥ ቃጭሎች ተጠቃሽ ናቸው፡፡ ቃጭል በፈረስ አንገት ላይ በማድረግ ፈረሱ በተንቀሳቀሰ ቁጥር ቁሱ ይቅጨለጨላል፡፡ ሲቅጨለጨል ፈረሱ ነቃ ይላል፡፡ በጉዞ ላይም ፈጣን እንዲሆን ያግዘዋል፡፡

## 4.12.2. ባህላዊ አገልግሎት

የአንጥረኛ ባለሙያዎች የተለያዩ ብረታ ብረትን እተቀጣጠለ ከሰል ውስጥ በማስገባት በተለያየ መጠንና ቅርፅ ቁሶችን በእጃቸው ይሰራሉ፡፡ ቁሶቹ ቀድሞ ከታለመላቸው ዓላማ ባሻገር ማህበራዊ ደረጃን የመጠቆም አቅም አላቸው፡፡

### ጀግንነትን የሚጠቁሙ ቁሶች

በማህበረሰብ ውስጥ የጀግንነት ማዕረግ ከሚያሰጡ ተግባራት መካከል ሀገር እንዳይወረር በጦርና መሰል መሳሪያዎች የተዋጉ እንዲሁም ትላልቅና አደገኛ የሚባሉ የዱር እንሰሳትን ከጫካ ውስጥ የሚያድኑ የሚሉት ይገኙበታል፡፡ የአደን ተግባራቱን ለመከወን ከሚያገለግሉት መካከል  በአንጥረኛ ባለሙያዎች የሚሰራው  ጦር ተጠቃሽ ነው፡፡

**ጦር፡-**ይህ ቁስ መጠሪያው አንድ አይነት ይሁን እንጂ ቅርፁና አገልግሎቱ ግን የተለያየ ነው፡፡ የማህበረሰቡ ክፍሎች ሰብላቸውን ከጃርትና መሰል እንሰሳት ለመከላከል ጨልጨል ጦርን ሲጠቀሙ እንደ ሚዳቋ ያሉ ስጋቸው የሚበሉ የዱር እንሰሳትን ለማደን ደግሞ ሰንዳ ጦርን ይጠቀሙበታል፡፡ አዝመራውን የጠበቀና የዱር እንሰሳትን አድኖ ስጋ ያበሉ ማህበረሰቡ ጀግና የሚል ስያሜ ይሰጣቸዋል፡፡

### 4.12.3. ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ

በባለሙያዎቹ የሚሰሩ ቁሶች ለባለሙያዎቹም ሆነ ለተጠቃሚዎቹ የማህበረሰብ ክፍል ጥቅም ይሰጣሉ፡፡ ለባለሙያተኞቹ የሚሰጡት ጥቅም ቁሱን ለተጠቃሚዎቹ በመሸጥ ራሳቸውንም ሆነ ቤተሰቦቻቸውን ያስተዳድራሉ፡፡

በሌላ መልኩ ቁሱ ለተጠቃሚው ማህበረሰብ የተለያዩ ተግባራትን መከወኛነት ይውላል፡፡ ተጠቃሚዎቹ በአካባቢያቸው የሚያገኟቸውን ባለሙያዎች የሚፈልጉትን ቁሶች በሚፈልጉት መጠንና ቅርፅ ማሰራት ይችላሉ፡፡ በአካባቢው የሚገኙ የማህበረሰብ ክፍል አብዛኛዎቹ በእርሻ ስራ የሚተዳደሩ እንደመሆናቸው መጠን ቁሶቹ ዘርፈ ብዙ ግልጋሎት ያስገኛል፡፡ ስለ ቁሶቹ ጠቀሜታ አቶ ነጋ ተካ እንደሚከተለው ገልፀውታል፡፡ ‹‹እኔ ስድስት ልጆቼን የማስተዳድረው ብረት በመቀጥቀጥ ነው፡፡ ስራው አድካሚ እንኳ ቢሆንም ልጆቼን ለማሳደግ እየሰራሁ እገኛለሁ፡፡ ቁሶቹን ሰርቼ በመሸጥ ባለቤቴ እህል ትሸምትበታለች፡፡ ለእድር የሚከፈለውም ከዚሁ ስራ ከሚገኘው ገንዘብ ነው፡፡ ሌላ ከየት አለ›› (ቃ.መ.7/08/09 ቡኢ ዙሪያ)፡፡

## 4.13. በአንጥረኛ ባለሙያ የሚሰሩ ቁሶች ወቅታዊ ሁኔታ

የአንጥረኛ ባለሙያዎች ልምድ እያደገ በሄደ ቁጥርና የተጠቃሚው ማህበረሰብ ፍላጎት ሲያሻቅብ ቁሶቹን በተለያየ መልክ ሊሰሩ ይችላሉ፡፡ የቁሶቹን ወቅታዊ ሁኔታ መነሻ በማድረግ ቁሶቹን የሚሰሯቸው ባለሙያዎች በሁለት ከፍለዋቸዋል፡፡ እነሱም፡-ድሮ የሚሰሩና በአሁኑ ወቅት የመሰራት መጠናቸው የቀነሱ ቁሶች እንዲሁም ድሮ የማይሰሩና በአሁኑ ወቅት የሚሰሩ ቁሶች የሚሉት ናቸው፡፡

### 4.13.1.ድሮ የሚሰሩና በአሁኑ ወቅት የመሰራት መጠናቸው የቀነሱ ቁሶች

**ጦር፡-**በአንጥረኛ ባለሙያዎች ከሚሰሩ ቁሶች መካከል አንዱ ጦር ነው፡፡ ቁሱ በአሁኑ ወቅት የመሰራት መጠኑ የተመናመነ ነው፡፡ ድሮ ማህበረሰቡ ወደጫካ በመሄድ በጦር የዱር አራዊትን ያድኑ ነበር፡፡ ድኩላና ሚዳቆ በማደን ስጋውን ለምግብነት ሲያውሉት የከርከሮ ስጋን ደግሞ ለመድሃኒት ሲጠቀሙበት ኖረዋል፡፡ በአሁኑ ወቅት ጦር የሚያሰራ የማህበረሰብ ክፍል ቁጥር እጅጉን ቀንሷል በሚያስችል ደረጃ ላይ ይገኛል ይላሉ፡፡

## 4.13.2. ድሮ የማይሰሩና በአሁኑ ወቅት የሚሰሩ ቁሶች

**የብረት ድግር፡-**ይህ ቁስ በአሁኑ ወቅት ከሚሰሩ ቁሶች መካከል አንዱ ነው፡፡ ቁሱ መሰራት ከተጀመረ ሦስትና አራት ዓመታትን አስቆጥሯል፡፡ ከዚህ በፊት ድግር የሚሰራው እንጨትን አስተካክሎ በቅርፅ በመጥረብ ነበር አገልግሎት ሲሰጥ የኖረው፡፡ ቁሱ በአሁኑ ወቅትም አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛል፡፡ የአንጥረኛ ባለሙያዎች የእንጨት ድግር ብዙ ዓመት አገልግሎት አይሰጥም፡፡ በጎንና ጎን እያረሰ አይሄድም በሚል መነሻ እሳቤ የብረት ድግርን ሰራን ይላሉ፡፡

**የዕቃ መጫኛ ኮርቻ፡-** በአሁኑ ወቅት በስፋት የሚሰራ ቁስ ነው፡፡ የቀጫጭን ብረት ቱቦዎችን ጫፍ በማቅለጥ፣ በመቀጣጠልና አግዳሚውን በማያያዝ የእንግሊዘኛውን ፊደል W ቅርፅ እንዲይዝ ተደርጎ ይሰራል፡፡ አህያ ጀርባ ላይ በማድረግ ጋሪውን እንዲስብ የሚታሰርበት ነው፡፡ ከእንጨት የሚሰራው ኮርቻ እየተሰበረ በማስቸገሩ ባለሙያዎቹ የብረት ኮርቻን እንድንሰራ አስችሎናል ይላሉ፡፡

## 4.14. በአንጥረኝነት ስራ ላይ የባለሙያዎቹ ፆታዊ ተሳትፎ

የጥናቴ ርዕስ ባተኮረባቸው ቀበሌዎች ሁሉ የብረት ስራን የሚያከናውኑት ወንዶች ናቸው፡፡ የሴቶቹ ሚና የተሰራውን ቁስ ወደ ገበያ ቦታ ይዞ በመሄድ የመሸጥ ተግባር መከወን ነው፡፡ የአንጥረኝነት ስራ በወንዶች የሚከናወንበትን ምክንያት አቶ ተሰራ ፈረጃ(ቃ.መ.19/06/09 ዳሞ ቀበሌ)እንዲህ ገልፀውታል፡፡

> እግድህ የብረት ስራ ጉልበት ያስፈልገዋል፡፡ ያው ብረት ቅጥቀጣ አደል ስራችን ምን ሴቶች በባህል ክልክል ስለሆነ አያበጁም፡፡ መዶሻ ማንሳት እኮ ያስቸግራል፡፡ እኛ እኳ ለምደነዋል፡፡ ያው ከሴትና ወንድ ጠካራ ወንድ እማደል እንዴ ወንድ ጠንካራ በመሆኑ ብረት ይቀጠቅጣሉ፡፡ ሴት ብረት አትሰራም፡፡ ያው ዶማና ማረሻ የሚጠቀም ወንድ በርሻ ላይ ነው፡፡ እኛ እምናበጀው ይታደሳል፡፡ ወንድ ያው አድ ሁለት ቢያገባና ቢፈታ ያው እድሉ ተበላሸ አይባልም፡፡ ሴቶች ከሆኑማ እድሏ አይ አንጉል ሆናለች፡፡

በክስታኔ ማህበረሰብ ውስጥ የጉልበት መጠንንና ባህልን መነሻ በማድረግ የስራ ክፍፍል ያደርጋሉ፡፡ በአንጥረኛነት ሙያ ላይ የወንዶቹ ሚና ለምን ከፍተኛ ሊሆን ቻለ? የሚለው ጥያቄ መነሻ በማድረግ የማህበረሰቡን አስተሳሰብ ለመመርመር ያስችለናል፡፡ በአንጥረኝነት

ሙያ ላይ የወንዶች ሚና ከፍተኛ የሆነው በሚከተሉት ምክንያቶች እንደሆነ መረዳት ያስችለናል፡፡ የከሰል እንጨት ፈለጣና በመዶሻ ብረትን መቀጥቀጥ ጠንከር ያለ ጉልበትን የሚጠይቅ ተግባር  መሆኑ ፣አብዛኛዎቹ በአንጥረኛ ባለሙያዎች የሚሰሩ ቁሶች ወንዶች ለእርሻና አደን ተግባር የሚገለገሉባቸው መሆናቸው አንደኛው ምክንያት ነው፡፡

ማህበረሰቡ ወንዶች በተፈጥሮ ሰውነታቸው ጥንካራ ነው ብለው ስለሚያምኑና በብረት የሚመስሏቸው መሆኑ ሌላኛው ምክንያት ነው፡፡ በሌላ መልኩ በአንጥረኛ ባለሙያዎች የሚሰሩ ቁሶች የመታደስ እድል አላቸው፡፡ ይህን የወንዶች ትዳር ሲፈርስ ወዲያውኑ መታደስ ከመቻሉ ጋር ያገናኙታል፡፡ አብዛኛዎቹ የሸክላ ቁሶች የመታደስ እድል የላቸውም፡፡ ይህም ሴቶች ትዳራቸውን ሲያፈርሱ ወዲያውኑ ትዳር ካለመመስረታቸው ጋር ይያያዛል ይላሉ፡፡

# 5.ማጠቃለያና የይሁንታ ሃሳብ

በዚህ ክፍል ውስጥ ጥናቱ የቁሶቹን አሰራርና አገልግሎት፣ የቁሶቹን መነሻ ቅርፅ እንዲሁም ቁሶቹ የማህበረሰቡን የህይወት ፍልስፋና በምን መልኩ ያሳያሉ? የሚሉትን ጉዳዮች ተመልክቶ የተገኙት ፍሬ ሃሳቦች የቀረቡበት ክፍል ነው፡፡ የጥናቱን ግኝትና ጥናቱ በተከናወነበት አካባቢ ላይ ለቀጣዩ ቢሰሩ መልካም ነው ያልኳቸውን ይሁንታዎች ታክለው ቀርበዋል፡፡

## 5.1. ማጠቃለያ

ይህ ጥናት ባህላዊ የሸክላና አንጥረኝነት ስራ በክስታኔ ማህበረሰብ በሚል ርዕስ የተከናወነ ነው፡፡ የጥናቱ ዋና ዓላማ አድርጌ የተነሳሁት በሸክላና አንጥረኛ ባለሙያዎች የሚሰሩ ቁሶች አሰራርና አገልግሎት መተንተን እንዲሁም በቁሶቹ አማካኝነት የማህበረሰቡን የህይወት ፍልስፋና መመርመር ነው፡፡ ቁሳዊ ባህል ከሚጠናባቸው ንድፈ ሃሳቦች ውስጥ ተግባራዊ ንድፈ /Functional theory/ ጥቅም ላይ ውሏል፡፡ በምልከታ፣ቃለ መጠይቅና ተተኳሪ ቡድን ውይይት የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች የተሰበሰቡት መረጃዎች ገላጭ የምርምር ዘዴን በመጠቀም ተተንትነዋል፡፡

ጥናቱ ባተኮረባቸው ቦታዎች ላይ በሸክላና አንጥረኛ ባለሙያዎች የሚሰሩ ቁሶች አሰራርና አገልግሎት ተመሳሳይነት ያላቸው መሆኑ ታውቋል፡፡

ማህበረሰቡ በመገልገያ ቁሶቹ አማካኝነት ማህበራዊ ቦታቸውን፣ኢኮኖሚያዊ ደረጃቸውንና ባህላዊ አኗኗራቸውን የሚያሳዩባቸው መሆናቸውን በጥናቱ ታውቋል፡፡

በክስታኔ ማህበረሰብ የአማች መመገቢያ ጣባ ጌጥ ይደረግበታል፡፡ የጌጡ ትዕምርት ከዘመድ ይልቅ ለአማች በተለይም ላልወለደ አማች ትልቅ ክብር የሚሰጡ መሆናቸው ማሳያ እንደሆነ ጥናቱ አሳውቋል፡፡

በነክብ ቁስ ከአባወራው ውጪ ሌሎች ሰዎች የማይመገቡበት ምክንያት የአባወራውን ክብር ለማሳያ ነው፡፡ አባዎራዎችና እማወራዎች በለቅሶ፣በሰርግና መሰል ጉዳዮች ላይ በእግር በሚጓዙበት ወቅት አባወራዎች ከፊት እማወራዎች ደግሞ ከኋላ እየተከተሉ የሚሄዱ መሆናቸውን ጥናቱ አረጋግጧል፡፡ ሚስት ባለቤቷን የምትጣራው አንቱ ወይም በመጀመሪያ ልጃቸው ስም የእገሌ አባት በማለት መሆኑ ታውቋል፡፡

በ‹‹አፈሳ›› አፈር ተበጥብጦ የጠለለው ውሃ ጎመን ሲቀቀል ከማሳ በሚቀጠፍበት ወቅት የነበረውን መልክ እንዲይዝ የሚያስችል መሆኑ ታውቋል፡፡ ቁሶቹ በበቀሉበት ማህበረሰብ ውስጥ ከተሰሩበት ተቀዳሚ ፋይዳ ባሻገር ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ደረጃቸውን የሚያመለክቱ መሆናቸው ታውቋል፡፡

በክስታኔ ማህበረሰብ ጎመን ተራ ውስጥ ሴቶች እንጂ ወንዶች የማይገቡበት ምክንያት የኢኮኖሚያዊ ደረጃን ለማመልከት መሆኑን ጥናቱ አረጋግጧል፡፡

የሸክላ ስራ በሴቶች የሚከናወነው አብዛኛዎቹ ቁሶች በቤት ውስጥ አገልግሎት የሚሰጡ በመሆናቸውና የአሰራር ሂደታቸውም ከቤት ውስጥ ስራ ጋር ተመሳሳይነት ያላቸው በመሆናቸው ምክንያት መሆኑ ታውቋል፡፡

የሸክላ ባለሙያዎች አደይ ሲፈነዳ ስራቸውንና ቀያቸውን ለቀው ጥቅምት አምስት ቀን የሚመለሱት ልመና ካልወጣን ርሃብና በሽታ በቤታችን ውስጥ ይገባል የሚል አስተሳሰብ ያላቸው መሆናቸውን በጥናቱ ታውቋል፡፡

የሸክላ ባለሙያዎች እየሱስ ክርስቶስ የተቀበረበትን መሬት የአንጥረኛ ባለሙያዎች ደግሞ የተሰቀለበትን ችንካር ሰጥተዋል በሚል ምክንያት ከሙያው ውጪ ያሉ የማህበረሰብ ክፍሎች እንደሚያገሏቸው ታውቋል፡፡

በአንጥረኛ ባለሙያዎች የሚሰራው ማጭድ መነሻ ቅርፁ በጋማ ከብቶች ድድ ላይ ተደርድረው የሚገኙ ጥርሶች መሆናቸውን ተረጋግጧል፡፡

የአንጥረኝነት ሙያ በወንዶች የሚተገበረው ብረት መቀጥቀጡ ጉልበትን የሚጠይቅ በመሆኑና አብዛኛዎቹ ቁሶች ለእርሻና አደን ተግባር ለመከወኛነት የሚያገለግሉ በመሆናቸው ምክንያት መሆኑ ታውቋል፡፡

እንሰት ለክስታኔ ማህበረሰብ ልዩ ትርጉም ያለውና ከህይወታቸው ጋር በእጅጉ የተቆራኘ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ የእንሰቱ ቅጠሉ ለከብቶች ምግብ፣ቅቤና አይቤ ለመያዣነት የሚያገለግል መሆኑን፤ ልጡ ደግሞ ለተለያዩ የቤት ውስጥ ማረፊያ ቁሶችን ለመስሪያነት የሚውል መሆኑን በጥናቱ ተረጋግጧል፡፡ የእንሰቱ ስር/የታችኛው ክፍሉ/ ለምግብነትና ለተለያዩ በሽታዎች መድሃኒትነት የሚጠቀሙበት መሆናቸውን ጥናቱ አረጋግጧል፡፡

## 5.2. የይሁንታ ሃሳብ

በሽክላና አንጥረኛ ባለሙያዎች የሚሰሩ ቁሶች የማህበረሰቡን የህይወት ፍልስፍና የሚያሳዩ መሆናቸው ታውቋል፡፡ ባለሙያዎቹ ቁሶቹን ሲሰሩ በአካባቢያቸው የሚመለከቱትን ቅርፅ መነሻ አድርገው ነው፡፡ ቁሶቹ ጥቅል የሆነ ለውጥ እንዳይከሰትባቸው የሚከተሉትን የይሁንታ ሃሳቦችን ሰንዝሬአለሁ፡፡

- የሀገር ሽማግሌዎችና የሚመለከታቸው አካላት በውህደት በሸክላና አንጥረኛ ባለሙያዎች የሚሰሩ ቁሶች የማንነት መግለጫ መሆናቸውን ለማህበረሰቡ ተከታታይ ግንዛቤ ቢፈጥሩ
- የማህበረሰቦቹን አስተሳሰብ በሚመለከተው አካል ተጠንቶ ለማህበራዊ መረጋጋት ማራመጃነት ቢገለገሉበት
- የሀገር ሽማግሌዎች፣ባህልና ቱሪዝም እንዲሁም ጥቃቅንናንግድ ጽ/ቤት ውህደት ፈጥረው ቁሶቹ በቅርስነት የሚቀመጡበት ሁኔታ ቢመቻች
- የሀይማኖት አባቶችና የሚመለከታቸው አካላት በሸክላ ባለሙያዎች የሚሰራውን የቤተክርስቲያን ጉልላትና ጥዋ እያነሱ ማህበረሰቡ ባለሙያዎቹን እንዲያበረታቱ ቢያስተምሩ
- የወረዳው ባህልና ቱሪዝም ጽ/ቤት ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ጥምረት በመፍጠር ስለሸክላና አንጥረኛነት ስራ የሚያበረታቱ ድራማዎችን በቪድዮ ቀርፀው ማህበረሰቡ በብዛት በሚገኙባቸው ቦታዎች ላይ እንደ አመቺነቱ ቢያሳዩ
- የወረዳው ጥቃቅንና ንግድ ኢንዱስትሪ ጽ/ቤት ተተኪ ባለሙያዎችን ለማፍራት የገንዘብ አቅርቦት ቢያመቻቹላቸው
- በትምህርት ቤት ውስጥ የባህል ጥናት የሚባል ክበብ ቢቋቋምና ቀጣይነት ባለው ሁኔታ ተግባራዊ ቢደረግ ጥሩ ውጤት ይመጣል የሚል ሃሳብ አለኝ፡፡

# ዋቢ ጽሑፎች


ሀብታሙ እንግዳው፤ ‹‹በደቡብ ጎንደር ዞን በሊቦ ከምከም ወረዳ ሻሞ ጉድጓዲት ገጠር ቀበሌ የሻሞ መድሃኒአለም ሸክላ ስራ ውጤቶች የአሰራር ሂደትና ጠቀሜታ››፤ ለኢትዮጵያ ሥነ ፅሁፍና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት ለማስተርስ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣2001፡፡

መሰረት ብርሃኔ፤‹‹ሽመናና አንጥረኝነት በጃና አሞራ ወረዳ››፤ለኢትዮጵያ ሥነ ፅሁፍና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት ለማስተርስ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት ፣አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ 2003፡፡

ሞገስ ዕቁቤ ጊዮርጊስ /ሊቀ መዘምራን/፤*ስነ ፍጥረት፤* አዲስ አበባ፣ንግድ ማተሚያ ቤት፣1987፡፡

በደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/መ በብሔረሰቦች ምክር ቤት በባህልታሪክና ቅርስ ጥናት ተቋም፤*የደቡብ ብሔሮች ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ፕሮፋይል*፤ሃዋሳ፣ፍቅረ ሰላም ማተሚያ ቤት፣2001፡፡

አስቴር ሙሉ፤‹‹ባህላዊ ቤቶችና ከሸክላ የተሰሩ የቤት ቁሳቁሶች በዘጌ ባህረ ሰላጤ››፤ ለኢትዮጵያ ሥነ ፅሁፍና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት ለማስተርስ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት፣አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣2000፡፡

አብይ አክሊሉ፤‹‹የክስታኔ ማህበረሰብ የቤት ውስጥ መገልገያ ቁሶች ጥናት››፤ለኢትዮጵያ ሥነ ፅሁፍና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት ለማስተርስ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት፣አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣2004፡፡

ወርቁ ተስፍዬ፤ *አይመለል*፤አዲስ አበባ፣ንግድ ማተሚያ ድርጅት፣1987፡፡

የሶዶ ወረዳ ፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ጽ/ቤት የተዘጋጀ፤*የስነ ሕዝብ ቡክሌት*፤ገፅ 31፣2009፡፡

ደግሰው ጥላሁን፤‹‹ባህላዊ የሸክላና ቆዳ ስራ በቡሬና ወንበርማ ወረዳ››፤ለኢትዮጵያ ሥነ ፅሁፍና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት ለማስተርስ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት ፣አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣2003፡፡

ድንበሩ ዓለሙ እና ሌሎች፤ *ጎጎት የጉራጌ ሕዝቦችታሪክ፣ባህልና ቋንቋ*፤ አዲስ አበባ፣ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት፣1987።

ፈቃደ አዘዘ፤ *የስነቃል መምሪያ*፤አዲስ አበባ፣ቦሌ ማተሚያ ድርጅት፣1991።

Ames,L. Kenneth. “Meaning in Artifacts;Hall Furnishings In Victorian America.” In Journal of Interdisciplinary History; Vol.Ix; No.1.pp.19-46;1978.

Beals,L. Ralph and Harry Hoijer. *An Introduction to Anthropology*. Los Angeles, University of California.1958.

Bricks, Tony*.The Art of the Modern potter*.London;Country Life Limited,1967.

Cleary,Mc Ann. “Material Culture” on line.WWW.http://Mc.Ann Cleary,html.2004. Saturday, March 11, 2017, 8:25:14 PM

Copper,Emmanuel. *A History of world pottery*.London:BT.Bats ford limited,1981.

Dorson,M.Richard/ed/. *FoLklore and Folk life:An Introduction*.Chicago and London; The university of Chicago press.1972.

Federal Democratc Republic of Ethopia Population Census Commission Central Statistical Agency.2007.

Fleming,E.McClung.“Artifact study;A proposed model.’’ Available on line at: URL:http//WWW.jstor.org/view/00840416/pdf.Saturday, March 11, 2017, 7:07:21 PM

Gedef Abawa,An Ethnoarchaeological Investigation of pottery making Among Traditional potters of Gondar. Department of Archaeology, M.A. Thesis, Addis Ababa university; 2005.

Glassie, Henry.Folkloristic study of the American Artifact;objects and objectives In *Hand book of American Folklore*. Richard M.Dorson/ed/. Bloomington; India University press,1983.

__________. *Material culture*.Bloomington and Indian polis, Indiana University Press; 1999.

Prown,J.David. “Mind in Matter: An Introduction to Material culture Theory and Method.›› Available on line at:URL:LttP;//WWW.Jstor.org/about/terms.html. PP.7-10; Saturday, March 11, 2017, 7:23:20 PM

Roberts,E.Warren. “Folk crafts››In Floklore and *Folk life;An Introduction*.Dorson Richard’s/ed./,Chicago and London;The university of Chicago press.1972.

Marchese,Ronald T.“Material culture and Artifact classification.” *In American Material culture;The shape of Things Around us*. Edith Mayo/ed./.Bowling Green;Bowling Green state university popular press.1984.

Mayo,Edith.*American Material Culture;The Shape of Things Around Us.*Bowling Green state university popular press.1984.

Noble,Joseph veach.*The Techniques of painted Attic pottery.*London:Faber and Faber Limited,1966.

Schelter,Thomas.“Understanding the nine models of material culture Interpetation”on line. Available at:http//WWW.btnep.org. PP.7-8; Saturday,March 11,2017,7:01:43 PM

Somjee,Sultan.*Material culture of Kenya*.Nirobi;East African Educational Publishers ,1993.

Takele Merid. Gendered culture pottery as women’s Activity in Ethiopia:A case Study of selected cites in Addis Ababa and its surroundings.Addis Ababa University;School of Graduate studies,MA.Thesis in Ethiopian Studies,2007.

Woodward,Jan.*Understanding Material Culture*. London, sage publications;2007.

# አባሪዎች

## አባሪ 1 ለሸክላ ባለሙያዎች የቀረቡ መሰረታዊ ጥያቄዎች

1 ሙሉ ስም፣ዕድሜ፣የልጆች ብዛት፣መኖሪያ አካባቢ?

2 የሸክላ ቁሶችን ስትሰሩ ምን ምን ትጠቀማላችሁ?

3 የሸክላ ስራ በሴቶች ብቻ የሚሰራበት ምክንያት ምንድን ነው?

4 የሸክላ ስራ ደረጃዎች ምን ምን ናቸው?

5 አደይ ሲፈነዳ የሸክላ ስራችሁንና ቤታችሁን ለቃችሁ የምትሄዱት ለምንድን ነው?

6 የምትሰሯቸው የሸክላ ቁሶች ምን ምን አገልግሎት አላቸው?

7 በሸክላ ቁሶች ላይ የተለያዩ ቅርፃችን  የምትሰሩት  ለምንድን ነው?

8 የሸክላ አፈር ስትቆፍሩ በቡድን ነው ወይስ በግል ለምን?

## አባሪ 2 ለአንጥረኛ ባለሙያዎች የቀረቡ መሰረታዊ ጥያቄዎች

1 ሙሉ ስም፣ዕድሜ፣የልጆች ብዛት፣መኖሪያ አካባቢ?

2 የብረት ቁሶችን ስትሰሩ ምን ምን ትጠቀማላችሁ?

3 ቁሶቹን ከብረት ስትሰሩ ምን አገልግሎት እንዲሰጡ አስባችሁ ነው?

4 ጥሬ እቃዎቹን በተለያየ መጠንና ቅርፅ ለመስራት የሚታለፉ ደረጃዎች ምን ምን ናቸው?

5 የአንጥረኝነት ሙያ በወንዶች የሚከናወነው ለምንድን ነው?

6 ድሮ ይሰሩ የነበሩና በአሁኑ ወቅት የማይሰሩ ቁሶች ምን ናቸው ለምን?

7 ድሮ የማይሰሩና በአሁኑ ወቅት ግን የሚሰሩ ቁሶች ምን ምን ናቸው ለምን?

8 የቁሶቹ ተጠቃሚዎች ለቁሶቹ ያላቸው አመለካከት ምን ይመስላል?

10 ቁሶቹን በመስራታችሁ ያገኛችሁት ጥቅም ምንድን ነው?

## አባሪ 3 ለሀገር ሽማግሌዎችናታሪክ አዋቂዎች የቀረቡ መሰረታዊ ጥያቄዎች

1 የክስታኔ ማህበረሰብ መነሻ ታሪክ ምን ይመስላል?

2 በክስታኔ ማህበረሰብ ምን ምን የሃይማኖት አይነቶች አሉ ?

3 በክስታኔ ማህበረሰብ ውስጥ ባህላዊ የሽምግልና ስርዓት ምን ይመስላል?

4 የክስታኔ ማህበረሰብ መተዳደሪያ ምን ምን ናቸው?

5 የመስቀል በዓል በክስታኔ ማህበረሰብ ውስጥ በምን አይነት ሁኔታ ይከበራል?

6 የሸክላ ባለሙያዎች አደይ ሲፈነዳ ስራቸውንና ቀያቸውን ለቀው የሚሄዱት ለምንድን ነው?

7 በሸክላና አንጥረኛ ባለሙያዎች የሚሰሩ ቁሶች ለማህበረሰቡ ምን ምን አገልግሎት ይሰጣሉ?

8 በሸክላና አንጥረኛ ባለሙያዎች የሚሰሩ ቁሶች ከእለት ግልጋሎት ውጪ ምን ጠቀሜታ አላቸው?

9 የሸክላና አንጥረኛ ባለሙያዎች ከጎርዴና ሴራ ውጪ እንዲመርቁ የሚፈለጉት ለምንድን ነው?

10 በሸክላ ባለሙያዎች ለሚሰሩ ቁሶች ማህበረሰቦቹ ያላቸው አመለካከት ምንድን ነው?

## አባሪ 4 ለወረዳው ባህልና ቱሪዝም ጽ/ቤት የቀረቡ መሰረታዊ ጥያቄዎች

1.በሸክላና አንጥረኛ ባለሙያዎች የሚሰሩ ቁሶች የማህበረሰቡን አኗኗር በምን መልኩ ያሳያሉ?

2 በሸክላና አንጥረኛ ባለሙያዎች ለሚሰሩ ቁሶች ማህበረሰቡ ያላቸው አመለካከት ምን ይመስላል?

3 በሁለቱ ባለሙያዎች የሚሰሩ ቁሶች ሙሉ በሙሉ ለውጥ እንዳይከሰትባቸው ያከናወናችሁት ተግባር ካለ ብገልፁልኝ ከሌለ ለምን?

4 የሸክላ ስራ በሴቶች አንጥረኝነት ደግሞ በወንዶች የሚሰራው ለምንድን ነው?

5 የሽክላና አንጥረኛ ባለሙያዎች ቁሶችን ሲሰሩ መነሻ የሚያደርጉት ቅርፅ ምንድን ነው?

## አባሪ 5 ለወረዳው ጥቃቅንና ንግድ ኢንዱስትሪ ጽ/ቤት የቀረቡ ጥያቄዎች

1 በሸክላና አንጥረኛ ባለሙያዎች የተለያዩ ቁሶችን እንዲሰሩ ምን አይነት ድጋፍ ታደርጋላችሁ?

2. የሸክላና አንጥረኛ ባለሙያዎች ተተኪን እንዲያፈሩ የተከናወነ ተግባር ካለ ብትገልፁልኝ ከሌለ ለምን?

3. በሸክላና አንጥረኛ ባለሙያዎች የሚሰሩ ቁሶች ለማህበረሰቡ የሚሰጡት አገልግሎት ምንድን ነው?

4. የሸክላና አንጥረኛ ባለሙያዎች ቁሶቹን ሲሰሩ መነሻ የሚያደርጉት ቅርፅ ምንድን ነው?

## አባሪ 6 በሸክላና አንጥረኛ ባለሙያዎች የሚሰሩ ቁሶችና አገልግሎታቸው

| ተ.ቁ | የቁሶቹ ስም | የቁሶቹ አገልግሎት |
|---|---|---|
| 1 | ኮለሊት | ጎመን ለመቀቀያ የሚያገለግል ቁስ ነው፡፡ |
| 2 | ኩሮ | የተነጠረ ቅቤ በአፍንጫ ቀዳዳ የሚሳብበት ቁስ ነው፡፡ |
| 3 | ደንጋሳ | በመስቀል በዓል ልጆች የሚመገቡበት ቁስ ነው፡፡ |
| 4 | ነክብ | አባዎራዎች ክትፎና አይቤ የሚመገቡበት ቁስ ነው፡፡ |
| 5 | ጥወ | ሀብታሞች የነጠረ ቅቤ የሚያስቀምጡበት ቁስ ነው፡፡ |
| 6 | እንጨቡዬ | በድሃ ቤት የተነጠረ ቅቤ የሚቀመጥበት ቁስ ነው፡፡ |
| 7 | ክርን | ወተትና እርጎ መጠጫ ቁስ ነው፡፡ |
| 8 | ትክዬ | ስጋና ንፍሮ መቀቀያ ቁስ ነው፡፡ |
| 9 | መስመስያ | ለጠላ መጠጫ የሚያገለግል ቁስ ነው፡፡ |
| 10 | ጋውዝየ | ቁሶችን የሚሸከም ጉልቻ |
| 11 | ሽሽት | አረቄ ሲወጣ ኮዳው እንዲቀዘቅዝ የሚቀመጥበት ነው፡፡ |

በአንጥረኛ ባለሙያዎች የሚሰሩ ቁሶችና አገልግሎታቸው

| ተ.ቁ | የቁሶቹ ስም | የቁሶቹ አገልግሎት |
|---|---|---|
| 1 | ሰንዳ | ለእንሰት መቁረጫ የሚያገለግል ነው፡፡ |
| 2 | ወለት | የደረሰ እንሰት የሚነቀልበት ቁስ ነው፡፡ |
| 3 | ቆፋሪ | ለእንሰት መኮትኮቻነት የሚያገለግል ቁስ ነው፡፡ |
| 4 | የብረት ሲቢሳ | የእንሰት ቃጫ የሚለይበት ቁስ ነው፡፡ |
| 5 | ቁንጥል | የእንሰት ሽፍንን በቅርፅ ለማውጣት የሚያገለግል ነው፡፡ |
| 6 | የብረት ዣግባ | ሃሚቸውን ለመቀጥቀጥ የሚያገለግል ቁስ ነው፡፡ |
| 7 | ጨልጨል ጦር | ስጋቸው የማይበሉ እንሰሳትን ለማደኛነት የሚያገለግል ነው |
| 8 | ሰንዳ ጦር | ስጋቸው ለሚበሉ እንሰሳት ማደኛነት የሚውል ቁስ ነው፡፡ |
| 9 | ማሊሲ ጦር | ከፈረስ ጋር ለጌጥ የሚያዝ ቁስ ነው፡፡ |

## አባሪ 7 የአውራ መረጃ አቀባዮች ዝርዝር

| ተ.ቁ | ሙሉ ስም | ፆታ | እድሜ | መኖሪያ | የስራ ድርሻ | ሰዓት | ቀን | ወር | ዓ.ም |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | አቶ ተሰራ ፈረጃ | ወ | 65 | ዳሞ | አንጥረኛ | 8:00-9:00 | 19 | 06 | 2009 |
| 2 | አቶተመስገን ዳልደቦ | ወ | 45 | ዳሞ | አንጥረኛ | 5:00-6:05 | 19 | 06 | 2009 |
| 3 | አቶ ግዛው ኡርጌሳ | ወ | 49 | ዳሞ | አንጥረኛ | 2:00-4:00 | 9 | 08 | 2009 |
| 4 | አቶ ለማ አንጨሞ | ወ | 37 | ዳሞ | አንጥረኛ | 8:00-9:00 | 9 | 06 | 2009 |
| 5 | አቶ አጉሌ ጣሳው | ወ | 56 | ዳሞ | አንጥረኛ | 2:00-4:05 | 8 | 05 | 2009 |
| 6 | አቶ ገዛኸኝ በእምነቱ | ወ | 34 | ዳሞ | አንጥረኛ | 2:00-4:05 | 8 | 05 | 2009 |
| 7 | አቶ ደጋጋ ኡርጌሳ | ወ | 53 | ዳሞ | አንጥረኛ | 8:00-9:00 | 8 | 05 | 2009 |
| 8 | አቶ አዱኛ ጉግሳ | ወ | 40 | ዳሞ | አንጥረኛ ናታሪክ አዋቂ | 8:00-9:30 | 11 | 05 | 2009 |
| 9 | አቶ ደሴ አንጨሞ | ወ | 41 | ዳሞ | አንጥረኛ | 2:00-3:00 | 11 | 05 | 2009 |
| 10 | አቶ ትርፌ ጌታሁን | ወ | 59 | ኬላ | አንጥረኛ | 3:05-4:10 | 6 | 06 | 2009 |
| 11 | አቶ ተሾመ ደበላ | ወ | 51 | ኬላ ዙሪያ ቀበሌ | አንጥረኛ | 5:05-4:00 | 1 | 06 | 2009 |
| 12 | አቶ ዱረሳ ተመስገን | ወ | 31 | ኬላ ዙሪያ ቀበሌ | አንጥረኛ | 8:00-10:00 | 1 | 06 | 2009 |
| 13 | አቶ መንግስቴ አብዬ | ወ | 54 | ኬላ ዙሪያ ቀበሌ | አንጥረኛ | 2:00-3:05 | 17 | 05 | 2009 |
| 14 | አቶ ሞላ እንዳለ | ወ | 63 | ኬላ ዙሪያ ቀበሌ | አንጥረኛ | 5:00-6:00 | 4 | 06 | 2009 |
| 15 | አቶ ሰብስቤ በየነ | ወ | 66 | ቡኢ ዙሪያ ቀበሌ | አንጥረኛ | 5:00-6:00 | 14 | 05 | 2009 |
| 16 | አቶ ነጋ ተካ | ወ | 56 | ቡኢ ዙሪያ ቀበሌ | አንጥረኛ | 8:00-9:00 | 7 | 08 | 2009 |
| 17 | ያለው ነጋ | ወ | 25 | ቡኢ ዙሪያ ቀበሌ | አንጥረኛ | 8:00-9:00 | 18 | 05 | 2009 |
| 18 | አቶ ባለእዳ ተካ | ወ | 54 | ቡኢ ዙሪያ ቀበሌ | አንጥረኛ | 4:05-6:00 | 18 | 05 | 2009 |
| 19 | ወ/ሮ ገረዶ በጃበጅ | ሴ | 48 | ዋጮ ቀበሌ | ሸክላ | 8:00-9:15<br>4:00-5:00<br>8:00-10:00 | 26<br>8<br>28 | 07<br>06<br>07 | 2009<br>2009<br>2009 |
| 20 | ወ/ሮ በዜ ሶሪ | ሴ | 54 | ዋጮ ቀበሌ | ሸክላ | 5:00-6:10 | 25 | 07 | 2009 |
| 21 | ወ/ሮ ቡላል ሶሪ | ሴ | 49 | ዋጮ | ሸክላ | 8:00-10:00 | 4 | 08 | 2009 |

| | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | ቀበሌ | | 4:00-5:00 | 28 | 07 | 2009 |
| 22 | ወ/ሮ ክቡ እንዳለ | ሴ | 48 | ዋጮ ቀበሌ | ሽክላ | 4:00-5:00 | 11 | 06 | 2009 |
| 23 | ወ/ሮ ኮኮቤ አርጋቸው | ሴ | 62 | ዋጮ ቀበሌ | ሽክላ | 8:00-9:15 | 26 | 07 | 2009 |
| 24 | ወ/ሮ ገረዶ ታዴ | ሴ | 53 | ዋጮ ቀበሌ | ሽክላ | 8:00-10:00 | 10 | 06 | 2009 |
| 25 | ወ/ሮ በለጡ አርጋው | ሴ | 56 | ሱተን ዙሪያ ቀበሌ | ሽክላ | 8:00-10:15 | 29 | 07 | 2009 |
| 26 | ወ/ሮ መሰሉ እንዳለ | ሴ | 43 | ሱተን ዙሪያ ቀበሌ | ሽክላ | 4:00-5:10 | 2 | 08 | 2009 |
| 27 | ወ/ሮ እሸቴ ኩራዝ | ሴ | 64 | ቆላ ኑረና ቀበሌ | ሽክላ | 5:00-6:30<br>8:00-10:00<br>8:00-10:00 | 19<br>20<br>5 | 05<br>05<br>06 | 2009<br>2009<br>2009 |
| 28 | ወ/ሮ አዩሽ ንጋቱ | ሴ | 47 | ቆላ ኑረና ቀበሌ | ሽክላ | 2:00-4:00<br>8:00-9:30 | 20<br>21 | 07<br>05 | 2009<br>2009 |
| 29 | ወ/ሮ ምንጩ ረጋሳ | ሴ | 35 | ቆላ ኑረና ቀበሌ | ሽክላ | 8:00-10:00<br>4:00-5:00 | 22<br>5 | 07<br>06 | 2009<br>2009 |
| 30 | ወ/ሮ ዋጋነሽ ኢታሞ | ሴ | 90 | ቆላ ኑረና | ሽክላ | 2:00-3:00 | 14 | 08 | 2009 |
| 31 | አቶ ፀጋዬ ታቦር | ወ | 62 | ቡኢ | በባህልና ቱሪዝም ጽ/ቤት<br>በሪከርድ ም/ሥ/አ ደራጅ ኦፊሰርና ታሪክ አዋቂ | 5:00-6:30<br>8:00-10:00 | 10<br>9 | 05<br>05 | 2009<br>2009 |
| 32 | ወ/ሮ የውብ ኮርቡ | ሴ | 45 | ቡኢ | የሶዶ ወረዳ ባ/ቱ/መ/ኮ/ጉ/ጽ/ቤት ሃላፊ | 3:00-4:00 | 5 | 05 | 2009 |
| 33 | ወ/ሮ እልፍነሽ ደኔ | ሴ | 85 | ኬላ | ታሪክ አዋቂ | 3:00-5:00<br>5:00-6:00 | 21<br>17 | 07<br>06 | 2009<br>2009 |
| 34 | ወ/ሮ ዘርጊ ተረዳ | ሴ | 86 | ኬላ | ታሪክ አዋቂ | 3:00-5:30<br>5:00-6:00 | 24<br>5 | 07<br>08 | 2009<br>2009 |
| 35 | አቶ ታደለ ወርቂ | ወ | 72 | ኬላ | የሃገር ሽማግሌና | 3:00-4:00 | 20 | 07 | 2009 |

| | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | ታሪክ አዋቂ | 8:00-10:00<br>9:00-11:00<br>8:00-9:00 | 17<br>27<br>30 | 08<br>07<br>07 | 2009<br>2009<br>2009 |
| 36 | አቶ ቡርቃ በዳሶ | ወ | 90 | ኬላ | ታሪክ አዋቂና የሃገር ሽማግሌ | 2:00-3:00 | 18 | 05 | 2009 |
| 37 | አቶ ታከለ ደኜ | ወ | 68 | ኬላ | ጡረተኛና ታሪክ አዋቂ | 9:00-11:00<br>5:00-6:00 | 17<br>16 | 05<br>06 | 2009<br>2009 |

## ንዑስ የመረጃ አቀባዮች ዝርዝር

| | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 38 | ወ/ሮ እንዳሻሽ ጌታሁን | ሴ | 43 | ሱተን ዙሪያ | ታሪክ አዋቂ | 4:00-5:30 | 13 | 08 | 2009 |
| 39 | ወ/ሮ ትዕግስት ወልዴ | ሴ | 32 | ቡኢ | መንግስት ሰራተኛ | 5:00-6:00 | 5 | 5 | 2009 |
| 40 | አቶ ሲሳይ ዘውዴ | ወ | 58 | ኬላ | ታሪክ አዋቂ | 8:00-9:00 | 28 | 05 | 2009 |
| 41 | ወ/ሮ መዓዛ ቡርቃ | ሴ | 47 | ኬላ | ታሪክ አዋቂ | 3:00-5:00 | 15 | 05 | 2009 |
| 42 | ወ/ሮ ድባቤ ይፋ | ሴ | 85 | ቆላ ኑረና | ታሪክ አዋቂ | 5:00-5:30 | 11 | 08 | 2009 |
| 43 | ወ/ሮ ስኳሬ ብሔ | ሴ | 56 | ኬላ | ታሪክ አዋቂ | 8:00-9:00 | 10 | 08 | 2009 |
| 44 | ወ/ሮ የትምወርቅ ሲሳይ | ሴ | 41 | ኬላ | ታሪክ አዋቂ | 9:00-10:30 | 23 | 07 | 2009 |
| 45 | ወ/ሮ አሰፌ ቡርቃ | ሴ | 38 | ኬላ | ታሪክ አዋቂ | 2:00-3:00 | 12 | 08 | 2009 |
| 46 | አቶ ደበላ ቁፍ | ወ | 90 | ኬላ | ታሪክ አዋቂ | 9:00-11:00 | 13 | 05 | 2009 |

## አባሪ 8 የፎቶ ንባብ

### የሀገር ሽማግሌዎችና ታሪክ አዋቂዎች በቃለ መጠይቅ ላይ



አቶ ፀጋዬ ታቦር



አቶ ታከለ ደኔ



አቶ ታደለ ወርቁ



ወ/ሮ እልፍነሽ ደኔ



አቶ ቡርቃ በዳሶ



አቶ አዱኛ ጉግሳ



ወ/ሮ ዋጋነሽ ኢታሞ ቁሶችን በመተኮስ ላይ



ወ/ሮ ምንጩ ረጋሳ ቁሶችን በመተኮስ ላይ



የሸክላ ቁሶች በቤ ሲተኮሱ



የወጨት፣ደንጋሳና ባለ አንድ ጡት ጀበና



የቅቤ ማስቀመጫ ጥወና ደንጋሳ ቁሶች



የሸክላ ቁሶች ሲተኮሱ





የሸክላ ቁሶች ሲተኮሱ

የሸክላ ቁሶች ሲተኮሱ





እንሰት በወለት ቁስ ሲነቀል

አመዳቸው ያልተራገፉ ቁሶች





የሸክላ ባለሙያዎች ቤት

ወደ ገበያ ጉዞ



አንጥረኛ ባለሙያዎች በስራ ላይ



የአንጥረኛ ውጤቶች



በመዶሻ ብረት ሲቀጠቅጡ



አንጥረኛ ባለሙያዎች በስራ ላይ



ባለሙያዎች ብረት ሲቀጠቅጡ



አንጥረኛ ባለሙያ በስራ ላይ

## አባሪ 9 ካርታዎች